
# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሰኞ 83ኛ ዓመት ቁጥር 336 ነሐሴ 6 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!

## ማሻሻያውና የጥቁር ገበያው ሰንሰለት ዕጣ ፈንታ


አዲሱ ገረመው


**ዜና ትንታኔ**

በቅርቡ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ይፋ ያደረገው የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ሥርዓት ማሻሻያ ለኢኮኖሚ ዕድገት ከሚያበረክተው አስተዋፅኦ ባሻገር ጥቁር ገበያን ሊያጠፋው እንደሚችል ምሁራን ይገልጻሉ።።

ለመሆኑ የጥቁር ገበያ መጥፋትስ ለሀገር ኢኮኖሚ ምን ፋዳ ይኖረዋል?

ትይዩ ገበያዎች በተለይ በማደግ ላይ ባሉ ኢኮኖሚዎች ላይ ሊያሳርፉ የሚችሉትን ተጽዕኖ አስመልክቶ የዓለም ባንክ ባወጣው መረጃ ጥቁር ገበያ ይፋዊ የኢኮኖሚ መረጃን በማዛባት ፖሊሲ አውጪዎች ትክክለኛውን የኢኮኖሚ ሁኔታ ለመገምገም እንዲቸገሩ ያደርጋል ሲል ያትታል።።

ከኦፊሴላዊው ሥርዓት ውጪ ከፍተኛ መጠን ያለው የገንዘብ ልውውጥ ሲደረግ የገንዘብ አቅርቦቱን፣ የዋጋ ግሽበትን እና ሌሎች ወሳኝ የኢኮኖሚ አመልካቾችን በትክክል


ማሻሻያውና የጥቁር ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል


## ቡና- የአፍሪካ ስትራቴጂካዊ ሸቀጥ


ዳግማዊት አበበ


**ዜና ትንታኔ**

በአሁኑ ጊዜ በዓለም ላይ ከሚመረተው የቡና ምርት አፍሪካ የምትሸፍነው 12 በመቶውን ብቻ ነው።። እ.ኤ.አ. በ2023 በዓለም አቀፍ ደረጃ 495 ቢሊዮን ዶላር ገቢ ከቡና ምርት የተገኘ ሲሆን አፍሪካ ከዚህ ውስጥ ያገኘችው ከአንድ በመቶ በታች መሆኑን በማሳያነት ማንሳት ይቻላል።።

በካምፓላ በተካሄደው የቡድን 25 የአፍሪካ ቡና አብቃይ ሀገራት ጉባዔ የቡና ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግና ንግዱን ለማስፋፋት ቡናን ከአፍሪካ ህብረት አጀንዳ የማጣጣምና የህብረቱ ስትራቴጂክ ሸቀጥ ሆኖ እንዲሰየም ውሳኔ ተላልፏል።።

በመቀጠልም ባለፈው የካቲት ወር 2016 ዓ.ም በተካሄደው 37ኛው የአፍሪካ የመሪዎች መደበኛ ጉባዔ ላይ ቡና የአፍሪካ ህብረት 2063 አጀንዳ እንደ አንድ ስትራቴጂካዊ ምርት ያጸደቀ ሲሆን


ቡና - የአፍሪካ ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል













## ታዳጊ የቀለም ቀንዶች


ሳሙኤል ወንደሰን


**ዜና ሐተታ**

በብላቴነት ዕድሜ፤ በለጋነት ዘመን ጨዋታ ሳያማልላቸው የስኬትን ኔክታር የቀመሱ የቀለም ቀንዶች ዛሬም አሉ። ብሩህ አዕምሯቸውን ለኪንና ለሳይንስ ያስገዙ፤ ብዕራቸውን ከበትር አጥብቀው የያዙ የመዲናችን ታዳጊዎች አስደማሚ ስኬት ለሌሎች "እነሆ ምሳሌ" ባይባል ንፉግ የሚያሰኝ ነው።

በተጠናቀቀው የትምህርት ዘመን ዕልፎች የ8ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ወስደዋል። ከነዚህ ተማሪዎች ውስጥ ደግሞ ከፍተኛ ውጤት በማምጣት ያስደመሙ አሉ።

ተማሪ ሱራፌል አያና፣ ተማሪ ሞቲ ተሾመ እና ተማሪ ኦብሲኔት ለማ ከቀለም ቀንዶቹ


ታዳጊ የቀለም ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል





# በከተማው በክረምት ወቅት የሚከሰቱ ድንገተኛ አደጋዎችን ለመቋቋም በቂ ዝግጅት ተደርጓል

- **በቅርቡ በደረሰው የመሬት መንሸራተት አደጋ የተፈናቀሉ ነዋሪዎች የሉም**

**መዓዛ ማሞ**

አዲስ አበባ፡- በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር በክረምትውቅት ሊገጥሙ የሚችሉ ድንገተኛ አደጋዎችን ለመቋቋም በቂ ዝግጅት መደረጉን የከተማዋ አደጋ ስጋት ኮሚሽን ገለጸ። በቅርቡ በደረሰው የመሬት መንሸራተት አደጋ የተፈናቀሉ ነዋሪዎች እንደሌሉም ጠቁሟል።

የኮሚሽኑ ኮሚሽነር አቶ ጣሂር ሮብሌ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ኮሚሽኑ በክረምት ወቅት አደጋዎች ሊያጋጥሙ ይችላሉ በሚል ዝግጅት አድርጓል። እንደ ድሬዳዋ ከተማ ጎርፍ ሊያጋጥም ይችላል በሚል ከከተማ አስተዳደር ጀምሮ እስከ ታችኛው መዋቅር ድረስ ቅድመ ዝግጅት ተደርጓል።

ወቅቱ ክረምት እንደመሆኑ ሕብረተሰቡ ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለበት ተናግረው፤ እርስ በእርስ በመረዳዳት የጎርፍ አደጋ ስጋት ከአለባቸው አካባቢዎች እንዲርቁ አሳስበዋል።

በቅርቡ በከተማዋ የደረሰው የመሬት መደርመስ አደጋ በሁለት ንኡስ ቀበሌዎች ላይ መሆኑን ጠቅሰው፤ በአደጋው በ21 አባወራዎች ላይ ከፊል የቤት መደርመስ፣ በ11 አባወራዎች በግምት የአንድ ነጥብ አምስት ሄክታር ላይ የማሳ የአፈር መናድ እንዲሁም በአንድ መኖሪያ ቤት ላይ ሙሉ መደርመስ አደጋ መድረሱን እና አራት ቤቶች ላይ ቀላል ጉዳት መከሰቱን ተናግረዋል።

እንደ ኮሚሽነሩ ገለጻ፤ አደጋው የደረሰባቸው ቦታዎች እና የሚያሰጉ ቦታዎች ተለይተዋል። በአካባቢው ያሉ ነዋሪዎች ተጨማሪ ስጋቶች የሚያጋጥሙ ከሆነ ወደ ሌላ ቦታ ለመቀየር እየተመቻቸ ነው።

ባጋጠመው የመሬት መደርመስ አደጋ ምንም የተፈናቀሉ ሰዎች የሉም ያሉት ኃላፊው፤ እስከ አሁን ሕብረተሰቡ እርስ በእርስ እየተረዳዳ ችግር የገጠማቸውን ወገኖች እያገዘ ይገኛል ሲሉ ገልጸዋል።

የአፈር መደርመስ አደጋ የደረሰባቸው ቀበሌዎች ገንደጀልዴ እና ጎላ አካባቢዎች በስጋት አካባቢነት መለየታቸውን በመጠቆም፤ በአካባቢው የሚኖሩ ሰዎች ጥንቃቄ እንዲያደርጉ አሳስበዋል።

አደጋ ስጋት ካለባቸው አካባቢዎች ነዋሪዎችን ለማንቀሳቀስ ብዙ ዝግጅት እንደሚያስፈልግ እና የባሰ ነገር የሚፈጠር ከሆነ ነዋሪዎችን ወደ ሌላ ቦታ የማዘዋወሩ ሥራ እንደሚተገበር አስረድተዋል።



# የከተማ አውቶብስ እና ሊሻሻል የሚገባው አገልግሎቱ

**ዮርዳኖስ ፍቅሩ**

**ዜና ሀተታ**

የመዲናዋ የከተማ አውቶብስ አገልግሎት የ 70 ዓመታት ዕድሜ ያስቆጠረ እና በቀን በአማካይ 600 ሺህ ነዋሪዎችን እያጓጓዘ ይገኛል።



የአውቶብስ አገልግሎቱ የክፍያ ታሪፍ ከሌሎች አማራጭ የትራንስፖርት አይነቶች ያነሰ በመሆኑ በብዙሃኑ አነስተኛና መካከለኛ ገቢ ባላቸው ነዋሪዎች ዘንድ ይዘወተራል። በአነስተኛ ክፍያ በአንድ ጉዞ ረጅም ኪ.ሜ የሚያጓጉዝ በመሆኑም ከተጠቃሚዎች ዘንድ “ባለውለታ” ተብሎም ይጠራል።

የከተማ አውቶብስ አገልግሎት የከተማዋና አጎራባች አካባቢ ነዋሪዎች ለረጅም ዓመታት የተገለገሉበት፣ ዛሬም የብዙኃኑ ምርጫ መሆኑ እሙን ሆኖ ሳለ፣ አገልግሎት አሰጣጡ ላይ ግን ቅሬታ ይነሳበታል። ተጠቃሚዎች ሊሻሻሉ ይገባል የሚሏቸው በርካታ ጉዳዮች አሉ።

የከተማ አውቶብስ ተጠቃሚ ወ/ሮ አበራሽ ዋሲሁን፣ ጠዋት ወደ ሥራ ለመውጣትም ሆነ ከሥራ ለመመለስ አውቶብስ እንደሚመርጡ ይናገራሉ።

እርሳቸው እንዳሉት፣ አውቶብሱን ፈልገው ቢጠቀሙም ብዙ ጊዜ ረጅም ሰዓት ቆመው ለመጠበቅ ይገደዳሉ። አውቶብስ ቆሞ መጠበቅ ደግሞ በተለይም ቀን በሥራ ለደከመና ለአቅመ ደካሞች በጣም አድካሚና አሰልቺ ይሆናል።

ከዚሁ ጋር አያይዘው፣ አውቶቡሶች ረጅም ሰዓት ቆይተው ሲመጡ የተሳፋሪው ቁጥር ከመብዛቱ የተነሳ ባሶች ከአቅማቸው በላይ የሆነ ሰው ጠቅጥቀው እንደሚጓዙ አንስተው፣ ይህም ለሌብነትና ሴቶችን ለወሲባዊ ትንኮሳ እያጋለጠ ነው ብለዋል።

የአውቶብስ ተጠቃሚው በሰላም ወጥቶ እንዲገባ አውቶብሶች በተገቢው ሰዓት ምልልስ እንዲያደርጉ መሥራት እና የአውቶቡሶችን ቁጥር በመጨመር ሰው ያለልክ ተጠቅጥቆ የሚጓዝበትን ሁኔታ ማስተካከል እንደሚገባ ጠቁመዋል።

አቶ ገዛኸኝ ይሁኔም የከተማ አውቶብስ የረጅም ዓመት ደንበኛ ናቸው። ለዓመታት በመጠነኛ ዋጋ ለከተማዋ ነዋሪ የትራንስፖርት አገልግሎት በመስጠቱ በእርሳቸውም ሆነ በአብዛኛው ነዋሪ ዘንድ የአውቶብስ አገልግሎት ተመራጭ መሆኑን ይናገራሉ።

ሶስትና አራት ታክሲ የሚፈልጉ ረጅም ርቀቶችን በአንድ ጉዞ መድረስ መቻሉም አውቶብስን በብዙሃን ዘንድ ተመራጭ አድርጎታል ይላሉ። ይህ እንዳለ ሆኖ ግን፣ የከተማ አውቶብስ አገልግሎት በርካታ ሊያስተካክላቸው የሚገቡ ጉዳዮች መኖራቸውን ያነሳሉ።

እርሳቸው ከጠቀሷቸው ጉዳዮች መካከል አንዱ የአውቶቡሶች ንጽህና ጉዳይ ሲሆን፣ አንዳንድ ጊዜ ውስጥና ውጪያቸው በጣም የቆሸሹ አውቶቡሶች እንደሚገጥሟቸው ይናገራሉ።

አውቶቡሶቹ በርካታ ሰዎችን ረጅም ርቀት የሚጓጉዙ በመሆናቸው ለመቆሸሽ ተጋላጭ እንደሚሆኑ ይታወቃል ያሉት አቶ ገዛኸኝ፤ ድርጅቱ ይህንን ታሳቢ ባደረገ መልኩ አውቶቡሶቹ ንጹህ ሆነው አገልግሎት የሚሰጡበትን ሁኔታ ቢያመቻች የሚል አስተያየት ይሰጣሉ።

አቶ ገዛኸኝ “ድርጅቱ ትልቅ ትኩረት ሰጥቶ ማስተካከል ያለበት ችግር ነው” ብለው ያነሱት በአንዳንድ የአውቶብስ አሽከርካሪዎችና ቲኬት ቆራጮች ላይ የሚታየውን የሥነ ምግባር ጉድለት ነው። እርሳቸው እንዳሉት፣ በአግባቡ አገልግሎት የሚሰጡ በርካታ ሹፌሮችና ቲኬት ቆራጮች እንዳሉ ሆነው፣ ከዚህ በተቃራኒ የሆኑና ተሳፋሪውን በእኩል ዓይን የማያስተናግዱ፣ ትንሽ ትልቅ ሳይሉ ከተሳፋሪ ጋር ስድብ የሚመላለሱ፣ ቆመው ሰው መጫን የሚገባቸውን ፌርማታ የሚያሳልፉ፣ ተሳፋሪውን ፌርማታ አሳልፈው የሚያወርዱ ሹፌሮችና ቲኬት ቆራጮች በብዛት እንደሚስተዋሉ አንስተዋል።

ድርጅቱ እንዲህ ያሉ ሥነ ምግባር የጎደላቸውን ሠራተኞቹን በአግባቡ ሊቆጣጠር ይገባል ያሉት አቶ ገዛኸኝ፤ ድርጅቱ ሠራተኞቹ በምን መልኩ አገልግሎት እየሠጡ እንዳሉ የሚያውቅበት መንገድ ቢያመቻች የተሻለ አገልግሎት እንዲሰጥ ያግዘዋል በማለት መክረዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አውቶብስ አገልግሎት ድርጅት ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ አካሉ አሰፋ፣ የሰዓት አጠቃቀምና ሰዎች ፌርማታ ላይ ረጅም ሰዓት ይቆማሉ በሚል የቀረበውን ቅሬታ አስመልክተው ሥራ አስፈጻሚው በባስ ፌርማታዎች ላይ አውቶብሱ ከመምጣቱ ቀደም ብሎ የመጣ ሰው ረጅም ጊዜ የሚቆይበት ሁኔታ ሊፈጠር እንደሚችል ያነሳሉ።

የዚህንም ምክንያት ሲያስረዱ እንዳሉት፣ የአዲስ አበባ ከተማ አውቶብስ አዲስ አበባ ላይ ብቻ ሳይሆን ከከተማ ውጪም ዜጎችን ያጓጉዛል። ከዚህ ረጅም ጉዞ በኋላ ሰው በሚጠብቅበት ፌርማታ ላይ እስኪደርስ ድረስ ጊዜ ይወስድበታል።

መንገድ በሚዘጋጋበት ጊዜ ደግሞ ይህ ሰው አውቶቡሱን የሚጠብቅበት ጊዜ ይረዝማል። ይህ ሁኔታ ወደፊት የአውቶብስ አቅርቦት እየተሻሻለ ሲመጣ የሚቀረፍ ይሆናል ሲሉ ያስረዳሉ።

አውቶቡሶች ከአቅም በላይ ከመጫን ጋር ተያይዞ የተነሳውን ቅሬታ በተመለከተም ሥራ አስፈጻሚው “በየትኛው ሀገር ቢሆን አውቶቡሶች አገልግሎት ሲሰጡ ወንበር ያገኘው ቁጭ ብሎ ወንበር ያላገኘ ሰው ደግሞ ቆሞ የሚሔድበት ሁኔታ ይኖራል።

በሀገራችን ያሉ ባሶች የወንበር ቁጥራቸው 42 እና 45 ሲሆን፣ ቆሞ የሚሄደውን ጨምሮ እስከ 70 ሰው ይጭናሉ። ካለው የተሳፋሪ ፍላጎት አኳያ፣ ሰው መንገድ ላይ ቆሞ ከሚቀር አውቶቡሶች እስከቻሉት ድረስ ቆመው መሄድ የሚፈልጉ ሰዎችን ይጭናሉ” በማለት ያስረዳሉ።

ይህ አይነቱ ጉዞ ለሌብነትና ለአላስፈላጊ ድርጊት የሚያጋልጥበት ሁኔታ ይስተዋልል የሚባለው እውነት ነው ያሉት ሥራ አስፈጻሚው፣ አውቶቡሶቻችን ውስጥ ፖሊስ የምናቆምበት አሠራር የለም ይላሉ።

ነገር ግን አውቶቡሶቻችን ሌብነትንና አላስፈላጊ ተግባራትን ለመቆጣጠር የሚያስችሉ 4 እና 5 ካሜራ የተገጠመላቸው ዘመናዊ አውቶቡሶች ናቸው ብለዋል። በአውቶቡሶች ካሜራ አማካኝነት እስካሁን ድረስ በርካታ ሌቦችን መያዝና ለፀጥታ አካላት ማስረከብ መቻሉንም አንስተዋል።

ከዚህ በበለጠ ግን እኛ ሕዝባችንን የምንመክረው ተገቢ ያልሆነ ድርጊት ሲከሰት አድራጊውን በማጋለጥና እርስ በእራሱም በመከባበር ጤናማ ጉዞ እንዲያደርግ ነው ብለዋል።

ከሥነ ምግባር ጋር ተያይዞ ያለውን ችግር አስመልክቶ ችግሮች መኖራቸውን አንስተው እነዚህን ለመፍታት የከተማ አስተዳደሩ ጥናት መሠረት ሪፎም ተዘጋጅቶ ወደ ሥራ መገባቱን ተናግረዋል።

በሪፎርሙ ከህብረተሰቡ ዘንድ የሚነሱ የአገልግሎት አሰጣጥ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል እንደሚሆን ተስፋቸውን ገልጸዋል።

ከንጽህና ጋር ተያይዞ ከተጠቃሚው የቀረበውን ቅሬታ የከተማዋ ነዋሪ የትራንስፖርት ፍላጎት ከድርጅቱ የአውቶብስ አቅርቦት በላይ በመሆኑ ድርጅቱ በአለው አቅም ነዋሪውን ለማገልገል ሲል አውቶቡሶቹ ከማለዳ እስከ ምሽት አገልግሎት እንደሚሰጡ ያነሳሉ። ከዚህ የተነሳ አውቶቡሶቹን በየቀኑ ለማጽዳት አስቸጋሪ ይሆናል ይላሉ።

ሆኖም አውቶብሶቹ ቢያንስ በሳምንት ሁለቴ እንዲታጠቡ እንደሚደረግ ጠቁመው፤ ከሥራው ባሕሪና ከአየር ጠባያችን አንጻር ግን፣ አውቶብሶች ጠዋት ታጥበው ማታ ሊቆሸሹ የሚችሉበት ሁኔታ ይፈጠራል ብለዋል።

አውቶቡሶቻችን በየቀኑ ቢጸዱ እኛም ደስ ይለናል ያሉት ሥራ አስፈጻሚው፣ ለወደፊቱ ለሕዝባችን ከዚህ የተሻለ ክብር ሰጥተን ጽዱ በሆኑ አውቶቡሶች ማገልገል ስላለብን፣ የጽዳት ማሽኖቻችንን ቁጥር በመጨመርና የጽዳት አገልግሎት አሠራርን በመቀየር በተቻለ አቅም የአውቶቡሶችን ንጽህና በየቀኑ ለመጠበቅ ጥረት እንደሚደረግ ገልጸዋል።

በመጨረሻም፣ ሥራ አስፈጻሚው፣ ህብረተሰቡ የራሱን ንብረት በአግባቡ ተንከባክቦ ጠብቆ በደረሰበት ሁሉ ክትትል እያደረገ ጉድለትም ሲያይ ጥቆማ እየሰጠ አግባብ ያለው አገልግሎት መስጠት እንዲቻል ትብብሩን ጠይቀዋል።

# በክልሉ የሻደይ፣ አሸንድዬና ሶለል በዓላትን ለማክበር የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች እየተሠሩ ነው

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- በአማራ ክልል በድምቀት የሚከበሩትን የሻደይ፣ አሸንድዬ፣ ሶለል እና ሌሎች በዓላትን በክልል ደረጃ ለማክበር የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑን የክልሉ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ አስታወቀ፡፡

የአማራ ክልል ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ዓባይ መንግሥቴ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በክልሉ የተለያዩ አካባቢዎች የአሸንድዬ፣ ሻደይ፣ ሶለል፣ የእንግጫ ነቀላ እና የቡሄ በዓላትን በድምቀት ለማክበር ከወረዳ ጀምሮ የተለያዩ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች እየተሠሩ ነው፡፡

በዓላቱ ትውፊታቸው ተጠብቆ በዋግሕምራ፣ በሰሜን ወሎ፣ በጎንደር፣ በጎጃምና በሌሎች አካባቢዎች እንዲከበር ለማድረግ፣ ወረዳዎች፣ ዞኖችና ከተማ አስተዳደሮች ትኩረት ሰጥተው እየሠሩ መሆናቸውን አስታውቀዋል፡፡

ከነሀሴ 17 ቀን 2016 ዓ.ም እስከ ነሀሴ 20 ቀን 2017 ዓ.ም ድረስ የአሸንድዬ፣ ሻደይ፣ ሶለል፣ ቡሄ እና የእንግጫ ነቀላ በዓልን በሚገልጽ መልኩ በክልል ደረጃ በባህርዳር ከተማ በድምቀት ለማክበር ታቅዷል ብለዋል፡፡

በዓላቱ የማህበረሰብ በዓል በመሆናቸው ትውፊታቸው ተጠብቆ እንዲከበር ማድረግ ይጠበቅብናል ያሉት አቶ ዓባይ፤ በዚህም ኮሚቴ በማቋቋም እና እቅድ በማዘጋጀት የተለያዩ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች እየተሠሩ እንደሚገኙ አመላክተዋል፡፡

ሻደይ፣ አሸንድዬ እና ሶለል ለልጃገረዶች የእኩልነት፣ የነፃነት እና የአንድነት ነፀብራቅ መሆናቸውን ገልጸው፤ በዓሉ በሚከበርባቸው ሁሉም ቦታዎች የሚገኙ ወጣቶች በዓላቱ እሴታቸው ተጠብቆ እንዲከበሩ በማድረግ የበኩላቸውን ኃላፊነት እንዲወጡ ጥሪ አቅርበዋል።

በክልሉ ከነሀሴ አጋማሽ ጀምሮ እስከ የካቲት ወር ድረስ የሚከበሩ በርካታ ሃይማኖታዊና ባህላዊ የአደባባይ በዓላት መኖራቸውን ገልጸው፤ በዓላቱን እሴታቸውን ጠብቆ በማክበር ለቱሪስት ክፍት ይደረጋሉ ብለዋል፡፡

በክልሉ የሚገኙ ባህላዊና ታሪካዊ የቱሪስት መዳረሻ ቦታዎችን እና የአደባባይ በዓላትን ለሀገር ውስጥና ለውጭ ጎቢኚዎች በተገቢው መንገድ በማስተዋወቅ ቱሪስቶች ወደ ክልሉ መጥተው እንዲዝናኑ እና እንዲያውቁት የማድረግ ሥራ በስፋት እንደሚሠራ አስታውቀዋል፡፡

አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ለቱሪስቶች ጥራት ያለው አገልግሎት እንዲያቀርቡ በማድረግ የቱሪስቶችን የቆይታ ጊዜ እንዲጨምር በማድረግ የቱሪዝም ገቢ እንዲያድግ እንደሚደረግ ጨምረው ገልጸዋል፡፡

የአካባቢው ማህበረሰብም የቱሪስቶችን ደህንነት በመጠበቅ የክልሉ ታሪካዊና ባህላዊ ቦታዎች እንዲጎበኙ በማድረግ ረገድ የበኩላቸውን ድርሻ ሊወጡ እንደሚገባ አሳስበዋል፡፡



አቶ አሕመድ ሻሚ

# በክልሉ ከ197 ሺህ በላይ ዜጎች ንጹህ የመጠጥ ውሃ ተጠቃሚ ተደርገዋል

**አማን ረሺድ**

አዲስ አበባ፡- በአፋር ክልል በጦርነት እና በተለያዩ ምክንያቶች የተጎዱ የውሃ ተቋማትን መልሶ በመገንባት ከ197 ሺህ በላይ ዜጎች ንጹህ የመጠጥ ውሃ አገልግሎት ተጠቃሚ ማድረጉን የክልሉ ውሐና ኢነርጂ ቢሮ አስታወቀ።

የአፋር ክልል ውሃና ኢነርጂ ቢሮ ኃላፊ አቶ አህመድ ሻሚ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በክልሉ በሰሜኑ ጦርነትና በተለያዩ ምክንያቶች በውሃ መሠረተ ልማቶች ላይ በደረሰ ውድመት በርካታ የማኅበረሰብ ክፍሎች ውሃ ሳያገኙ ቆይተዋል።

እነዚህን የማኅበረሰብ ክፍሎች ንጹህ የመጠጥ ውሃ እንዲያገኙ ለማድረግ በ2016 በጀት ዓመት በተሠራው የመልሶ ግንባታ ሥራ ከ197 ሺህ በላይ ዜጎች በድጋሚ የመጠጥ ውሃ አገልግሎት ተጠቃሚ ሆነዋል።

የመልሶ ግንባታ ሥራው የክልሉን መንግሥት ጨምሮ የተለያዩ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር በመተባበር የተከናወነ መሆኑን ጠቁመዋል።

እንደ አቶ አሕመድ ገለጻ፤ ህብረተሰቡ ተጨማሪ ንጹህ የመጠጥ ውሃ እንዲያገኝ ከማድረግ አኳያ በተሠሩ ሥራዎች አበረታች ውጤት ተገኝቷል።

የተጀመሩ ፕሮጀክቶችን በተያዘላቸው ጊዜ ለማጠናቀቅ የበጀት እጥረት፣ የዋጋ ንረትና የኮንትራክተሮች የአቅም ውስንነት ያጋጠሙ ተግዳሮቶች መሆናቸውን ጠቅሰው፤ ችግሩን ለመቅረፍ ከውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ጋር በቅንጅት እየተሠራ ይገኛል ብለዋል።

የአዋሽ፣ የሚሌ፣ የሎጊያና ሰመራ ከተሞች የውሃ ተደራሽነትን ለማሳደግ የሚያግዙ የተለያዩ የውሃ ፕሮጀክቶች እየተሠሩ መሆናቸውን ገልጸው፤ የህብረተሰቡን የውሃ ተጠቃሚነት ወደ ሚፈለገው ደረጃ ለማድረስ ክልሉ የበጀት እጥረት እንዳለበት አስረድተዋል።

በአዋሽ ከተማ ግንባታው ከተጀመረ ረጅም ዓመት ያስቆጠረ ፕሮጀክት መኖሩን አውስተው፤ በፍጥነት ለማጠናቀቅ በሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ደረጃ ከፍተኛ ድጋፍና ክትትል እየተደረገለት እንደሚገኝ ጠቁመዋል።

አቶ አሕመድ አክለውም፤ ቢሮው ለጤና ጣቢያ እንዲሁም ለተቋማት የሚሆኑ የተለያየ መጠን ያላቸው የሶላር ኃይል ቴክኖሎጂ ተከላና የማገዶ ቆጣቢ ምድጃዎችን ለማሰራጨት ዝግጅት እያደረገ ይገኛል ብለዋል።

በተጨማሪም ቢሮው ከክልሉ ኤሌክትሪክ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ጋር በመተባበር መብራት ባልተዳረሰባቸው ቀበሌዎችና መንገዶች ላይ እንዲደርስ የተለያዩ ሥራዎች መሠራታቸውን አቶ አሕመድ ገልጸዋል።

በክልሉ የሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች የአማራጭ ኢነርጂ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ከማድረግ አኳያ ጠንካራ ሥራ አለመሠራቱን አውስተው፤ በቀጣይ ስለ ማገዶ ቆጣቢ ምድጃ የማስተዋወቅና ግንዛቤ የመፍጠር ሥራ ትኩረት ተሰጥቶት እንደሚሠራ አመላክተዋል።

# ኢትዮ ቴሌኮም ከ900 ሺህ በላይ ዜጎችን ተጠቃሚ የሚያደርግ የገጠር ቴሌኮም አገልግሎት አስጀመረ

**አማን ረሺድ**

ቦሃባር፡- ኢትዮ ቴሌኮም በመላው ሀገሪቱ 903 ሺህ ዜጎችን ተጠቃሚ የሚያደርግ የገጠር ቴሌኮም አገልግሎት አስጀመረ፡፡

ኢትዮ ቴሌኮም በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ ዞን እዣ ወረዳ ቦሃባር ከተማን ጨምሮ በመላ ሀገሪቱ ገጠራማ አካባቢዎች ያስገነባቸውን 100 የገጠር ቴሌኮም ፕሮጀክቶችን አገልግሎት አስጀምሯል፡፡

በኢትዮ ቴሌኮም የኔትወርክ መሠረተ ልማት ምክትል ቺፍ ኦፊሰር አቶ አለም ኃይለማርያም በወቅቱ እንደገለጹት፤ ተቋሙ በአራት ምዕራፍ 500 የገጠር ሞባይል ኔትወርክ ሶልሽን ፕሮጀክት ለመገንባት የታቀደ ሲሆን በመጀመሪያው ምዕራፍ 100 የገጠር ቴሌኮም ፕሮጀክቶችን በመገንባት ህብረተሰቡን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል።

የቴሌኮም አገልግሎትን ተደራሽ በማድረግ ዘመኑ የደረሰበትን የቴክኖሎጂ ተጠቃሚነት ለማስፋት በትኩረት እየተሠራ መሆኑን ገልጸው፤ የተመረቁት ፕሮጀክቶች 903 ሺህ ዜጎች ተጠቃሚ ያደርጋል ብለዋል።

ዘርፉን በማጠናከር ዲጅታል ኢትዮጵያን እውን ለማድረግና የዘርፉን እድገት ለመደገፍ እንደሚሠራም ገልጸዋል።

አገልግሎት የጀመረውም የኔትወርክ መሠረተ ልማት የዚሁ ጥረት አካል መሆኑን ተናግረዋል።

ዜጎች ኔትወርክ እና ተዛማጅ አገልግሎት ለማግኘት በአማካይ እስከ 20 ኪሎ ሜትር የሚያደርጉትን ጉዞ በማሳጠር አካታች የዲጂታል ፋይናንስ አገልግሎት ተጠቃሚ ለማድረግ የሚያግዝ መሆኑን ጠቁመዋል።

አገልግሎቱ በገጠራማ የሀገሪቱ ክፍል የሚኖረው የማህበረሰብ ክፍል መሠረታዊ የቴሌኮም አገልግሎት እንዲያገኙ ያደርጋል ሲሉ አቶ አለም ተናግረዋል።

በተጨማሪም በትምህርት፣ በጤና፣ በግብርና እና በሌሎችም ዘርፎች የዲጂታል አገልግሎቶችን በማቅረብ የዜጎችን ሕይወት በማሻሻል ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው አብራርተዋል።

የቦሃባር ከተማ ሥራ አስኪያጅ አቶ ሲሳይ ሽምነሳ በበኩላቸው፤ ከዚህ ቀደም በከተማውና በአካባቢው በሚገኙ ቀበሌዎች ላይ የኔትወርክ አገልግሎት ባለመኖሩ ለከፍተኛ ችግር መጋለጣቸውን ገልጸው፤ ፕሮጀክቱ መገንባቱ በአካባቢው የሚኖሩ አርሶ አደሮች ኢኮኖሚያቸውን እንዲያሳልጡ፣ ባንኮች እንዲከፈቱና የቁጠባ ባህል እንዲያድግ ትልቅ ፋይዳ ይኖረዋል ብለዋል።

ፕሮጀክቱ የአካባቢው ማህበረሰብ በቴሌብር አማካኝነት ገንዘብ ከመላክ፣ ከመቀበልና ግብይት ከማከናወን ባሻገር ኑሮውን ለማሻሻል እንደሚረዳው ጠቁመዋል፡፡

ኢፕድ ያነጋገራቸው የቦሃበር ከተማ ነዋሪ የሆኑት መምህር ኑሬ መንገሻ እንደገለጹት፤ ከዚህ ቀደም የኔትወርክ አገልግሎት ባለመኖሩ ከፍተኛ ችግር ውስጥ ቆይተዋል፡፡

ነግር ግን አሁን ላይ ፕሮጀክቱ አገልግሎት በመጀመሩ የሞባይል ዳታ እና የስልክ አገልግሎት መጠቀም ችለናል ብለዋል።

ሌላኛዋ የከተማው ነዋሪ ወይዘሮ ሰሚራ ሙሰማ በበኩላቸው፤ ከዚህ ቀደም ምንም አይነት የቴሌኮም አገልግሎት በከተማው አለመኖሩን ገልጸው በዚህም ለዘርፈ ብዙ ችግሮች ተዳርገን ቆይተናል ሲሉ አስረድተዋል።

አሁን ላይ የሞባይል አገልግሎት ተጠቃሚ በመሆናቸው መደሰታችን አውስተው ኢትዮ ቴሌኮምን አመስግነዋል።



# የዓለም አቀፉ የክህሎት ማህበረሰብ አባል መሆን የወጣቶችን ክህሎት ለማሳደግ ይረዳል

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ የዓለም አቀፉ የክህሎት ማህበረሰብ አባል ሆና መቀላቀሏ የወጣቶችን ክህሎት በዓለም አቀፍ ደረጃ ለማሳደግ እንደሚረዳ የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር አስታወቀ።

ኢትዮጵያ የዓለም አቀፍ የክህሎት ማህበረሰብ አባል መሆኗን አስመልክቶ የሥራና ክህሎት ሚኒስትር ሙፈሪሃት ካሚል እንደገለጹት፤ ላለፉት ዓመታት የዓለም አቀፍ የክህሎት ማህበረሰብ መስፈርቶችን አዘጋጅቶ የተለያዩ የአፍሪካና የዓለም ሀገራትን በአባልነት ሲቀበል ቆይቷል። በዚህም ኢትዮጵያ የዓለም አቀፍ የክህሎት ማህበረሰብ 88ኛ አባል ሀገር ሆና ተቀላቅላለች።

ኢትዮጵያ አባል መሆኗ በክህሎት ምህዳር ውስጥ ትልቅ ፋይዳና ትርጉም እንዳለው በመጥቀስ፤ ወጣቶች ክህሎታቸውን እንዲያሳድጉ እና ተወዳዳሪ እንዲሆኑ እገዛ እንደሚያደርግ አመልክተዋል። በተለይ የወጣቶች ሙያና ክህሎት ቦታ እንዲኖራቸው የሚያስችል መድረክ በመሆኑ ለወጣቶች ትልቅ ጠቀሜታ እንዳለው አስረድተዋል።

ኢትዮጵያ ለጥቁርና ለመላው ግፉዓን ሕዝቦች ነጻነት ፋና ወጊ የሆነች ሀገር ናት ያሉት ወይዘሮ ሙፈሪሃት፤ አባል መሆኗ ጠቀሜታው አፍሪካዊ ጭምር መሆኑን አስገንዝበዋል። የአፍሪካ ህብረት የ2063 አጀንዳን ቀርጾ እንደ አህጉር እየተንቀሳቀሰ እንደሚገኝ ጠቅሰው፤ አፍሪካውያን በዓለም አቀፍ ደረጃ በክህሎት ዐሻራ ማሳረፍ ሂደት ውስጥ ኢትዮጵያ የራሷን ሚና እየተጫወተች እንደምትገኝ ተናግረዋል።

እንደ ሚኒስትሯ ገለፃ፤ አባልነቱ ከተቀረው ዓለም የሚፈጠሩ ተጨማሪ እድሎችን ለማግኘት የሚያስችል እና አዲስ አውድ የሚፈጥር ነው። ከመላው ዓለም የሚመጡ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች በየሁለት ዓመቱ በአንድ ላይ ተገናኝተው የሚያካሂዱት መድረክ በመሆኑ



ወይዘሮ ሙፈሪሃት ካሚል

የክህሎት ሽግግር፣ ወጣቶች የልምድ ልውውጥ ለማድረግ የሚያስችሉ እድሎችን ይፈጥራል።

አባል ለመሆን ከሁለት ዓመት በላይ ጠንካራ ሥራ መሠራቱን ጠቅሰውም፤ በዚህም ጥሩ ውጤትም ማግኘት መቻሉን ጠቁመዋል። ኢትዮጵያ በአሁኑ ጊዜ በዓለም አቀፍ የክህሎት ማህበረሰብ ውስጥ ከአባልነት በላይ በአመራርነት የምታገለግልባቸው መድረኮች እንዳሉም አመላክተዋል።

የ2024 የዓለም ክህሎት ውድድር በፈረንሳይ እንደሚካሄድ ጠቁመው፤ ኢትዮጵያ የውድድር ኮሚቴ ውስጥ በቋሚ ኮሚቴነት መወከሏን ተናግረዋል። እንዲሁም በአስተዳደር መዋቅር ውስጥ ተወክላ አስተዋጽኦ እያበረከተች ትገኛለች ብለዋል።

ፈረንሳይ በሚካሄደው የክህሎት ውድድር ላይ ኢትዮጵያ በሶስት መሠረታዊ የሥራ መስኮች ለመወዳደር ዝግጅት እያደረገች ነው ያሉት ሚኒስትሯ፤ በጣውላ ሥራ ዘርፍ፣ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ (አይቲ) እና በማሽን ማምረት ዘርፎች ላይ ሙያተኞች ዝግጅት እያደረጉ ነው። ለኢትዮጵያ የመጀመሪያ መድረክ በመሆኑ በቂ ልምድና ትምህርት እንደሚቀስምበት ጠቁመዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የአየር መንገዳችን ሌላው ከፍታ!

የኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን መገለጫና ኩራት የሆነው የኢትዮጵያ አየር መንገድ በአፍሪካ የአየር መንገድ ኢንዱስትሪም በመሪነት ሚናው ይታወቃል። በዓለም አቀፍ ደረጃም የበረራ አድማሱን በማስፋት አገልግሎቱንም የተቀላጠፈና የዘመነ በማድረግ ዝናን አትርፏል።

አየር መንገዱ በእዚህ ሁሉ የላቀ ተግባሩ በከፍታ ላይ ከፍታን እየደረበ ይገኛል። የበረራ አድማሶቹን በማስፋት፣ ዘመናዊ አውሮፕላኖችን በመጠቀም፣ የአውሮፕላኖቹን ብዛት በየጊዜው በማሳደግ፣ የአውሮፕላን ባለሙያዎችን በማሰልጠን፣ የሌሎች ሀገሮችን አውሮፕላኖችን ጨምሮ በመጠገን፣ ወዘተ ዝናው በዓለም የናኘ ነው።

ዓለም አቀፍና አህጉራዊ ተቋማት በርካታ እውቅናዎችን በማግኘትም ይጠቀሳል። የቅርብ የሆኑትን እንኳ ብንጠቅስ በኮቪድ 19 ወረርሽኝ ወቅት ዓለም በሩን ዘግቶ ተቀምጦ እያለ በዓለም አቀፍ ደረጃ መንገደኞችንና መድሃኒቶችን በማጓጓዝ የሰው ልጅን ሕይወት በመታደጉም ይታወሳል። በዚህም ሠብዓዊ ተግባሩ በቅርቡ ዓለም አቀፍ እውቅና ተቸሮታል። አየር መንገዳችን በአሜሪካ ላደረገው አገልግሎትም የፕሬዚዳንት ጆ ባይደን ፊርማ ያረፈበትን የአሜሪካ ፕሬዚዳንት የስኬታማነት ሽልማትን በቅርቡ በፕሬዚዳንት ጆ ባይደን ተበርክቶለታል።

አየር መንገዱ አሁንም ይህን ከፍታውን ወደ ላቀ ደረጃ ለማድረስ የሚያስችሉትን ተግባሮች ማከናወኑን ቀጥሏል። እየጨመረ የመጣውን የመንገደኞች ብዛት በሚገባ ማስተናገድ የሚያስችለውን ግዙፍና ዘመናዊ የአውሮፕላን ማረፊያ ለመገንባት እያከናወነ ያለው ተግባርም ይህንኑ ያመለክታል።

የኢትዮጵያ አየር መንገድ ከቢሾፍቱ ቅርብ ርቀት ላይ አቡሴራ በሚባል አካባቢ ለሚያስገነባው ግዙፍ የአውሮፕላን ማረፊያ የዲዛይን ሥራና የማማከር አገልግሎት ከሚያካሂደው «ዳር» ከተሰኘው ታዋቂ የውጭ ኩባንያ ጋር ስምምነት ተፈራርሟል። በስድስት ቢሊዮን ዶላር የሚገነባው ይህ ዓለም አቀፍ የአውሮፕላን ማረፊያ እየጨመረ የመጣውንና በቀጣይም የሚጨምረውን የአየር መንገዱን ተጓዦች ብዛት ለማስተናገድ እንዲሁም ሀገሪቱን የአፍሪካ ዋና የአቪዬሽን ኢንዱስትሪ ማእከል ማድረግን ያለመ ነው።

ኩባንያው በኢትዮጵያ፣ በኬንያ፣ በኡጋንዳ ሌሎች ሀገራት የአውሮፕላን ማረፊያ ግንባታ ዲዛይን በመሥራትና በማማከር አገልግሎት የሚታወቅ ሲሆን፣ የዲዛይን ሥራውን በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ሠርቶ የሚያስረክብ ይሆናል፤ በግንባታ ተቋራጭ መረጣ ላይ በሚካሄደው ሥራም አማካሪ ሆኖ ይሠራል። ከዚህ ሁሉ መረዳት የሚቻለው የግንባታ ፕሮጀክቱ በከፍተኛ የኤክስፐርት ደረጃ እና አቅም እንደሚካሄድም ነው።

የአውሮፕላን ማረፊያው ግንባታ ፕሮጀክት በሁለት ምዕራፍ የሚካሄድ ሲሆን፣ በመጀመሪያው ምዕራፍ በአመት 60 ሚሊዮን መንገደኞችን ማስተናገድ የሚችል የግንባታ ፕሮጀክት ይካሄድበታል። ግንባታውም በአምስት ዓመታት ውስጥ እንዲጠናቀቅ ተደርጎ ነው የሚካሄደው። ትልቅ ኢንቨስትመንት የሚካሄድበትም ነው።

ሁለተኛው ምዕራፍ እጅግ ሰፊና የአየር ማረፊያውን መንገደኞች የማስተናገድ አቅም በዓመት ወደ 100 ሚሊዮን የሚያሳድግ ይሆናል። የአየር ማረፊያውን ከቦሌ ዓለም አቀፍ አየር ማረፊያ ጋር የሚያስተሳስሩ የባቡርና የመንገድ መሠረተ ልማቶችን ጨምሮ ሌሎች ሰፋፊ ተያያዥ ሥራዎች የሚካሄዱበትም ይሆናል።

አየር መንገዱ ይህን ግዙፍ ፕሮጀክት ለመገንባት መንቀሳቀስ ከጀመረ ቆይቷል፤ አሁን ወደ ዋናው ግንባታ ለመግባት ወደሚያስችለው ወሳኝ ሥራ ገብቷል። የዚህ አውሮፕላን ማረፊያ ፕሮጀክት ወደ ትግበራ እየተሸጋገረ መምጣት በራሱ የአየር መንገዱን ጥንካሬ፣ በከፍታ ላይ ከፍታ የመደረብ ህልሙን እውን ለማድረግ ምን ያህል ቁርጠኛ እንደሆነ ይጠቁማል።

አየር መንገዳችን በከፍታ ላይ ከፍታ እየደረበ የመጣው ግን ነገሮች አልጋ ባልጋ ሆነውለት እንዳልሆነም መታወቅ ይኖርበታል። በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተቋሙን ስም ለማጥፋት ሙከራዎች ተደርገውበታል። ለእነዚህ ሙከራዎች ጆሮም ሳይሰጥ ሥራና ሥራውን ብቻ እየተመለከተ «ውሾቹ ይጮኻሉ ግመሉ ግን መንገዱን ቀጥሏል» እንደሚባለው አየር መንገዱ ለላቀ አገልግሎት የሚያበቁትን ግዙፍ ተግባራት እያከናወነ ስሙንና አቅሙን በእጅጉ እየገነባ ይገኛል።

አየር መንገዱ ዘመኑ ያፈራቸውን ቴክኖሎጂዎች እየተጠቀመ፣ ብቃት ያላቸው ባለሙያዎችን እያፈራ የሀገር ውስጥ በረራውን እያሰፋ በአፍሪካም ሆነ በመላው ዓለም ተወዳዳሪነቱን ወደ ላቀ ደረጃ እያደረሰ ነው ለእዚህ ከፍታ የበቃው። በቀጣይም የሚሆነው ይሄው ነው። ምክንያቱም ኢትዮጵያን ኢትዮጵያውያንን የሚመጥነው ሁሌም ከፍ ማለት ነውና!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው።በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።

## የሀገር ውስጥ ባንኮችን ተፎካካሪነት ለማሳደግ

**ኃይለማርያም ወንድሙ**

በወርሃ ሰኔ 2016 ዓ.ም በኢትዮጵያ የባንክ ዘርፍ ለውጭ ኢንቨስትመንት ክፍት እንዲሆን የሚያስችል ተስፋ ሰጪ ርምጃ ተጀምሯል። ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የተመራው የባንክ ሥራ ረቂቅ ማሻሻያ አዋጅ በመንግሥት የተላለፈውን የፖሊሲ ውሳኔ ወደ ተግባር ለማሸጋገር ያለመ ነው። አዋጁን ተከትሎ የውጭ ሀገር ባንኮች ወደ ኢትዮጵያ ገብተው ሥራ ሲጀምሩ ለዜጎች ጥሩ የባንክ አማራጭ ሊሆኑ ይችላሉ ፤ አዳዲስ አማራጮችንና ቴክሎጂዎችን እንድንጠቀም በር ይከፍታል። መንግሥት የባንኩን ዘርፍ ለውጭ ኢንቨስተሮች ክፍት ማድረግ "አገልግሎቶች በእውቀት እና በቴክኖሎጂ ለመደገፍ፣ የሀገሪቱን ምጣኔ ሀብት ከዓለም አቀፍ ገበያ ጋር የበለጠ እንዲተሳሰር ለማድረግ ያስችላል "የሚል እምነት አለው።

ሃሳቡ ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ አዲስ የሚባል ቢሆንም ከኢትዮጵያ ያነሰ ምጣኔ ሀብት ያላቸው የአፍሪካ ሀገራት ጭምር ከውጭ ባንኮች ጋር መሥራት ከጀምሩ ዓመታት ተቆጥረዋል። ኬንያ ፣ ሱዳን ፣ ጋና ፣ ናጄሪያ እና ደቡብ አፍሪካ የውጭ ባንኮችን በሀገር ውስጥ በማሳተፍ ጥሩ የሚባል ተሞክሮ ያላቸው ናቸው ። ይህን ተከትሎም የውጭ ባንኮች ወደ ኢትዮጵያ መግባት በርካታ ጠቀሜታዎች እንዳሉት የምጣኔ ሀብት ባለሙያዎች ይስማማሉ።

የውጭ ሀገር ባንኮቹ የሚመጡት ከበለፀገ ሀገር በመሆኑ ከፍተኛ የሆነ የፋይናንስ ቴክኖሎጂ ይዘው ይገባሉ። የውጭ ባንኮቹ ደንበኛው በቤት ውስጥ ሆኖ ሁሉንም የባንክ አገልግሎቶች የሚያገኝበትን አሠራር ይዘው እንደሚመጡ ይጠበቃል። በባንኮች መካከል ፉክክር በማሳደግ ተጠቃሚው የተሻለ አማራጭ እንዲያገኝ ዕድል እንደሚፈጥር ይታመናል።

ባንኮቹ ወደ ኢትዮጵያ ሲገቡ እንደማንኛውም የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት በውጭ ምንዛሪ ኢንቨስት የሚያደርጉ በመሆኑ እንዲሁም የሥራ ፈቃዳቸውንና ሌሎች ወጪዎቻቸውን በውጭ ምንዛሪ የሚከፍሉ በመሆኑ ያለውን የምንዛሪ ችግር ያቃልላል። ወደ ሀገር ውስጥ ሲገቡ እነሱን ተከትለው የሚገቡ የውጭ ኢንቨስተሮች እና ተቋማት ይኖራሉ።

ይህ ኢኮኖሚው ላይ የውጭ ምንዛሪ በማምጣትና የሀገሪቷን ምርት በማሳደግ እንዲሁም የሥራ ዕድል በመፍጠር የራሱ ትልቅ ጠቀሜታ አለው። በሌላ በኩል የውጭ ባንኮች መግባት ወደ ሥራ ለመሠማራት ለተዘጋጁ ወጣቶች የብድር አማራጭ በመሆን ለሥራ ፈጣሪዎች ጥሩ ዕድል ይዞ የሚመጣ ነው።

ባንኮቹ የራሳቸውን ትልቅ ካፒታል ይዘው የሚመጡ በመሆኑ የነበሩ የአነስተኛ ብድር እጥረቶችን እና ያለዋስትና ብድር የማግኘት ችግሮችን እንደሚቀርፉም ይታመናል። የውጭ ባንኮቹ መግባት ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ማደግ ትልቅ ፋይዳ ቢኖረውም ፤ አዋጁን ተከትለው በሚወጡ መመሪያዎች ላይ ከፍተኛ ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበትም ባለሙያዎቹ ይመክራሉ። መንግሥት የባንኩን ዘርፍ ለውጭ ኢንቨስትመንት ክፍት ማድረጉና የውጭ ባንኮቹ መግባት የሀገር ውስጥ ባንኮችን ባለአክሲዮኖችን ሕልውናን እስከመፈታተን ሊደርስ ይችላል።

የሀገራችን ባንኮች ለተወሰኑ አቅም ላላቸው ጥቂት ባለሀብቶች ከማበደር ባለፈ፤ ድሃውን እና በገጠር የሚኖረውን ኢትዮጵያዊ በአግባቡ እያገለገሉ ናቸው ለማለት አያስደፍርም። የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ዋነኛ ምሰሶው ግብርናው በሆነበት ሁኔታ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ገበሬው ከባንኮች መበደር የሚችልበት አማራጭ አልነበረውም ።

ከብት የሚያረቡም፣ ቡና፣ የቅባት እህል ፣ አዝዕርትና አትክልት አምርተው የሚሸጡ ገበሬዎችን ባንኮቻችን ሊደግፉ የቻሉበት መንገድ ብዙም አይታይም። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በወጣ መመሪያ ገበሬው የሚያርስበትን መሬት አስይዞ ብድር ሊያገኝና ሊሠራ የሚችልበትን እየተመቻቸ ነው።

አሁንም ቢሆን በገጠር እየኖሩ ገንዘባቸውን በባንክ ማስቀመጥ እንዳለባቸው የማይገነዘቡ ዜጎች ሞልተዋል። ለገበሬው ግንዛቤ ሰጥተው ተበድረው በመስኖ ምርት ማምረት የሚችሉበትን ሁኔታ አልተፈጠረም። እነዚህ እና መሰል ውስንነቶች የሚስተዋሉባቸው የሀገር ውስጥ ባንኮች ከውጭ ባንኮች ጋር መፎካከር ይችላሉ ለማለት አያስደፍርም።

**ባንኮቹ የራሳቸውን ትልቅ ካፒታል ይዘው የሚመጡ በመሆኑ የነበሩ የአነስተኛ ብድር እጥረቶችን እና ያለዋስትና ብድር የማግኘት ችግሮችን እንደሚቀርፉም ይታመናል**

በጥቅሉ የሀገር ውስጥ የባንኮቻችን የወለድ ምጣኔ፣ ማስያዣ እና ሌሎችም የብድር አሠራሮች ለተገልጋዩ የተመቸ አይደለም። ከባለ አክሲዮኖች በተሰበሰበ ገንዘብ፣ ከቁጠባ፣ ከብድር ወለድ እንዲሁም ከአገልግሎት ክፍያ በሚያገኙት ገንዘብ የሚንቀሳቀሱት የሀገር ውስጥ ባንኮች ከውጭ ባንኮች ጋር በካፒታል የመፎካከር አቅም አይኖራቸውም።

የሀገር ውስጥ ባንኮች ከውጪ ባንኮች በውድድር ወቅት የሚጠብቃቸውን ስጋት ለመቋቋም መሰባሰብ ይጠበቅባቸዋል። ይህም በሰው ሃይል እና በገንዘብ አቅማቸውን በማቀናጀት የተሻለ ቁመና እንዲኖራቸው ያስችላቸዋል።

ከዚህም ጎን ለጎን ከውጪ ከሚገቡ ባንኮች ካፒታል መበደርና አብሮ በመሥራት ተወዳዳሪ መሆን ይጠበቅባቸዋል። አሁን ባለው ሁኔታ የሀገር ውስጥ ባንኮች በቴክኖሎጂ፣ በአሠራር ፣ በደንበኛ አያያዝ፣ በአገልግሎት እና በፋይናንስ አሳታፊነት ክፍተት አለባቸው።

በአጠቃላይ የሀገር ውስጥ ባንኮቻችን መጪውን የውድድር ጊዜ ለመቋቋም አሠራራቸውን ከወዲሁ መለወጥ ይጠበቅባቸዋል። ትላልቅ ባለሀብቶች ወይም ተበዳሪዎች ላይ ብቻ ትኩረት ከማድረግ አዋጭ ለሆኑ ጥቃቅን ቢዝነሶች ብድሮችን በመስጠት የራሳቸውን ደንበኛ መፍጠር ላይ ሊሠሩ ይገባል። በተጨማሪም እንደ ግብርና እና አገልግሎት ዘርፍ ያሉ ግዙፍ የኢኮኖሚ ምንጮች ላይ በተለየ መንገድ ኢንቨስት በማድረግ የካፒታል አቅማቸውንም ማሳደግ ይኖርባቸዋል።

እዚህ ጋር ከሰሞኑ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዐቢይ አሕመድ የማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲ ማሻሻያውን ተግባራዊ ማድረግ ተከትሎ ከባለድርሻ አካላት ጋር በነበራቸው የውይይት መድረክ ላይ ያነሱትን ምክረ ሃሳብ ማየት ተገቢ ይሆናል። እንደ እርሳቸው ሃሳብ የውጪ ሀገር ባንኮች በኢትዮጵያ እንዲሠሩ ለመፍቀድ እየተደረገ ያለው ዝግጅት የሀገር ውስጥ ባንኮችን የሚያነቃቃ እንጂ ስጋት የሚሆን አይደለም። ለዚህ በማሳያነት የጠቀሱት ኢትዮቴሌኮምን ነው። ሳፋሪ ኮም የቴሌኮም ዘርፉን ሲቀላቀል በሚያስገርም ፍጥነት ኢትዮቴሌኮምም የማይጠበቅና ፈጣን የሆነ እድገት አሳይቷል። ይህ ሊሆን የቻለው በገበያው ላይ የውድድር ስሜት መፈጠሩና አዳዲስ የአሠራር ሥርዓቶችና የፖሊሲ ማሻሻያዎች በመደረጋቸው እንደሆነ በማብራሪያቸው ላይ ገልፀዋል።

ይህ ሃሳብ በባንኮች ላይ እንደሚሠራም ጠቁመው የመጣ ያለውን እድል እንዲጠቀሙበት አሳስበው ነበር። በተለይ በአንድነት አቅማቸውን ቢያሰባስቡና ቢዋሃዱም የሚመጣውን ውድድር ማሸነፍ እና ህልውናቸውን ማስጠበቅ እንደሚያስቸላቸው መክረው ነበር። ከዚህ መረዳት እምንችለው የፋይናንስ ዘርፉ ግልፅ በሆነ ፖሊሲ እና ሕግን የተከተለ ውድድር እንደሚመራ ነው። ሥርዓቱ ተዘርግቶ ተግባር ላይ ሲውል ደግሞ የሀገር ጥቅል ኢኮኖሚ፣ የባለሀብቶችና የነጋዴዎች እንዲሁም የእያንዳንዱ ዜጋ ላይ ቀጥተኛ አዎንታዊ ተፅእኖ እንደሚኖረው ነው። በመሆኑም የፋይናንስ ዘርፉ ለውጪ ኢንቨስተሮች ክፍት በመሆኑ ለኢትዮጵያ አያሌ በረከቶችን የዞ እንደሚመጣ ይጠበቃል።

ዜና

# ቡና - የአፍሪካ ስትራቴጂካዊ ...

ከ 1ኛ ገፅ የዞረ

የአፍሪካ ቡና አብቃይ ሀገራት ድርጅትንም የአፍሪካ ህብረት ልዩ ኤጀንሲ አድርጎ ሾሟል፡፡

ለመሆኑ የአፍሪካ ቡና አብቃይ ሀገራት ድርጅት ህብረቱ ያስተላለፈው ውሳኔ የሚያስገኘው ፋይዳ ምንድነው?

የአፍሪካ ቡና አብቃይ ሀገራት ድርጅት ሊቀ መንበር እና የኢትዮጵያ የግብርና ሚኒስትር ግርማ አመንቴ፣ ቡና የህብረቱ ስትራቴጂካዊ ሸቀጥ ተድርጎ መሰየሙ ከኢኮኖሚ አንጻር ትልቅ ለውጥ የሚያመጣ መሆኑን ጠቅሰው፤ ውሳኔው ለአፍሪካ ቡና አምራች ገበሬዎች መልካም ዜና ነው ይላሉ።

ቡና የአፍሪካ ዋነኛ ምርት እንዲሆን የተወሰነው ውሳኔ ዋና ጠቀሜታው በተለይም የአፍሪካ መሪዎች በቅርቡ ተግባራዊ ያደረጉት የአፍሪካ ነጻ የንግድ ቀጣና ስምምነት ላይ በመመሥረት ከአንዱ የአፍሪካ ጫፍ ወደ ሌላኛው የአህጉሪቱ ጫፍ ቡናን በተመሳሳይ ታሪፍ፣ ጥራት፣ ሕግና መመዘኛ መገበያየት እንዲያስችል ማድረጉ የሚያስችል መሆኑን ያስረዳሉ፡ ፡ በተጨማሪም በአህጉሪቱ ውስጥ ላሉና ቡና አምራች ላልሆኑ ሀገራት የቡና ምርት ላይ ትኩረት አድርገው እንዲሰሩ ትልቅ መነሳሳትን የሚፈጥር መሆኑንም ይገልጻሉ፡፡

በሌላ በኩል ውሳኔው የቡና ምርት፣ ጥራትና ንግዱን ለመደገፍ የአፍሪካ ልማት ባንክን ጨምሮ የአፍሪካ የፋይናንስ ተቋማት በቡና ምርት ላይ ለተሰማሩ ባለሀብቶች ልዩ ድጋፍ እንዲያገኙ የሚያደርግ ነውም ይላሉ፡፡

ቡና በአፍሪካ ህብረት አጀንዳ 2063 መካተቱ አፍሪካ ከዚህ በኋላ በቡና ምርት ዙሪያ የተባበረ ድምጽ እንዲኖራት የሚያደርግ ከመሆኑ ባሻገር ዓለም ላይ ቡናን በተመለከተ የትኛውም ውሳኔ ላይ እንደ አንድ የምትወሰን ይሆናል ሲሉ ይናገራሉ፡፡

የአፍሪካ ቡና በአሁኑ ጊዜ ወደ ገበያ እየቀረበ ካለው 99 በመቶው በጥሬው ነው የሚሉት ሊቀመንበሩ፤ በቀጣይ የትኩረት አቅጣጫ ተብሎ የተያዘው አፍሪካ የቡና ምርቷ ላይ እሴትን ጨምራ ወደ ገበያ በማቅረብ የሚገኘውን ገቢ ማሳደግ ይገባል የሚል መሆኑን ይገልጻሉ፡፡

ኢትዮጵያ ዘንድሮ ለመጀመሪያ ጊዜ ከቡና የወጪ ንግድ አንድ ነጥብ አራት ቢሊዮን ዶላር ማግኘቷን ያነሱት ሊቀመንበሩ፤ ይህም እስካሁን ካሉት ዓመታት ከፍተኛው መሆኑን ይጠቁማሉ፡፡

አሁን ላይ የቡና የወጪ ንግድ በኢትዮጵያ ካለው አጠቃላይ የወጪ ንግድ 36 በመቶውን መያዙን በመጠቆም፤ ይህም ለሀገሪቱ ቡና ወሳኝ ምርት መሆኑን ማሳያ እንደማሳያ የሚጠቀስ ያስረዳሉ፡፡

ሊቀመንበሩ እንደሚሉት፤ ኢትዮጵያ በቡና ምርት ላይ ኑሯቸውን መሠረት ያደረጉ አምስት ሚሊዮን አባወራ ያሉባት ሀገር መሆኗ እና በቡና ምርት ከአፍሪካ ኡጋንዳን በማስከተል የምትመራ መሆኗ ውሳኔው ከየትኛውም የአፍሪካ ሀገራት የበለጠ ተጠቃሚ ያደርጋታል ይላሉ፡፡

ባለፉት ዓመታት በተደረጉ ጥረቶች ውሳኔው እንዲተላለፍ በመደረጉና ኢትዮጵያም የአፍሪካ ቡና አብቃይ ድርጅትን በሊቀመንበርነት እንድትመራ መደረጉ የኢትዮጵያን ቡና ለሌሎች ሀገራት ለማቅረብ፤ ለመገበያየት እና የንግድ መዳረሻዎችን ለማስፋት ትልቅ እድል ይዞ የመጣ ነው ሲሉም ተናግረዋል፡፡

እድሉን በመጠቀምም በቡና ምርት፣ ጥራት እንዲሁም ንግድ ላይ በትኩረት መሥራት ያስፈልጋል ሲሉ አስተያየታቸውን ይሰጣሉ፡፡

የግብርና፣ የገጠር ልማት፣ የብሉ ኢኮኖሚ እና የዘላቂ ልማት ኮሚሽነር አምባሳደር ጆሴፋ ሊዮን እንደሚሉት ፤ ከ70 በመቶ በላይ የሚሆኑት የአፍሪካ ዜጎች ኑሯቸው በቡና ምርት ላይ የተመሠረተ በመሆኑ ከዘርፉ የሚገኘውን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ መገንዘብ አስፈላጊ ነው፡፡

ቀጣናዊ ትብብርን ማስፋት ፣ የሥራ እድሎች መፍጠር ፣ ከአፍሪካ ህብረት ዋና ተግባራት መካከል ናቸው ያሉት አምባሳደር ጆሴፍ በመሆኑም ውሳኔው የአፍሪካ ቡና አብቃይ ሀገራት ቡናን በአፍሪካ ነጻ የንግድ ቀጣና ሥርዓት እንዲገበያዩ የሚያደርግ ወሳኝ ምዕራፍ መሆኑን ይገልጻሉ፡፡

አምባሳደሯ ፤ ግብዓቶችን ማሰባሰብ፣ በኢንዱስትሪዎች ትኩረት አድርጎ መሥራት፣ እሴት የተጨመረበት ቡና ለገበያ ማቅረብና ከዚህ ቀደም ያሉ አሠራሮችን መቀየር ይኖርብናል ሲሉ ይናገራሉ፡፡

የአፍሪካ ቡና አብቃይ ሀገራት ድርጅት ዋና ጸሃፊ አምባሳደር ሰለሞን ሩተጋ እንደሚሉት ፤ የውሳኔው ዋና ራዕይ የአፍሪካን የቡና ዘርፍ እሴት በመጨመር ወደ ላቀ ስኬት ማሸጋገር ነው። በዓለም ዙሪያ ውሳኔውን ተግባራዊ ለማድረግም የዲፕሎማሲ ሥራው ወሳኝ በመሆኑ እሱ ላይ ትኩረት ሊደረግ ይገባል ይላሉ፡፡

በዓለም ላይ በትልቅነቱ ሁለተኛ ደረጃ የያዘው የቡና ምርት የሚገባውን ያህል ትኩረት እንዳላገኘ የሚናገሩት ዋና ጸሃፊው በአሁኑ ጊዜም እንደ ሞሮኮ እና አልጄሪያ ያሉ ሀገራት ወደ ድርጅቱ እንዲቀላቀሉ ማድረግ ተችሏል፡፡ ይህም የኢትዮጵያ ቡና በአፍሪካ ነጻ የንግድ ቀጣና በኩል እንዲገበያዩ የሚያደርግ ነው ብለዋል፡፡

የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር አቶ አዱኛ ደበላ (ዶ/ር) እንደተናገሩት፤ የአፍሪካ ህብረት ቡናን እንደ ስትራቴጂካዊ ምርት መውሰዱ የአፍሪካ ሀገራት በቡና ላይ እንዲሁም በገበያው ላይ አንድ አቋም እንዲይዙ ያስችላል።

ከ13 በመቶ በላይ የአፍሪካ ሀገራት ቡናን ሲያስገቡ አህጉሪቱ ደግሞ 12 በመቶ ምርቱን ለዓለም ገበያ እያበረከተች ነው የሚሉት ዶ/ር አዱኛ ቡናን ወደ አፍሪካ ገበያ መላክ አምራቾችን ብቻ ሳይሆን ሌላውን የህብረተሰብ ክፍል በተለያየ መንገድ ተጠቃሚ እንደሚያደርግ ይገልጻሉ።

# ማሻሻያውና የጥቁር ገበያው...

ከ 1ኛ ገፅ የዞረ

ለመለካት አስቸጋሪ እንደሆነም አመላክቷል፡፡

በሌላ በኩል ጥቁር ገበያ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴን ከመደበኛው እና ታክስ ከሚከፈልበት ኢኮኖሚ በማራቅ የመንግሥትን ገቢ ያዳክማል ይላል፡፡

የውጭ ምንዛሪ ሁኔታን በተመለከተ፣ በሕጋዊ መስመር ሊወጣና ታክስ ሊከፈልበት የሚችል ከፍተኛ መጠን ያለው የውጭ ምንዛሪ እንደሚገበያይና ይህ የገቢ መጥፋት የመንግሥት እና የሕዝብ አገልግሎቶችን እንዲሁም መሠረተ ልማትን ለመደገፍ እንቅፋት እንደሚፈጥር ይጠቅሳል፡፡

ከዚህም ባሻገር የጥቁር ገበያ ሰው ሠራሽ እጥረትን በመፍጠር እና የዋጋ ንረት በመጨመር የኑሮ ውድነትን ሊያባብስ እንደሚችል መረጃው ይዳስሳል፡፡

ሆኖም ጥብቅ ደንቦችን በማክበር እና የገንዘብ ልውውጥን በመከታተል መንግሥታት ሕገወጥ የገንዘብ ልውውጥን መቆጣጠር እንደሚችሉ ያነሳው መረጃው፤ ይህ በናይጄሪያ በግልጽ መታየቱን ለአብነት ይጠቁማል፡፡

በሀገሪቱ የማዕከላዊ ባንክ የጥቁር ገበያ ግብይትን ለመግታት የተወሰደው ርምጃ፣ ከመደበኛው የምንዛሪ ተመን ሥርዓት ማሻሻያ ጋር ተዳምሮ የጥቁር ገበያ እንቅስቃሴን በከፍተኛ ሁኔታ እንዲቀንስ ማድረጉን ይጠቅሳል፡፡

የፐብሊክ ፖሊሲና ምጣኔ ሀብት ምሁሩ ዶክተር ቆስጠንጢኖስ በርኸተስፋም እንደሚሉት፤ በቅርቡ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ይፋ ያደረገው የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ሥርዓት ማሻሻያው ጥቁር ገበያን የሚያዳክም መሆኑን እና ለዘለቄታውም ሊያጠፋው እንደሚችል ይናገራሉ፡፡

የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ሥርዓቱ የውጭ ምንዛሪ ተመን በባንኮችና በደንበኞቻቸው መካከል ወደሚወሰንበት የገበያ ሥርዓት መሸጋገሩና ሰዎች ዶላርን ቀጥታ በባንክ የሚመነዝሩበት አግባብ መኖሩ፤ ይህም ከጥቁር ገበያው በተለየ አስተማማኝ መሆኑ ጥቁር ገበያን የሚያዳክም ነው የሚሉት የምጣኔ ሀብት ባለሙያው፤ ይህ ዳግም የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ለማጠናከር ከፍተኛ ሚና አለው ሲሉ ነው የሚገልጹት፡፡

እስካሁን ሰዎች ወደ ጥቁር ገበያ የሚሄዱት ባንክ ውስጥ ገንዘብ በማጣታቸው እንደነበር ጠቅሰው፤ የምንዛሬ ሕግ ቢወጣም ባንኮች ብዙ ዶላር መሰብሰብ አልቻሉም ነበር፡፡ አሁን ግን ባንኮች በከፍተኛ ደረጃ ምንዛሪ የሚያሳድጉበት ደረጃ ላይ ናቸው ሲሉ ያስረዳሉ፡፡

ይፋ በተደረገው እና ወደሥራ በገባው ማሻሻያ መሠረት ከዳያስፖራው የሚመጣውን ገንዘብ የትም ባንክ በመሄድ መመንዘር እንደሚቻል በመጥቀስ፤ ባንኮች በቂ ዶላር ሲኖራቸውና የውጭ ምንዛሪ አገልግሎትን በሙሉ አቅም መስጠት ሲጀምሩ ሰዎች ወደ ጥቁር ገበያ አይሄዱም ይላሉ፡፡ በዚህ መንገድም ጥቁር ገበያው ይዳከምና ይጠፋል ሲሉ ያስረዳሉ፡፡

ለዚህም እንደ ኬንያ፣ ዩጋንዳና ታንዛኒያ ያሉ ሀገራት ማሳያ መሆናቸውን አንስተው፤ በእነዚህ ሀገራት ይህ አይነት ፖሊሲ ተግባራዊ በመደረጉ ጥቁር ገበያ የሚባል ነገር አለመኖሩን በማሳያነት ያስቀምጣሉ።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የግል የውጭ ምንዛሪ ቢሮዎችን ለመክፈት የሥራ ፈቃድ ማመልከቻዎችን መቀበል መጀመሩም ለጥቁር ገበያው መጥፋት ወሳኝ ሚና ካላቸው ጉዳዮች አንዱ እንደሆነ በመጥቀስ፤ በዚህ መልኩ የምንዛሪ ተደራሽነት መስፋት ጥቁር ገበያውን እንደሚያጠፋው ነው የሚናገሩት፡፡

የጥቁር ገበያው መጥፋት፣ መደበኛ ባልሆነው የምንዛሪ ዋጋ ምክንያት የሚፈጠሩ የሰው ሠራሽ የዋጋ ግፊቶች ተወግደው የዋጋ ንረትን ለመቆጣጠር እንደሚያግዝ በመጥቀስ፤ ይበልጥ የተረጋጋ ምንዛሪ ከውጭ ለሚገቡ እቃዎች ዋጋ እንዲቀንስ ሊያደርግ እንደሚችል፤ ይህም ሸማቾችን እና የንግድ ድርጅቶችን እንደሚጠቅም ያነሳሉ፡፡

የኮንትሮባንድ ንግድ የሚስፋፋው በጥቁር ገበያ አማካኝነት በመሆኑ፤ ኢትዮጵያ ገበያ መር ወደሆነው የውጭ ምንዛሪ ሥርዓት መሸጋገሯ ይበጃታል ሲሉ ይመክራሉ፡፡ ጥቁር ገበያው ሲጠፋ የኮንትሮባንድ ንግዱም በዛው እንደሚዳከም ጠቁመዋል፡፡

በትክክለኛ የቁጥጥር ርምጃዎች በመታገዝ፣ ጥቁር ገበያን በውጤታማነት ማፍረስ እንደምትችል፤ ይህ ሽግግር ኢኮኖሚውን ከማረጋጋት ባለፈም ሥራው ሕጋዊነት ላይ የተመሠረተ በመሆኑ የመንግሥትን ገቢ እንደሚያሳድግ፤ በፋይናንሺያል ተቋማት ላይ መተማመንን እንደሚያድስ፣ የውጭ ኢንቨስትመንትን በመሳብ ለዘላቂ የኢኮኖሚ ልማት መሠረት እንደሚጥል እና ወጣቶችንም ወደ ፋይናንሺያል ቴክኖሎጂ እንደሚስብ ነው ዶክተር ቆስጠንጢኖስ ያስገነዘቡት፡፡

የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ምክትል ገዥ አቶ ፍቃዱ ድጋፌ በበኩላቸው፤ የትይዩ ገበያ በመደበኛው ገበያዎች ለሚጠየቀው ጥያቄ በቂ ምላሽ ሳይሰጡ ሲቀር የሚፈጠር እንደሆነ ያስገነዝባሉ፡፡

በኢትዮጵያ የውጭ ምንዛሪ ትይዩ ገበያ የተፈጠረው በዚህ የተነሳ መሆኑን በመጠቆም፤ በተለይ መደበኛ ገበያው ከማሻሻያው በፊት የነበረው በገበያ ተመን ሳይሆን በውሳኔ በመሆኑ በትይዩ ገበያው ውስጥ ብልጫ መወሰዱን ያብራራሉ፡፡

በማሻሻያው መሠረት አቅርቦትን ያገናዘበ የዋጋ ተመን ሲደረግ ከትይዩ ገበያ ጋር የመቀራረብ እድል እንደሚፈጥር ጠቅሰው፤ ይህም የጥቁር ገበያውን ዋጋ እያሳነሰ እንደሚመጣ ተናግረዋል፡፡

የግል የውጭ ምንዛሪ ቢሮዎች መከፈትም ጥቁር ገበያውን እንደሚያዳክመው እና ይህም ዘላቂነት ላለው የኢኮኖሚ ግንባታ ትልቅ ፋይዳ ያለው መሆኑን አመላክተዋል፡፡

# ታዳጊ የቀለም...

ከ 1ኛ ገፅ የዞረ

ተርታ ቀዳሚ ተሰላፊዎች ናቸው። እነሆ አርዓያዎች ናቸው እና ልምዳቸውን እንጋራው።

ተማሪ ሱራፌል አያና ከአቡነ ጎርጎሪዎስ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በቅርቡ በተካሄደው የስምንተኛ ክፍል ከተማ አቀፍ ፈተና 99 ነጥብ ዘጠኝ ፐርሰንታይል በማግኘት ወደ ዘጠነኛ ክፍል ተዘዋውሯል። ይህ ወደር የለሽ ስኬት ተማሪውን በአዲስ አበባ ከፍተኛ ውጤት ካመጡ ተማሪዎች ተርታ አሰልፎታል።

የሱራፌል ቁርጠኛነት፣ የማንበብ ልምድ፣ በፕሮግራም መመራት እና በፈተና ሰዓት መደረግ ያለበትን ጥንቃቄ ማድረጉ የውጤቱ ምስክሮች መሆናቸውን ይናገራል። ሱራፌል ለስምንተኛ ክፍል ከተማ አቀፍ ፈተና ከ2015 ዓ.ም ሐምሌ ወር ጀምሮ ዝግጅት ሲያደርግ መቆየቱን ተናግሯል።

ይህም ለውጤታማነቱ አንዱ ምክንያት መሆኑን ገልጾ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች ፈተና ሲደርስ የማጥናት እና የመደናገጥ ባህሪ እንደሚታይባቸው ተናግሯል። ውጤታማ ለመሆን እለት ተእለት ማንበብ እና እውቀትን ማሳደግ እንደሚገባም ይናገራል።

የራሱ የሆነ የአጠናን ሥርዓት እንዳለው የሚናገረው ተማሪ ሱራፌል፤ ይህም የመማሪያ መጽሐፉን በጥልቀት ማንበቡን መሆኑን ነው የተናገረው። ይህም የስምንተኛ ክፍል ከተማ አቀፍ ፈተናው ጥሩ እንዲሆን ማድረጉን ይገልጻል።

ተማሪዎች የመማሪያ መጽሐፍ ላይ ያለውን ዓላማ መሠረት ያደረገ ጥናት እንዲያደርጉ መክሯል። አያይዞም በመማሪያ መጽሐፉ ላይ ያለውን ሁሉንም ጥያቄዎች በተገቢው መልኩ መመለስ እንደሚገባ የገለጸ ሲሆን ይህም የተሻለ ውጤት ለማምጣት እንደሚያስችል ተናግሯል።

ስለፈተናው ተማሪዎችና ሰዎች ሲያወሩ ጭንቀት የተሞላበት ቢሆንም ፈተናው ላይ ላለመደንገጥ የሥነ ልቦና ዝግጅት ማድረጉን ገልጾ ፈተናው ቀላል እና የመማሪያ መጽሀፉን መሠረት ያደረገ መሆኑን ተናግሯል። ለዚህም የተጣራ እቅድ ሊኖር እንደሚገባ እና ከፈጣሪ ጋር ጠንክሮ መሥራት ውጤቱን ወርቃማ እንደሚያደርገው ገልጿል።

በቀጣይ የ12ኛ ክፍል ማትሪክ ፈተና እንደሚጠብቀው እና ፈተናው ከዘጠነኛ ክፍል ጀምሮ ያለውን ትምህርት እንደሚያጠቃልል ገልጾ ለፈተናው ከአሁኑ ዝግጅት በማድረግ የተሻለ ውጤት ለማምጣት ጥረት እንደሚያደርግ እና ወደፊት የጠፈር ተመራማሪ ለመሆን የተፈጥሮ ሳይንስ ትምህርቶችን እንደሚከታተል ተናግሯል።

የጀነራል ዋቆ ጉቱ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ቁጥር ሁለት ተማሪ የሆነው ሞቲ ተሾመ በበኩሉ፤ ለስምንተኛ ክፍል ሚኒስትሪ ፈተና መምህራን የሚያስተምሩትን ትምህርት በመቅደም ጥናት የሚያከናውን ሲሆን ይህም በሚኒስትሪ ፈተና የተሻለ ውጤት እንዲያመጣ እንደረዳው ገልጿል።

ፈተና ሲደርስ ተማሪዎች ሲረበሹ እንደነበር ገልጾ ከመረበሽ ይልቅ ሃሳብን በመሰብሰብ በትኩረት ማንበብ ይገባል ሲልም ተናግሯል። ተማሪ ሞቲ ከተማሪዎች ጋር መልካም ግንኙነት እንዳለው ገልጾ ተማሪዎች ከሶሻል ሚዲያ ራሳቸውን በመጠበቅ ሁሌም ውጤታማ ለመሆኑ ሊሠሩ እንደሚገባ ተናግሯል።

"ተማሪ ኦብሲኔት ለማ"ም ልክ እንደተማሪ ሱራፌል እና እንደተማሪ ሞቲ የስምንተኛ ክፍል ከተማ አቀፍ ፈተና 99 ነጥብ ዘጠኝ ፐርሰንታይል በማግኘት ወደ ዘጠነኛ ክፍል ተዘዋውራለች። የተማሪ ኦብሲኔት አባት ለማ መገርሳ እንደሚሉት፤ የልጆች የመጀመሪያው ትምህርት ቤት ቤተሰብ መሆኑን ገልጸዋል።

ተማሪ ኦብሲኔት በትምህርቷ ውጤታማ እንድትሆን ከልጅነቷ ጀምሮ ሲያስጠኗት እንደነበር የገለጹት አቶ ለማ፤ የወላጆች ሚና ለልጆች ውጤታማነት ጉልህ ሚና ያለው በመሆኑ ወላጆች ልጆቻቸውን ከታች ጀምረው ትምህርታቸው ላይ እንዲጠነከሩ አቅጣጫ ማሳየት እንደሚገባ ተናግረዋል።

ተማሪ ኦብሲኔት በበኩሏ፤ አዳሪ ትምህርት የመማር ፍላጎት ያላት ሲሆን ይህ እውን እንዲሆን የስምንተኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፉን ትምህርት ሳትጀምር ቀድማ ማንበብ እንደጀመረች ተናግራለች። ከዚህም ባለፈ ለራሷ የሚመቻትን የጥናት ስልት ማዘጋጀቷን ገልጻለች።

በቁርጠኝነት ማንኛውም ግብ ሊደረስበት የሚችል መሆኑን የምትናገረው ተማሪ ኦብሲኔት፤ በ2017 ዓ.ም የስምንተኛ ክፍል ከተማ አቀፍ ፈተና ላይ ለሚቀመጡ ተማሪዎች መልካም እድል ተመኝታለች።

ኢኮኖሚ

# ግብርና

# ግብርናው ቴክኖሎጂን አሟጦ መጠቀምና ገበያ ማፈላለግን ይጠይቃል

በኃይሉ አበራ

በግብርናው ዘርፍ በተከናወኑ ተግባሮች ምርትና ምርታማነት በየአመቱ እያደገ ይገኛል፡፡ ይህ እድገት ግን ካለው እምቅ አቅምና ሀገሪቱ ከምትፈልገው የግብርና ምርት አኳያ ሲታይ አሁንም ምርትና ምርታማነቱ ማደግ እንዳለበት ይታመናል፡፡

በሀገሪቱ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥና የግብርና ምርቶችን ለውጭ ገበያ ለማቅረብ በሚደረገው ጥረት የግብርና ምርትና ምርታማነት ማሳደግ የኢትዮጵያ መንግሥት የምንጊዜም ሥራ ሆኖ ቀጥሏል፡፡ ግብርና አሁንም በሀገሪቱ ኢኮኖሚ ውስጥ ሰፊውን ድርሻ የያዘ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ለቀጣዩ የኢንዱስትሪም ሆነ ሌሎች ልማቶች አንዱ አቅም የሚገኘው ከዚሁ ከግብርናው ዘርፍ ነው፡፡ ለእዚህም ነው በዘርፉ ኩታ ገጠም እርሻን፣ ሜካናይዜሽንን፣ የበጋ መስኖ ልማትን ፣ ወዘተ ለማስፋፋት በትኩረት እየተሠራ ያለው፡፡

ሰሞኑን የግብርና ኢኮኖሚ ባለሙያዎች ማህበር ባዘጋጀው የፓናል ውይይት ላይ በዘርፉ ጥናታዊ ጽሁፎቻቸውን ያቀረቡት የግብርና ኢኮኖሚ ባለሙያዎች እና ተመራማሪዎች እንዳስታወቁትም፤ የግብርናውን ዘርፍ ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ እንዲያስችሉ ሥራ ላይ በዋሉት እንደ ኩታ ገጠም እርሻ፣ ሜካናይዜሽን ፣ወዘተ ባሉት ለውጦችን ማስመዝገብ እየታቸለ ነው፤ የበለጠ ለውጥ ለማስመዝገብ ግን አሁን በትኩረት መሥራት ያስፈልጋል፡፡

በግብርናው ዘርፍ የግል ዘርፍ አማካሪ የሆኑት ዶክተር ደምስ ጫንያለው ፤ ግብርናው በተለይ በእርሻው አካባቢ ለውጦች እንደሚታዩ ጠቅሰው፣ ለውጡ የምንፈለገውን ያህል አይደለም ይላሉ። ይህም የሆነው ከታች ከመሬት ጉዳይ ጀምሮ ከዘር፣ ማዳበሪያ አቅርቦት በተለይ ከስርጭት ጋር የተያያዙ ችግሮች እንደሚስተዋሉ ጠቁመዋል።

ዶክተር ደምስ እንዳሉት፤ ኩታገጠም እርሻዎች ላይ ያለው ለውጥ በጣም ትልቅ ነው። ከሶስት አራት ዓመታት በፊት የነበረው ዜሮ ነጥብ ስድስት ሄክታር በኩታገጠም ይታረስ የነበረው መሬት አሁን ስምንት ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ሄክታር ደርሷል። ምርማነቱም ጥሩ ነው።

የተገኘውን ምርት ወደ ሸማቹ ወይም ገበያ ለማድረስ ከመጋዘን አቅርቦት፣ ከማጓጓዝ ጀምሮ ችግሮች ስለመኖራቸው በስፋት እንደሚሰማም ጠቁመዋል። ምርታማነቱ ዘላቂነት እንዲኖረው ለማድረግ ምርቱ ጥሩ ዋጋ ማግኘት አለበት ይላሉ፡፡ ከዚህ አኳያ ጥሩ ለውጥ እንዳለም ጠቅሰው፣ ተያይዘው የተከሰቱ ችግሮች መኖራቸውን አመላክተዋል።

አማካሪው እንደገለፁት፤ በግብርናው ዘርፍ ከማምረት፣ የማምረቻ መሬት ከማስፋት፣ ከመጠቀም እና ምርታማነትን ከመጨመር በእያንዳንዱ አካባቢ በጥራት ከማቅረብ አንፃር ሥራዎች ተሠርተዋል። ይሁንና አርሶ አደሩ በኢንተርፕሩነርሺፕ ራሱን አሻሽሎ በምርታማነት ማደግ የሚያስፈልገውን ከማግኘት አንፃር ገና ብዙ መሰራት ይኖርበታል፡፡

እስካሁንም በግብርናው በተለይ በእርሻው ክፍል ውስጥ የመዋቅር ለውጥ ለማምጣት የተጀመረ ሥራ የለም ሲሉም ጠቅሰው፣ ይህን አንቆ የያዘው አንደኛው የመሬት ጉዳይ ነው ብለዋል። አሁንም ቢሆን በቅርቡ ማሻሻያ አድርገናል፤ ብዙ መሥራት ግን ይኖርብናል። መሬትን ወደ ግል ከመቀየር ውጪ ግን በማሰባሰብ ሊያድጉ የሚችሉ ገበሬዎች ከእርሻው ውስጥ እንዳይወጡ ማድረግ መቻል አለብን ሲሉም አስገንዝበዋል።

ሁለት ሄክታር ይዞ ጥሩ አፕል ሲያመርት የነበረ አንድ ገበሬ፣ ከሁለት ሄክታር ያገኘውን ገንዘብ ይዞ ከተማ ገብቶ ቤት ወይም ወፍጮ ለመሥራት ከመሄድ ይልቅ እዛው ሆኖ እርሻውን የሚያስፋፋበትን መንገድ መፍጠር እንደሚገባም ጠቁመዋል፡፡ ዘለቄታዊ ለውጥ ለማምጣት የዚህ አይነት የስትራቴጂ አስተሳሰብ ያለው አሠራር መቅረጽ እንደሚገባም ነው ያመለከቱት።

በስንዴው የጀመርነውን በሌላውም በተመሳሳይ መስራት አለብን ሲሉም ጠቁመው፣ የተፈጥሮ ሀብት በበቂ ያለን በመሆኑ በዚህ ላይ መሥራት አለብን ሲሉ አማካሪው ገልጸዋል።



ዶክተር እንዳሻው ሀብቴ

የግብርና ኢኮኖሚክስ ባለሙያና ተመራማሪ ዶክተር ዳዊት ዓለሙ በበኩላቸው እንደሚገልፁት የግብርና ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ጥራት ያለው የግብርና ግብዓት ያስፈልጋል። ለምግብ አምራቾች እንዲሁም ለውጭ ገበያው የሚላከውን ጥራት ያለው ምርት ለማምረት የሚያስችል የግብርና ግብዓት ያስፈልጋል። ከዚህ ውስጥ ትልቁ የዘር ሥርዓት፣ የማዳበሪያ አቅርቦት እና ኬሚካል አቅርቦት ጉልህ ድርሻ አላቸው። ከዚህ በተጨማሪም ችሎታ ያላቸው የሰው ኃይል እንዲሁም የግብርና ማሽነሪዎችም ወሳኝ ናቸው። ሌሎችም መሰል ግብዓቶች አሉ።


የግብርና ግብዓች እንደየግብዓቱ ዓይነት የራሳቸው ጥንካሬ እና ደካማ ጎን አላቸው። የዘር ሥርዓቱ ብዙ የግል ሀብቶች የሚሳተፉበት ቢሆንም ብዙ በመንግሥት ድርጅቶች የሚመራ ነው። ይሄም ብዙውን ወደተወሰኑ ሰብሎች ላይ ያተኮረ ነው። ወደ 80 በመቶ የተረጋገጠ ዘር የሚመረተው ለስንዴ እና ለበቆሎ ነው። ለስንዴም ለበቆሎም ሆኖ ለጥቂት ዝርያዎች ነው። ሀገር ውስጥ ከሚመረቱት አኳያ አዳዲስ ዝርያዎች ወደ ምርት አይገቡም። በሥራ ላይ ያሉት ዝርያዎች አማካኝ እድሜያቸው ወደ 15 ዓመት ይሆናል፤ ነገር ግን መሆን ያለበት በ 15 ዓመቱ አዳዲስ ዝርያዎች እየተኩ እንዲሄዱ ነው።

ለዚህም ዋናው ችግሩ መነሻው ጠንካራ የሆነ የአስተዳደር ሥርዓት የለንም በየጊዜው መንግሥታት በተቀያየሩ ቁጥር የአስተዳደር ሥርዓቱ ይቀያየራል። ያ ደግሞ የነበሩ ደካማና ጠንካራ ጎኖችን አይቶ ለማሻሻል የሚያስችለውን አሠራር ለመተግበር ትልቅ ችግር ያለ በመሆኑ በዚህ ላይ አተኩሮ መሥራት ያስፈልጋል።

አሁን መስከረም ላይ የፀደቀው አዲሱ የዘር አዋጅ ከላይ የተገለጹትን ችግሮች ይፈታል ተብሎ ይጠበቃል። ከዚህ ጋር ተያይዞም አዳዲስ መመሪያዎችና ደንቦች ማውጣት የሚጠበቅ መሆኑንም አስታውቀዋል።

የአትክልት ዘርን በተመለከተ ፕሬዚደንቱ እንደገለፁት በጣም ወሳኝ በሆነ ደረጃ ከውጭ ጥገኛ ነን። ይህም የዘር ሉዓላዊነት ችግርን ያመጣል። የዛሬ ሶስት ዓመት ህንድ የሽኩርት ዘርን ጨምሮ የተለያዩ የአትክልት ዘር ወደ ውጭ መላክን ስትከለክል የዘር አቅርቦት በጣም ችግር ውስጥ ገባ። በመሆኑም አሁን የአትክልቶች የዘር ሥርዓት በቅመማቅመም ማስፋት ያስፈልጋል። ለእንደዚህ ዓይነት ሰብሎች ላይ ትኩረት አድርጎ መሥራት ያስፈልጋል። ይህ በአጠቃላይ የመንግሥት እና የግል ተሳታፊዎችን ሚና ለይቶ ማን ምን ይደግፍ የሚለው ታይቶ ወደ ሥራ መግባት ያስፈልጋል።

የአግሮ ኬሚካል ግብይትን በመተለከተ የአሠራር ሥርዓት እና ሕጎች አሉ ያንንን የማስፈፀም ተገቢ ነው ሲሉም ነገር ግን ትልቁ ችግር አሁን ያለው የአግሮኬሚካል ግብይት ሁሉም አርሶአደር ስለበሽታውም ሆነ ስለኬሚካሉ እውቀት አለው ብሎ ያስባል። ነገር ግን በሚጠበቀው ልክ ላይሆን ይችላል። በመሆኑም በእውቀት ላይ የተመረኮዘ አጠቃቀም እንዲኖር የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት ያስፈልጋል። ይሄም ወደ አገልግሎት አቅርቦት የመሄድ የተማሩ ሰዎች ወደዛ ቢዝነስ የሚገቡበት እና በሽታውን ለይተው የትኛው ኬሚካል መቼ ይረጭ፣ ምን ያህል ይረጭ የሚለውን ሁሉ የሚለዩ መሆን አለባቸው። ምክንያቱም ሀገር ውስጥ ለምንመገበው ብቻ ሳይሆን ወደ ውጭ ለሚላከውም የኬሚካል አቅርቦቱ ወሳኝ በመሆኑ ወደ ቢዝነስ መር አገልግሎት መውሰድ የግድ መሆኑን አመላክተዋል።



ዶክተር ደምስ ጫንያለው

**ሁለት ሄክታር ይዞ ጥሩ አፕል ሲያመርት የነበረ አንድ ገበሬ፣ ከሁለት ሄክታር ያገኘውን ገንዘብ ይዞ ከተማ ገብቶ ቤት ወይም ወፍጮ ለመሥራት ከመሄድ ይልቅ እዛው ሆኖ እርሻውን የሚያስፋፋበትን መንገድ መፍጠር እንደሚገባም ጠቁመዋል**

የኬሚካል ማዳበሪያ አስመልክተው ፕሬዚደንቱ ሲገልጹም ሙሉ በሙሉ ከውጭ የሚመጣ ነው። አንዳንድ ካምፓኒዎች ፍቃድ ወሰዱ ይሄንን ያህል ኢንቨስት አደረጉ ሲባል ይደመጣል። አሁን የድሬዳዋውን የማዳበሪያ ኩባንያ በ2023 የተፈራረሙ ቢሆንም እስካሁን ምንም አልታየም ነገር ግን አንደኛው የሀገር ውስጥ ምርት የሚመረትበትን ማመቻቸት ነው። ሁለተኛው ግን አሁን ወደ ሀገር ውስጥ ስናስገባ ብቁ እንድንሆን የሚያደርግ ነው። ዓለምአቀፍ መስፈርት ለማሟላት እና አቅም የመገንባት ሥራ ነው። በመሆኑም በዚህ ደረጃ አቅም መፍጠር ተገቢ መሆኑን ተናግረዋል።

ከ 400 በላይ ኬሚካሎች በምርምር ተጠንተው ውጤታማነታቸው ተመዝግበዋል። በዚህ ዓመትም በሚቀጥለው ዓመትም ወደ ሀገር ውስጥ ይገባል። ውጤታማነቱም ምርምሩ ላይ የተሞከረው ይሁን አይሁን የሚፈተሽበት የለም ደረጃውን ብቻ ነው የምናየው። በመሆኑም ይሄንን አቅም ማሳደግ ያስፈልጋል። ይህም የራሱ ትልቅ ክፍተት የሚፈጥር ነው።

በመሆኑም ግብርና ኬሚካል ላይ የሚቆጣጠረው የተፈለገው ደረጃ መኖሩን ብቻ ነው። በመሆኑም በብዙ ግፊት የተደረገው እና የኢትዮጵያ ግብርና ባለሥልጣን እንዲቋቋም የተደረገው በኬሚካልም በዘርም የቁጥጥር አቅም በራሱ ችሎ መሰራት አለበት። ነገር ግን ያ አቅም ስለመፈጠሩ እና አለመፈጠሩ ወደ ፊት በጋራ የሚታይ መሆኑን አመላክተዋል።

የመሣሪያዎች አቅርቦቱም በተመሳሳይ ሙያዊ በሆነ መልኩ የሚመራበት መንገድ መፈጠር አለበት፤ የዓለም አቀፍ የማዳበሪያ ንግድ ዓለም አቀፍ ፖለቲካ አለበት፣ ግፊት አለበት። በመሆኑም ይሄንን ግንዛቤ ውስጥ ያስገባ አቅም መፍጠር ያስፈልገናል። በባለሙያ ብቻ ሳይሆን በብዙ ተዋናዮች ሊሠራ የሚገባው ነው ነገር ግን ይህም ሆኖ ከገባ በኋላ በቂ ሥርጭት ያስፈልገዋል።

መንግሥት ከወደብ ወደ ማዕከላዊ መጋዘን አስገብቶ ከዚያም ወደ ማዕከላት በማስገባት የሚያሰራጨው ሁኔታ የተሻለ ውጤታማ አሠራር ነው። አሁን ግን ይህ አሠራር እየተዳከመ ስርጭቱም ወደ አልተገባ የንግድ ጥቅም እየገባ መሆኑን ጠቁመዋል።

‹‹ገበያ ማለት የሚገዛ ኃይል ማለት ነው። ሁልጊዜ የሚገዛው ኃይል የሚያመርተውን ኃይል ይመራዋል።›› የሚሉት የኢትዮጵያ ኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማህበር ፕሬዚደንት ዶክተር እንደሻው ሀብቴ፣ ምርት መመረቱ ብቻ በራሱ በቂ አይሆንም፤ ምክንያቱም ስርጭት መታየት መቻል አለበት ሲሉ ይገልጻሉ።

እሳቸው እንዳስታወቁት፤ ስርጭት ደግሞ ከገበያው ጋር ይገናኛል። ከአቅርቦት ጋር ይገናኛል፤ መንገድ፣ የገበያ መረጃ ሥርዓት መኖር አለባቸው። ሰዎች ምርት የት እንደ ተመረተ፣ መቼ እንደሚመረት፣ አምራቹም ደግሞ ገበያው የት እንዳለ ማወቅ መቻል አለባቸው፡፡

እነዚህን በሚገባ ሥርዓት ማስያዝ ከተቻለ፣ ቢያንስ አሁን ያለውን የምግብ ሥርዓት ማስያዝ ቢቻል፣ ቢያንስ አሁን ያለውን የምግብ እጥረት ሙሉ ለሙሉ መቅረፍ ባይቻል ትርጉም ባለው ደረጃ ለውጥ ማምጣት ይቻላል ተብሎ የሚታመን መሆኑን ገልፀዋል።

በሀገራችን ካሉ ለውጦች አንፃርም ዝግጁነቱ መኖር እንዳለበት ያስረዳሉ። ለምሳሌ የሕዝብ ቁጥር ሲጨምር ተያይዞ የምግብ ፍላጎትም በተመሳሳይ ያድጋል ሲሉም የማህበሩ ፕሬዚዳንት ጠቁመው፤ ከዚህ ጋር ተያይዞ ዝግጁነት መኖር እንዳለበትም አፅንኦት ሰጥተው ተናግረዋል።

ግብርናውን ከዘመናዊ ቴክኖሎጂዎች ጋር አያይዘው ሲገልጹም የካፒታል አቅርቦት መኖር እንዳለበት አስገንዝበዋል። የማህበሩ ፕሬዚዳንት አምራቹ ኃይል በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ መደራጀት መቻል አለበት ሲሉም አመልክተዋል።

ከገበያም ሆነ ከምርት አኳያ እንደ ህብረት ሥራ ማህበራት ያሉትን፣ በተለይ የኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩትን ኩታገጠም እርሻ ተብሎ የተጀመረው ትልቅ ተነሳሽነት መኖራቸውን በአዎንታዊነት ጠቅሰዋል። ይህም በበሬ እና በሰው ኃይል ከማረስ ቴክኖሎጂን፣ ትራክተሮችን የመሳሰሉትን ለመጠቀም እና ለሌሎች የተቀናጀ ሥራዎች አስቻይ ሁኔታዎችን እንደሚፈጥር ገልጸዋል።

ዶክተር እንዳሻው እንዳብራሩት፤ ከመሬት፣ ከእውቀት፣ ከቴክኖሎጂ አቅርቦት ጋር ተያይዞ ያሉትን ሁኔታዎች ማሻሻል ከተቻለ ገበያው ይሄንን ማቀላጠፍ ይችላል። ዘመናዊ ቴክኖሎጂም ለመጠቀም አርሶአደሩም የተሻለ እድል ይኖረዋል። ገበያ ሲባል የብድር አገልግሎትንም ጨምሮ ሰዎች ገንዘብ ሲፈልጉ መበደር መቻልም አለባቸው። ያንንም የሚያቀርብ ገበያ መኖር አለበት።

የኤክስቴንሽን አገልግሎቱም እውቀትን በአግባቡ ማቅረብ አለበት ሲሉም ጠቅሰው፣ የዘር ስርጭቱም ወይም ሌሎች የሜካናይዜሽን ሥራዎች በአግባቡ ተደራሽ መሆን እንዳለባቸው አስታውቀዋል።

ማህበራዊ

# አስኳላ

# የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ትስስር

**ብርሃን ፈይሳ**

የትምህርት አንዱ አላማ በዕውቀት የታነጸና ብቁ የሆነ አምራች ዜጋን በማፍራት ወደ ሥራ ዓለም መቀላቀል ነው። ለዚህ ደግሞ የትምህርት ተቋማት በሥራቸው ላሉ ተማሪዎችና ሰልጣኞች የሚሰጧቸው የንድፈ ሃሳብ ዕውቀቶች ብቻቸውን በቂ ባለመሆናቸው ከሥራ በፊት የተግባር ልምምድ አስፈላጊ ይሆናል። በዚህ ረገድ የነበረው የልምድና የእውቀት ሽግግር የአንድ ወገን ማለትም ተማሪዎች በወረቀት ሲማሩት የነበረውን በሥራ ላይ ካሉት በተግባር የሚቀስሙበት አካሄድ ብቻ ነበር። በትምህርት ተቋማትና በኢንዱስትሪዎች ወይም ሌሎች የሥራ ቦታዎች ሊኖር የሚችለው የዕውቀት ሽግግር ግን የበለጠ ውጤታማ የሚያደርግ ይሆናል።

የከፍተኛ ትምህርትና ሌሎች ተቋማት ትስስርም ይህንን እውን ለማድረግ የተጀመረ ቅንጅት ነው። ይህም ትስስር ተማሪዎችን ከማብቃት ባለፈ የትምህርት ተቋማቱንና ራሳቸው ኢንዱስትሪዎቹንም ተጠቃሚ የሚያደርግም ነው። ይህ ትስስር ለኢትዮጵያ አዲስ ቢሆንም በአውሮፓና የሩቅ ምስራቅ ሀገራት ብዙ ተሰርቶበት አበረታች ውጤት የተመዘገበበትም ነው። በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ይህንን ትስሰር በተቻለ አቅም በመተግበር እያስመዘገቡ ካሉ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት መካከል የሰላሌ ዩኒቨርሲቲ ይጠቀሳል።

ከአራተኛ ትውልድ ዩኒቨርሲቲዎች መካከል አንዱ የሆነው የሰላሌ ዩኒቨርሲቲ ከተመሰረተ 7 ዓመታትን ያስቆጠረው ሲሆን፤ የተሰጠውን የመማር ማስተማር፣ የጥናትና ምርምር እንዲሁም የህብረተሰብ አገልግሎት ሥራ እየተገበረ ይገኛል። በሶስት ኮሌጆች በ9 የመጀመሪያ ዲግሪ መርሃ ግብር የተቋቋመው ዩኒቨርሲቲው በዚህ ወቅት የመማር ማስተማር ሂደቱን በማስፋፋት በ6 ኮሌጆች እና አንድ ትምህርት ቤት ውስጥ በ33 የመጀመሪያ ዲግሪ እና 41 ሁለተኛ ዲግሪ መርሃ ግብሮች የመማር ማስተማር ተግባሩን እያሳለጠ ይገኛል። ‹‹ጥራትን በጋራ/በጥምረት›› የሚል መሪ ቃል ያለው ዩኒቨርሲቲው ይህንኑ ተግባራዊ ለማድረግም ከመማር ማስተማር ሂደቱ በተጓዳኝ ከሀገር ውስጥ እና በውጭ ሀገር የሚገኙ የምርምርና ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ጋር በትስስር ሥራዎቹን በማከናወን ላይ እንደሚገኝ በዩኒቨርሲቲው መምህርት እንዲሁም የሕዝብና የውጭ ግንኙነት ዳይሬክተር የሺመቤት ቦጋለ (ዶክተር) ይገልጻሉ።

ዳይሬክተሯ እንደሚሉት፣ በዚህም ዘርፍ ተጠቃሽ የሆኑ እንቅስቃሴዎች ያሉ ሲሆን፤ የመማር ማስተማር ሂደቱን በማሳለጥ፣ የጥናትና ምርምር አድማስን በማስፋት እንዲሁም የምርምር ውጤቶችን ወደ ማህበረሰቡ ለማውረድ እንዲቻል የቴክኖሎጂ ሽግግር ለማከናወን ከሚያግዙ ተቋማት ጋር ጥምረት በመፍጠር ነው። ዩኒቨርሲቲው በሀገር ውስጥ ከአቻ የትምህርት ተቋማት ጋር የሚሰራ ሲሆን እንደ ጅማ ዩኒቨርሲቲ ያሉ አንጋፋ ተቋማትም በቀዳሚነት ይጠቀሳሉ። ሰላሌ ዩኒቨርሲቲ አራተኛ ትውልድ እንደመሆኑ ዕውቀትና ልምድ ለመቅሰም፣ አሰራሮችን ለማሻሻል እንዲሁም ዕውቀትን ለማሻገር ያመች ዘንድ በትብብር ይሰራል። ለአብነት ያህልም በጅማ ዩኒቨርሲቲ በስፋት ተግባራዊ የሆነውን ከተማሪዎች ምዘገባ አንስቶ ሌሎች አገልግሎቶችን በአንድ ካርድ ብቻ ማግኘት እንዲችሉ የሚያደርግ አሰራር ወደ ተቋሙ ማሻገር ተችሏል። በዚህም በቴክኖሎጂ የተደገፈ አገልግሎት ማስጀመርን በማሳያነት መጥቀስ ይቻላል።

በተመሳሳይ በግብርና ዘርፍ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ከደረሱ የትምህርት ተቋማት መካከል አንዱ ከሆነው ሃሮማያ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመሆንም የባለሙያዎችን አቅም በመገንባት ረገድ ስልጠናዎችን በመስጠት፣ ተማሪዎችን በማማከርና በመመዘንና ወዘተ ዘርፎች እየተሰራ ነው። እንደ አዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ እንዲሁም አርሲ ዩኒቨርሲቲ ካሉ ተቋማት ጋርም መሰል የቴክኖሎጂ ሽግግር እና የልምድ ልውውጥ ላይ በጋራ በመሥራት ላይ ይገኛል።

ከትምህርት ተቋማት ባለፈም ዩኒቨርሲቲው ከመንግሥታዊ ተቋማት ጋር በተለያዩ መስኮች አተኩሮ በመሥራት ላይም ይገኛል። ለዚህም ዳይሬክተሯ በማሳያነት የሚያነሱት የኢትዮጵያ ኢንተርፕሬነር ሺፕ ኢንስቲትዩት ሲሆን፤ የዩኒቨርሲቲውን ሠራተኞች በማሰልጠን፣ ተማሪዎች ሥራ ከመፈለግ ይልቅ ሥራ ፈጣሪ እንዲሆኑ በማስገንዘብ እንዲሁም የአካባቢው ህብረተሰብ ይህንኑ እንዲረዳ የማድረግ ተግባር ላይ አተኩሮ እየሰራ ነው። እንደ ሰበታ የምርምር ማዕከል ያሉ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ተቋማት ጋርም በጥምረት በመሥራት በዕውቀት ልውውጥና ልምድ ሽግግር ረገድ ከፍተኛ ጠቀሜታ እያገኘም ነው፡፡

ዩኒቨርሲቲው ከተለያዩ አካላት ጋር በትስስር ሲሰራ የጥናትና ምርምር ሥራዎችን ወደመሬት ለማውረድ እገዛ ከማድረጉ ባለፈ በተለያዩ ኢንዱስትሪዎች ውስጥ ያሉ ችግሮችን ለይቶ በማውጣት በጥናትና ምርምር መፍትሔ ለማግኘትም ረድቶታል። እንደሚታወቀው በኢትዮጵያ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ በሚገኙ ተማሪዎች እንዲሁም መምህራን የሚሰሩ የጥናትና ምርምር ሥራዎች ተግባራዊ ሆነው ችግሮችን ከመፍታት ይልቅ መደርደሪያ ላይ መቀመጥ እጣ ፋንታቸው ነው።

ነገር ግን የትምህርት ተቋማቱ ከተለያዩ አገልግሎት ሰጪዎችና ኢንዱስትሪዎች ጋር አብረው መሥራት ቢችሉ መሰል ችግሮች በቀላሉ በተማረ የሰው ኃይልና በሳይንሳዊ አሰራር ሊቀረፉ ይችላሉ። በዚህም የትምህርት ሆኖ ሌሎች ሥራዎች ላይ የተሰማሩት ተቋማት ጥናቱን ተግባራዊ በማድረግ እንዲሁም ችግርን በመፍታት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖራቸዋል። በሌላ በኩል ይህንን አሰራር ተግባራዊ በማድረጋቸው ዩኒቨርሲቲው ዓላማ አድርጎ የተነሳውን ጥራት እና ብቁ ዜጋን ከማፍራት ረገድ ጠቀሜታው ከፍተኛ መሆኑንና ኢንዱስትሪው ላይ ያለውን ችግር ለመለየት እንደሚረዳም ዳይሬክተሯ ያብራራሉ። ይህም ብቻ ሳይሆን ሁለቱ አካላት በምርምር የተደገፈ የማህበረሰብ አገልግሎት የሚሰጡበትንም መንገድም ይቀይሳል።

ይኸው አሰራር በከፍተኛ ትምህርት እንዲሁም የምርምር ተቋማት ውስጥ ከፍተኛ ወጪ ተደርጎባቸው የሚገነቡ የጥናትና ምርምር ቤት ሙከራዎችንና ማዕከላትንም በጋራ በመጠቀም የሀገር ሀብት እንዳይባክን ለማድረግም ያስችላል። ሰላሌ ዩኒቨርሲቲ ምስረታው ጥቂት ዓመታትን ያስቆጠረ እንደመሆኑ በውድ ዋጋ መሰራት የሚያስፈልጋቸው የቤተሙከራ ሥራዎችን ለማከናወን አቅም ባለማዳበሩ ምክንያት ጥምረት ከፈጠረባቸው የምርምር ተቋማት ቤተሙከራዎች ለመገልገል ዕድል ፈጥሮለታል። ትልልቅ ቤተሙከራ ያላቸው እንደ ሰበታ እና ሆለታ የምርምር ማዕከልን የመሳሰሉ ተቋማትም ከፍተኛ ሚና በመጫወት ላይ ይገኛሉ፡፡

በዚህ ሁኔታ በየተቋማቱ ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቁ ቤተሙከራዎችንና ወርክሾፖችን በመገንባት የሚወጣውን የሀገር ሀብት ከብክነት መታደግ እንዲሁም ውጤታማ ሥራን ለማከናወን እንደተቻለም አሰራሩ ማሳያ ይሆናል። ተግባር ተኮር ትምህርትን ከመስጠት አንጻርም ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ከሚያገኙት የንድፍ ትምህርት ባለፈ በዓይናቸው እየተመለከቱና በተግባር ተሳታፊ ሆነውበት በመማር ክህሎትንም እንዲያዳብሩ ከኢንዱስትሪዎች ጋር በትስስር መሥራት የተሻለ እድልን ይፈጥራል። በተጨማሪም ተማሪዎች የዩኒቨርሲቲ ቆይታቸውን አጠናቀው ከተመረቁ በኋላ ወደ ሥራው ዓለም ሲገቡ ለአሰራሩ አዲስ እንዳይሆኑ ይረዳቸዋል።

በሌላ በኩል ዩኒቨርሲቲዎች ከሌሎች ተቋማት ጋር በመተባበር መሥራታቸው አስቀድሞ ገበያው የሚፈልጋቸውን ተማሪዎች አውቆ ለማፍራትም ያስችላል። በተደጋጋሚ እየተስተዋለ እንደሚገኘው ኢንዱስትሪዎች የራሳቸውን የትምህርት ሥርዓት በማዘጋጀት ተማሪዎችን ተቀብለው ስለሚያሰለጥኑ ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የሚወጡ ተመራቂዎች ቦታ የሚያጡበት ሁኔታ ይፈጠራል። ይህ እንዳይሆንም የትምህርት ተቋማቱ ከኢንዱስትሪው ጋር መሥራት የሀገሪቱ ገበያ የሚፈልገው ምን ዓይነት ተማሪዎችን ነው የሚለውን ለመለየት ከማስቻሉም ባለፈ ሥራ ከማጣት ጋር ተያይዞ የሚፈጠረውን ቀውስ ለመቀነስ ይረዳል። በመሆኑም እነዚህ ተቋማት አብረው ከመሥራት ባለፈ በሥርዓተ ትምህርት ቀረጻም ላይ ተሳታፊ እንዲሆኑ ማድረግ ዘርፈ ብዙ ፋይዳ አለው።

ከትምህርትና ጥናት በዘለለ ከተጣመራቸው ተቋማት ጋር በመሆን የአካባቢውን ህብረተሰብ ተጠቃሚ ሊያደርግ በሚችል የማህበረሰብ አቀፍ አገልግሎት ላይም እየተሳተፈ ነው። በማሳያነት ለማንሳት የሚቻለውም ከሰላሌ ዩኒቨርሲቲ ተመርቀው ሥራ ያላገኙ ወጣቶችን በማሰባሰብ በኢትዮጵያ ብዝሀ ሕይወት ኢንስቲትዩት ጋር በነበረው ስምምነት መሰረት ምርጥ የወተት ዝርያ ያላቸውን ላሞች የማዳቀል ስልጠና እንዲያገኙ በማድረግ በየአካባቢው አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግን ነው። ከዚህ ጎን ለጎን ሀገር በቀል ካልሆነ ግብረሰናይ ድርጅት እና ከአርሲ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመሆን የወተት ዝርያ ያላቸውን ላሞች ለማዳቀል የሚያስችል ዘር ከኮሪያ በማስመጣትና የሰለጠኑትን ወጣቶች በመጠቀም በሰሜን ሸዋ ዞን ለሚገኙ 1ሺ አርሶ አደሮች በነፃ አገልግሎቱ እንዲሰጣቸው ተደርጓል። በዚህም ከ1ሺዎቹ መካከል 700 የሚሆኑት ስኬታማ እንደነበሩ በተደረገው ክትትል ማረጋገጥ ተችሏል።

ከአካባቢ ማልማት ጋር በተያያዘም በረሃማ የነበሩ አካባቢዎችን መልሶ እንዲያገግም በማድረግ ረገድ ስትራቴጂ በመንደፍና የሶስትዮሽ ግንኙነት በመፍጠር፤ በሰላሌ ዩኒቨርሲቲ ቅርብ ርቀት ላይ የሚገኘውን የዓባይ በረሃ ከደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ እንዲሁም ከኢትዮጵያ ደን ልማት ኢንስቲትዩት ጋር በመሆን የበረሃ ቀርከሃ ችግኝ በማፍላትና በማላመድ የማልማት ሥራ እየተሰራ ነው። ከቀርከሃው በተጨማሪ የቆላ ፍራፍሬዎችን በማልማት ለአካባቢው ማህበረሰብ እንዲሰራጭም ተደርጓል። በአካባቢው እምብዛም ያልተለመደውን የቡና ተክል ምርታማ ሊሆን በሚችል መልኩ በማላመድ ለማህበረሰቡ ተከፋፍሏል። በዚህም ገላጣና የተራቆተ የነበረውን ስፍራ መልሶ እንዲያገግም በማድረግ ማሳያ የሆነ ፕሮጀክት ተግባራዊ በመደረግ ላይ እንደሆነም ዳይሬክተሯ ዶክተር የሺመቤት ያስረዳሉ፡፡

‹‹ደረጃ ዶትኮም›› የተባለና የሥራ ፈጠራ ላይ ለተማሪዎች ስልጠና የሚሰጥ ድርጅትም ከዩኒቨርሲቲው ጋር በፈጠረው ቁርኝት ተማሪዎች በሥራ ፍለጋ ክህሎት፣ በሲቪ አጻጻፍ እና በሌሎች ጉዳዮች ላይ ላለፉት ዓመታት ስልጠና ሲሰጥ ቆይቷል። ከመገናኛ ብዙሃን ጋር በመሆንም የተቋሙን ሥራዎች ለሕዝብ ተደራሽ በማድረግ እንዲሁም የጋዜጠኝነትና የኮሙዩኒኬሽን ትምህርት ክፍል ተግባራዊ ልምምድ እንዲያደርጉ በማመቻቸት በኩልም በትስስር ይሰራል። በዩኒቨርሲቲው ስር ያለውን የፊቼ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ከጳውሎስ ሆስፒታል ጋር በመሆንም ለአካባቢው ነዋሪዎች የነፃ ሕክምና እንዲያገኙም ተደርጓል። ከባንኮች ጋር በመተባበር ለተማሪዎች ተግባራዊ ልምምድ እንዲሁም የዩኒቨርሲቲውንም ሆነ ሌላውን ማህበረሰብ ሊጠቅም በሚችሉ ጉዳዮች ላይም በጋር ይሰራል።

ይህንንም በቀጣይ ለማጠናከርና አዳዲስ ቁርኝቶችን ለመፍጠርም ዩኒቨርሲቲው በትኩረት እየሰራ ይገኛል። ተቋማት በትስስር የህብረተሰቡን ችግር ለመቅረፍ መሥራት ተገቢ በመሆኑ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት፣ የመንግሥትና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት በጋራ ቢንቀሳቀሱ ሥራቸው ይበልጥ ውጤታማና ፍሬያማ መሆን ይችላሉ። ሀገርን በመጥቀም እንዲሁም ሀብትን በጋራ መጠቀም እንደሚያስችልም ዳይሬክተሯ አስረድተዋል።



**በሰላሌ ዩኒቨርሲቲ የሕዝብና የውጭ ግንኙነት ዳይሬክተር የሺመቤት ቦጋለ (ዶክተር)፤**

# ወቅታዊ

# ‹‹ሰላማዊ የፖለቲካ እንቅስቃሴ የሚፈጠሩ እድሎችን በአግባቡ መጠቀም ይገባል››

አቶ ደስታ ዲንቃ
የኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ሰብሳቢ

ራስወርቅ ሙሉጌታ

የደርግ መንግሥት ውድቀትን ተከትሎ በመጣው ለውጥ በኢትዮጵያ በርካታ የፖለቲካ ፓርቲዎች ወደ እንቅስቃሴ ለመግባት በቅተዋል። አብዛኞቹ ፓርቲዎች ግን ያላቸውን አቅምና በሕዝብ ዘንድ የነበራቸውን ቅቡልነት ይዘው ለመዝለቅ አልታደሉም። በራሳቸው ድክመትም ሆነ በውጭዊ ጫና ከፖለቲካው መድረክ የተሰናበቱትም በርካቶች ናቸው። ስም በመቀየር፤ ለሁለት በመከፈል እና ጥምረት መፍጠር አባላትና ደጋፊዎቻቸውን ግራ ሲያጋቡ የነበሩም በርካቶች ናቸው።

ይህም ሆኖ እነዚህ የፖለቲካ ፓርቲዎች ሚዲያም ሆነ የተለያዩ መድረኮችን ሲያገኙ የፖለቲካ ምህዳሩ ጠባብ ነው በሚል ቅሬታ ከማቅረብ በዘለለ ያለውን አጋጣሚ ሲጠቀሙ አይታይም። ለምርጫ ሰሞን ከሚደረግ ጥድፊያ በዘለለም በንቃት ዓመት ከዓመት ሲሰሩም አይስተዋልም። አብዛኛዎቹ ድምጻቸውን የሚያሰሙት መንግሥትን በረባ ባረባው ለመቃወምና ስህተቶችን ፈልጎ በማውጣት ችግር መኖሩን ለመግለጽ ብቻ ነው። ዛሬም ድረስ ሀገሪቷ ካላት ብዝሀነት እና ካሉባት ዘርፈ ብዙ ችግሮች አኳያ አዳዲስ ሃሳቦችን፤ ከችግር መውጫ መንገዶችንና ሀገራዊ አጀንዳዎችን ይዘው የሕዝብን ቀልብ ገዝተው የሚንቀሳቀሱ አሉ ለማለት አያስደፍርም።

በቅርቡ የተከሰተው ለውጥም ቢሆን ብዙዎቹን ፖለቲከኞች ከእስር በማውጣት በተለያዩ ሀገራት የነበራቸውን እንቅስቃሴ ወደ ሀገር ቤት እንዲያመጡ ቢያደርግም በነበረው ሙቀት መቀጠል አልተቻለም የሚሉና ተያያዥ አስተያየቶች ሲሰነዘሩ ይሰማል።

እኛም ለዛሬው እትማችን ከላይ የተዘረዘሩትን ጥያቄዎች በማንሳት ያላቸውን አስተያየት እንዲያካፍሉን የኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ሰብሳቢ እና የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ ፀሐፊ አቶ ደስታ ዲንቃን አነጋግረን የሚከተለውን ይዘን ቀርበናል።



ፎቶ:- ሃዲስ አብርሃ

**አዲስ ዘመን፤- የኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ሲመሰረት መዳረሻ አላማው ምን ነበር?**

**አቶ ደስታ፤-** የኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት በ2011 ዓ.ም ሲመሰረት አላማው ያደረገው አዲስ መንግሥት መምጣቱን ተከትሎ በወቅቱ የነበረውን ተቃውሞ ወደ ሰላማዊ እንቅስቃሴ ለመቀየርና መረጋጋት ለመፍጠር ነበር። ከዚያ በኋላም ግን የነበረውን ሁኔታ ከግምት በማስገባት የሕግ የበላይነት እንዲረጋገጥ፤ ገዢውን ፓርቲና መንግሥትን ጨምሮ የፖለቲካ ፍላጎትና አመለካከት አለን የሚሉ አካላት ለሕግ ተገዢ ሆነው እንዲንቀሳቀሱ የሚያስችል የፖለቲካ ሥርዓት ለመፍጠር እየሰራ ይገኛል።

በተጨማሪም ፓርቲዎች ሀገራዊ በሆኑ አጀንዳዎች ላይ ተመሳሳይና ተቀራራቢ አቋም በመያዝ በኢኮኖሚ፤ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ሁኔታዎች አብረው ለመሥራት የሚያስችሉ ሁኔታዎችን ያመቻቻል። ባጠቃላይም በመንግሥት በዜጎችና በፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል የሚኖረው ግንኙነት ሕገ መንግሥታዊ እንዲሆን ግቡን ያደረገ ገዥውን ፓርቲ ጨምሮ ሁሉም የፈረሙትን የቃል ኪዳን ሰነድ ተግባራዊ ለማድረግ እየሰራ ይገኛል። በተግባርም የጋራ ምክር ቤቱ ለመጀመሪያ ጊዜ ሁሉንም ተቃዋሚ ፓርቲዎች በአንድ መድረክ እንዲወያዩና አላማን በኃይል ለማሳካት የሚደረግ እንቅስቃሴ እንዲቀንስ ለማድረግ የበቃም ነው። በጋራ ምክር ቤቱ ስር ያሉት ሁሉም ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች የሰላምን መንገድ የመረጡ ናቸው። በመሆኑም ምክር ቤቱ ከተቋቋመ በኋላ እነዚህን ፓርቲዎች ተከትሎ የተፈጠሩ የሰላም መደፍረስ ችግሮች አለመከሰታቸውም ለዚህ አንዱ ማሳያ ነው።

**አዲስ ዘመን ፤- የፖለቲካ ፓርቲዎች እንቅስቃሴ ወቅታዊነት ይስተዋልበታል፤ መቃወም ላይ የሚያተኩሩ ናቸው ፤ የሕዝብ ቀልብ ይስብልናል የሚሉት አጋጣሚ ካልተፈጠረ ሲንቀሳቀሱ አይስተዋልም የሚሉ ትችቶች ይሰሙባቸዋል፤ ለእነዚህ ሃሳቦች ያለዎት ምላሽ ምንድን ነው?**

**አቶ ደስታ፤-** በዚህ ሃሳብ አልስማማም:: እንደ ጋራ ምክር ቤት እኛ ሁልጊዜም ሥራ ላይ ነን። በአቅም ውስንነት የኮሙዩኒኬሽን ሥራው ደካማ በመሆኑ ለሕዝብ አይደርስም እንጂ የፖለቲካ ፓርቲዎችም ዓመቱን ሙሉ ሥራ ላይ ናቸው። አሁን እየተካሄደ ያለው የፖለቲካ ፓርቲዎች ውይይት ሊደረግ የቻለውም በእኛው አነሳሽነት ነው። በጋራ ምክር ቤቱ የተፎካካሪ ፓርቲዎች ጥምረት ብቻ ሳይሆን የገዥው ፓርቲ አባላትም አሉ። ለምሳሌ የእኔ ምክትል በገዢው ፓርቲ ውስጥ የዲሞክራሲ ባሕል ግንባታ ዘርፍን የሚመሩ ናቸው።

ከዚህ ቀደምም በሚያዝያ ወር ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ጋር ውጤታማና ጥሩ የሚባል የተሳካ ውይይት አድርገናል። ይህንንም ተከትሎ የክልል ፓርቲዎች ከትግራይ ክልል ውጭ ከክልል መንግሥታት ጋር ውይይት ማካሄድ ችለዋል። በተጨማሪ በአዲስ አበባ እና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮች በፖለቲካ ፓርቲዎቹና በከተማ አስተዳደሮቹ መካካል ተመሳሳይ ውይይት ተከናውኗል። የጋራ ምክር ቤቱ ያልተሳተፈበት በሲዳማ የተካሄደው ውይይት አሳታፊ ያልነበረ ሲሆን በእኛ እይታ አጥጋቢ ውጤት የተገኘበትም አልነበረም። በተጨማሪ ሀገር አቀፍ ፓርቲዎች በምክትል ጠቅላይ ሚንስትር ማዕረግ የዲሞክራሲ ባሕል ግንባታ ኃላፊ ከሆኑት ከአቶ አደም ፋራህ ጋር ውይይት ተካሂዷል። ከዚህ ሁሉ በኋላ የፖለቲካ ፓርቲዎች የሕዝቡን ጥያቄዎች በመያዝ ሐምሌ አሥራ አምስት ቀን ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ጋር በመገናኘት ውይይት ያካሄድነው። ውይይቱም ውጤታማ ነበር ማለት ይቻላል። ስለዚህም የፖለቲካ ፓርቲዎች እጃቸውን አጣጥፈው የተቀመጡበት ሁኔታ የለም::

**አዲስ ዘመን፤ - ኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር እያካሄደች ነው:: ሆኖም በውይይቱ ያልተሳተፉ የጋራ ምክር ቤቱ አባል የሆኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች እንዳሉ ይታወቃል። ይህ እንዴት ሲሆን ቻለ ?**

**አቶ ደስታ፤-** የጋራ ምክር ቤቱ አባላት የሆኑ በውይይቱ ያልተሳተፉት ፓርቲዎች አሉ። ምክንያታቸው ደግሞ አባሎቻችን ታስረውብናል፤ ቢሮዎች ተዘግተውብናል የፖለቲካ ምህዳሩ አልተስተካከለም፤ በሕገ መንግሥቱ መሠረት መብታችን ተጠብቆልን መንቀሳቀስ አልቻልንም፤ በመንግሥት በኩል በውይይት መሠረታዊ ለውጥ ለማምጣት የሚያስችል ርምጃ እየተወሰደ አይደለም የሚል ምክንያት ያላቸውና ያኮረፉ ናቸው። በዚህም ከሀገራዊ የምክክር ኮሚሽኑ ጋር ከምናደርጋቸው ውይይቶችም ራሳቸውን አግልለዋል።

ከዚህ ውስጥ አንዳንድ እኛም የምንቀበላቸው ጉዳዮች አሉ። ለምሳሌ ሰባት የኦነግ አመራሮች ክስ ሳይመሰረትባቸው ለሁለት ዓመታት የታሰሩ አሉ። በዚህም ፓርቲው አንዳንድ ውሳኔዎች ለማስተላለፍ ከግማሽ በላይ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አመራሮች መገኘት ስላለባቸው መወሰን ሳይችሉ የቀሩበት ሁኔታ አለ። ይህም ሆኖ እስካሁን ከቆየንበት የፖለቲካ ባሕል መውጣት እንዳለብን እናምናለን። አሁንም ድረስ ያለን የፖለቲካ አካሄድ የሚያሳየን የአመለካከት መለያየትን እና የፍላጎትን ልዩነትን በአግባቡ ማስተናገድ ሳንችል ቆይተናል። ይህ አካሄድም እንደ ሀገር በኢኮኖሚው በፖለቲካውና በማህበራዊ መስክ ብዙ ዋጋ አስከፍሎናል። በመሆኑም ዛሬም ነገም አማራጭ ሊሆን የሚገባው በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥም ብንሆን በሰላማዊ መንገድ እየተገናኙ መምከር ብቻ ሊሆን ይገባል።

**አዲስ ዘመን፤- ከለውጡ በኋላ ለፖለቲካ ፓርቲዎች እንቅስቃሴ ምቹ ሁኔታ ተፈጥሯል ለማለት ያስደፍራል?**

**አቶ ደስታ፤-** ችግር የለም ሁሉም ነገር ምቹ ነው የሚል ምልከታ የለንም። የጋራ ምክር ቤቱ ሲቋቋም ቃል ኪዳን የተግባባነው በሰላማዊ መንገድ ብቻ ለመንቀሳቀስ ነው። ሁሉም ነገር የተስተካከለ ሊሆን እንደማይችል ግንዛቤው አለን። መሥራት ያለብን በዛ ችግርና ጫና ውስጥም ሆነን ቢሆን በሰላማዊ መንገድ አላማችንን ለማሳካት ነው። ይህም ሆኖ እንደ ፓርቲ ብቻ ሳይሆን እንደ ግለሰብም በተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲ አባልነት ለመሳተፍም ስጋት አለ። በዚህም ዜጎች ራሳቸውን ከፖለቲካ ሲያገሉ ይታያል። ከእነዚህም መካከል ለውጥ የለም እና ለውጡ አዝጋሚ ነው የሚል ምልከታ ያላቸውም አሉ።

ሌላው በተፎካካሪ ፓርቲዎችና በመንግሥት መካከል ያለው ግንኙነት እንዲሻክር ከሚያደርጉት መካከል አንዱ የሰላም መደፍረስ ነው። ይህን በተመለከተ ስህተቱ የመንግሥትም የተፎካካሪ ፖለቲካ ፓርቲዎችም ሊሆን ይችላል:: እኛን ግን በማንኛውም ሁኔታ ያለ የሰላም

**የኃይል ርምጃ** እና ጦርነት ወገንን ለስቃይና ለሞት ይዳርጋል፤ ንብረት ያወድማል ሰላም ያደፈርሳል በመሆኑም የሰላም መንገድ ቀዳሚ አማራጭ ነው። የሰላም መንገድን ይዞ በቀስታ ወደ ዲሞክራሲ መጓዝ ይቻላል። የጋራ ምክር ቤቱም ሆነ አባል የፖለቲካ ፓርቲዎች ፍላጎትና እንቅስቀሴም ሰላም ነው

ወደ ገጽ 10 ዞሯል

# ወቅታዊ

# ‹‹ሰላማዊ የፖለቲካ እንቅስቃሴ የሚፈጠሩ...

ከገጽ 9 የዞረ

መደፍረስ ያሳስበናል። ግጭቶች በማህበረሰቡ ሰላም፤ በሥራ ፈጠራ በኢንቨስትመንት ጫና እየፈጠሩ ይገኛል። ብዙ ትምህርት ቤቶች ከመማር ማስተማር ተግባራቸው እንዲስተጓጎሉ ሆነዋል፡፡ የጤና ኬላዎች ላይ ጉዳት ደርሷል፡፡ ይህ እንደ ጋራ ምክር ቤቱም አባላት የፖለቲካ ፓርቲዎችን የሚያሳሰብ ነው።

ይህ ችግር በሰላም እንዲፈታ የሰላም ሚንስትሩን አቶ ብናለፍ አንዱዓለምን አነጋግረናል። ከእሳቸውም ሆነ ከጠቅላይ ሚንስትሩ ጋር በነበረን ውይይት ችግር ስለመኖሩ ከስምምነት ደርሰናል። እነዚህ ችግሮች አለመፈታታቸው ቅሬታ ፈጥሮብናል።

ለምሳሌ በአዲስ አበባ ሰላማዊ ሰልፍ ለማድረግ የተንቀሳቀሱ ግለሰቦች እና ፓርቲዎች ፈቃድ ማግኘት አልቻሉም። ምክንያቱ ደግሞ የሰላሙ ሁኔታ አስጊ በመሆኑ እንደሆነ መንግሥት አስቀምጧል። ይህ ፍርሃት እንዲወገድና በዜጎች መካከል መተማመን እንዲፈጠርና አንዱ የሌላው ስጋት እንዳይሆን መሥራት የሚጠበቅ ይሆናል። ለዚህ ደግሞ ውይይት ተመራጭ መንገድ ነው። እየተወያየን እየተግባባን ፍላጎቶቻችንንም ስጋቶቻችንንም እየገለጽን በህብረት የፖለቲካ ባሕላችን መቀየር ይጠበቅብናል። በአሁኑ ወቅት በተደጋጋሚ ውይይቶች እንዲካሄዱ እየሰራን ያለውም ለዚሁ ነው።

**አዲስ ዘመን ፧- የጋራ ምክር ቤቱም ሆነ የምክር ቤቱ አባል የፖለቲካ ፓርቲዎች የሀገርና የሕዝብ ሰላም እንዲጠበቅ ቅድሚያ የሚሰጡ ከሆነ በአሁኑ ወቅት በሀገሪቱ አንዳንድ ቦታዎች የተፈጠሩ የፀጥታ መደፍረሶች ተወግደው ሰላም እንዲሰፍን ምን የሰሩት ሥራ አለ?**

**አቶ ደስታ ፧-** እኛ አጣብቂኝ ውስጥ ነው ያለነው፡፡ መንግሥትን ደግፈህ ከተናገርክ ጫካ የገቡት በጠላትነት ይፈርጁናል። እነሱንም ደግፈን ከተናገርን መንግሥት በተመሳሳይ በጠላትነት ያስቀምጠናል። በዚህ ሁኔታ የሸምግልና ሚና መጫወትም ይከብዳል። እንደ እኛ ለሰላም ሲባል መሳሪያ ሳያነሱ መታገል ይሻላል የሚል አቋም አለን።

እኛ በተቃዋሚ ጎራ ሆነን የማንቀሳቀሰው ትግላችንን ስናካሂድ እንሰቃያለን፤ እንታሰራለን ፤ እንሞታለን ብለን እንጂ እንገድላለን፣ እናስራለን፣ እናሰቃየለን እያልን አይደለም። ሁሉም እንደኛ ይህንን መንገድ ቢከተሉ ይሻላል የሚል እምነትም አለን። የኃይል ርምጃ እና ጦርነት ወገንን ለስቃይና ለሞት ይዳርጋል፤ ንብረት ያወድማል ሰላም ያደፈርሳል በመሆኑም የሰላም መንገድ ቀዳሚ አማራጭ ነው። የሰላም መንገድን ይዞ በቀስታ ወደ ዲሞክራሲ መጓዝ ይቻላል። የጋራ ምክር ቤቱም ሆነ አባል የፖለቲካ ፓርቲዎች ፍላጎትና እንቅስቀሴም ሰላም ነው። መንግሥትን የዲሞክራሲ ምህዳሩን እንዲያሰፋ የምንጠይቀውም ለዚህ ነው። የጋራ ምክር ቤቱና የፖለቲካ ፓርቲዎቹ ጥረት፤ በመንግሥትም በኩል እየታየ ያለው ፍላጎት እነዚህ ችግሮች በሚፈቱበት ጉዳይ ላይ ለመሥራት ነው። ለዚህም በቀጣይ የፖለቲካ ባሕሉን ለመቀየርና ለማዘመን የምንሰራቸው ሥራዎች ይኖራሉ።

**አዲስ ዘመን፧- በሀገሪቱ ዘላቂ ሰላም ለማስፈን ተስፋ ከተጣለባቸው ጉዳዮች መካከል ሀገራዊ ምክክሩ አንዱ ነው። ከምክክር ኮሚሽኑ ጋር ያላችሁ ግንኙነት ምን ይመስላል?**

**አቶ ደስታ፧-** የሀገራዊ ምክክር አላማዎች መሠረታዊ የሆኑ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ያሉ ልዩነቶችን በማጥበብ መግባባትን ለመፍጠር፣ በተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች መካከልና ከመንግሥት ጋር ያለን ግንኙነት ለማሻሻል፣ መተማመንን ለማጎልበት፣ የመነጋገር ባሕልን ለማጎልበት፣ ዘላቂ ሰላምን ለማምጣት፣ ጠንካራና ቅቡልነት ያለው ሀገረ መንግሥት በጋራ ለመገንባት፣ ልዩነቶችን በሰላማዊና ሕጋዊ መንገድ ለመፍታት፣ የዴሞክራሲና የፖለቲካ ሽግግር ለማስቻል፣ ልማትን ለማፋጠን ምቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠር ነው።

እነዚህ አላማዎች ደግሞ ምክር ቤቱና አባላት የፖለቲካ ፓርቲዎች የሚደግፉት ነው። በመሆኑም ከሀገራዊ ምክክር ኮሚሽኑም ጋር በቅርበት እየሰራን እንገኛለን። እስካሁንም የፖለቲካ ፓርቲዎች አጠቃላይ ተሰባስበን ከኮሚሽነሮቹ ጋር እየተገናኘን በተደጋጋሚ መክረናል። በተጨማሪ ከዓለም አቀፍ ለጋሽ ድርጅቶችም ጋር በመተባበር እየሰራን እንገኛለን። በቢሾፍቱ ሶስት ጊዜ አዲስ አበባ ሁለት ጊዜ የጋራ መድረክ በማዘጋጀት ኮሚሽነሮቹ ለፖለቲካ ፓርቲ አመራሮች ምን እየሰሩ እንዳለ ገለጻ አድርገዋል። ምን ያህል ከፖለቲካ ነፃ ሆነው እየሰሩ መሆኑን እንዲያሳውቁ ሁኔታዎችን አመቻችተናል። ከአዲስ አበባ ውጭ ወጥተው ሲንቀሳቀሱ በእኛ በኩል ሊደረግላቸው የሚፈልጉት ነገር ካለም ድጋፍ እያደረግንላቸው እንገኛለን።



**አዲስ ዘመን ፧- የፖለቲካው መድረክ የተለያዩ ሃሳቦች እንዲንሸራሸሩበት ለማድረግ በገዢው ፓርቲና በተፎካካሪ ፓርቲዎች መካከል ካለው ውይይት ባለፈ በተፎካካሪዎች መካከልም የሃሳብ ልውውጥ እንዲደረግ ይጠበቃል። በዚህ ረገድ የሰራችኋቸው ወይንም ልትሰሩ ያሰባችሁት ካለ ቢያካፍሉን?**

**አቶ ደስታ ፧-** እስካሁን ባለው ሂደት የጋራ ምክር ቤቱ በመንግሥትና በተፎካካሪ ፓርቲዎች መካከል እንደ ድልድይ በመሆን በርካታ ሥራዎችን ለማከናወን በቅቷል። ነገር ግን ከዚህም በዘለለ ዋነኛ አላማው የሃሳብ የበላይነትን የተከተለ የፖለቲካ ምህዳር እንደ ሀገር መፍጠር በመሆኑ በዚህ ረገድ ሁሉን ሥራዎች አቅማችን በፈቀደ የምንሰራ ይሆናል። እስካሁን ድረስም ውይይቶች ተካሂደዋል ስንል የጋራ ምክር ቤቱ አባላት አንድ ሃሳብ አንድ አቋም ይዘው ከመንግሥት ጋር የሚሞግቱበት ሳይሆን እርስ በእርስ የሚቃረኑ ሃሳቦች የሚስተናገዱባቸው ናቸው።

በአንዳንድ ወገኖች እይታ ተቃዋሚዎችን ሁሉ አንድ አድርጎ የማየት ነገር ይስተዋላል። ግን በውስጣችን የተለያዩ ልዩነቶች አሉ። ምን አልባት በአንዳንድ የፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል ያለው ልዩነት በሃሳብ ደረጃ ከመንግሥት ጋር ካለው የሰፋ ሊሆን ይችላል። ይህ አስተያየት ራሱ ካልተስተካከለ የፖለቲካ አመለካከት የሚመነጭና ብዙዎቻችን ውስጥ ያለና ሊስተካከል የሚገባው ነው።

እኛ ባለን መረጃ አንደ ሃሳብ የሚነሳው የጋራ ምክር ቤቱ መንግሥትን ማለትም ገዢውን ፓርቲ የሚገዳደር ሳይሆን ራሱ የመንግሥት አንድ ወገን ተደርጎ እንደሚወሰድ ነው። እኔ ራሴ በ2002 ዓ.ም ፖለቲካውን ከተቀላቀልኩበት ጊዜ ጀምሮ የመንግሥት ሰዎችን አልቀርብም ነበር። መንግሥትን መቅረብ እንደ ስህተት፤ እንደ ክህደት ፖለቲካውን እንደ ማበላሸት የምንቆጥር የፖለቲካ ፓርቲዎች ብዙዎች ነን። በአንዳንድ ወገኖች በኩል እንደ ወንጀለኝነትም ሲታይ ይስተዋላል። እኔ ይህ አካሄድ አዋጭ አለመሆኑን ከተረዳሁ ውዬ አድሪያለሁ። መነጋገር ሲኖርብን በሰላማዊ መንገድ እስከሆነ ድረስ መነጋገር መወያየት አለብን። ይህ አካሄድ ሊለመድ ይገባል።

የኢትዮጵያን ፖለቲካ የሚያበላሹና በሕዝብ ዘንድ አመኔታን የሚያሳጡ ተግባራት የሚያከናውኑ በገዢው ፓርቲና በመንግሥት ውስጥ ብቻ ሳይሆን በተፎካካሪ ፓርቲዎችም ውስጥ አሉ። በተለይም ከለውጡ በኋላ ጠንካራ የተባሉ ለውጥ ያመጣሉ የተባሉ ፖለቲከኞች የፖለቲካ አላማቸውንና ደጋፊዎቻቸውን እርግፍ አድርገው ትተው አሁንም ሕዝብን በማታለል ውስጥ ያሉ ፖለቲከኞች አሉ።

**መ**ንግሥትን መቅረብ እንደ ስህተት፤ እንደ ክህደት ፖለቲካውን እንደ ማበላሸት የምንቆጥር የፖለቲካ ፓርቲዎች ብዙዎች ነን። በአንዳንድ ወገኖች በኩል እንደ ወንጀለኝነትም ሲታይ ይስተዋላል። እኔ ይህ አካሄድ አዋጭ አለመሆኑን ከተረዳሁ ውዬ አድሪያለሁ

**አዲስ ዘመን፧- በሀገሪቱ ያለው የፖለቲካ እንቅስቃሴ ሀገር በሚጠቅም መልኩ የተቃኘ እንዲሆን ከገዢው ፓርቲ/ ከመንግሥትም ሆነ ከተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምን ይጠበቃል።**

**አቶ ደስታ፧** - በዚህ ረገድ እንደ ጋራ ምክር ቤት የያዝነው ሃሳብ እስካሁንም በቀጣይም የምንሰራበት ለሰላማዊ እንቅስቃሴ ቅድሚያ መስጠት ነው። የእኛም ቀዳሚ ትኩረት ይሄ ነው። በቅርቡ ለጠቅላይ ሚንስትሩ በሀገሪቱ አንዳንድ ቦታዎች ያለውን ግጭት መንግሥት በሰላም በሆደ ሰፊነት እንዲፈታ ጠይቀን ነበር። እሳቸው በሰጡን ምላሽ ሰላም እንዲሰፍን ሙሉ ፍላጎት እንዳለ ለዚህም መሥራት ያለባቸውን ሥራ እየሰሩ እንደሆነ ነግረውናል። ነገር ግን መሳሪያ አንስተው የሚተኩሱ ሰዎችን ዝም ማለት የማይቻል መሆኑን ተናግረዋል። እኛ ግን እንደ ዛሬው ሁሉ ነገም የትኛውም ትግል በሰላማዊ መንገድ እንዲሆን ከመሥራት አንቆጠብም።

ለሰላም የሚሰራ ሥራ በአንድ ወገን እንቅስቃሴና ፍላጎት ብቻ ውጤታማ ሊሆን አይችልም። ሁላችንም ለሰላም አንዱ ለሌላው የህልውና ስጋት ሳይሆን መንቀሳቀስ መቻል አለብን። ለዚህም እንደ ጋራ ምክር ቤትም፤ እንደ ፖለቲካ ፓርቲም፤ እንደ ግለሰብም ለጦርነትና ለግጭት ከሚዳርጉ አመለካከቶችና ተግባራት መቆጠብ እንዳለብን አምነን እየሰራን ነው።

ይህም ሆኖ የአንድ ሀገር ፖለቲካ እንዲስተካከል የፖለቲካ ፓርቲዎች ብቻ ሳይሆን የሌሎች አካላትንም ተሳትፎ ይጠይቃል። የፖለቲካው መስክ ብዙ ተዋናዮች አሉት። ከእነዚህ መካከል ሚዲያው ትልቅ ድርሻ አለው። ሚዲያው የሚታመን ሥራ ይሰራል ብለን እናምንም። ይህንን ስንል መንግሥትን ይቃወም እኛን ይደግፍ ማለታችን አይደለም። ነገር ግን በማህበረሰቡ ዘንድ ያሉ ችግሮችን እየተከታተለ የማስተላለፍ ኃላፊነት እንዳለበት ይሰማናል። ይህ አካሄድ በቀጥታ የሀገሪቱን ፖለቲካ መስመር የሚያሲይዝ ነው። ሁሉም የፖለቲካ ፓርቲ የሚንቀሳቀሰው እንደ ሀገርም ሆነ እንደ ማህበረሰብ እወክለዋለሁ ያለውን ሕዝብ ችግር ለመቅረፍ ነው። ሚዲያው ችግሩን ለሕዝብና ለመንግሥት ተደራሽ አድርጎ መፍትሔ የሚያሳይ ከሆነ በፖለቲካው መስክ ትልቅ ሚና ይጫወታል ማለት ነው፡፡ በዚህም ትልቅ ሀገራዊ ሥራ ሰራ ማለት ነው። እንደ ጋራ ምክር ቤት ይህ እንዲሆን እንፈልጋለን።

በተመሳሳይ ከሌሎች መንግሥታዊ ከሆኑ ተቋማትና ከፍትህ ሥርዓቱም ይበቃል። እነዚህ ተቋማት ሕግን መሠረት አድርገው የሚንቀሳቀሱ ከሆነ በአንድም ይሁን በሌላ መንገድ የሕዝብን መብት አስከበሩ ለሕዝብ ጥያቄ ምላሽ ሰጡ ማለት ነው። የፖለቲካ ፓርቲዎችና የፖለቲከኞችም የመጨረሻ ግብ ለሕዝብ ጥያቄ ምላሽ መስጠት፤ የሕዝብን ችግር መቅረፍና ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ነው። በመሆኑም እንደ ሀገር ሲታይ በየትኛውም መንገድ ቢሆን የሚፈለገው የሕዝብ ጥያቄ መፍትሔ ማግኘቱ ነው።

**አዲስ ዘመን፧- በቀጣይ ከጋራ ምክር ቤቱ ምን እንጠብቅ ?**

**አቶ ደስታ፧-** የጋራ ምክር ቤቱ የራሱ የሆነ የፖለቲካ አመለካከት የለውም። ራሱ በሀገሪቱ ያለው የፖለቲካ አመለካከት የተስተካከለ እንዲሆን መሥራት ነው። የተስተካከለ ማለት ደግሞ በዋነኝነት የፖለቲካ አመለካከቶችን በሰላማዊ መንገድ በመቻቻልና በመነጋገር ማስተናገድ ማለት ነው። ይህ መሳካት ከቻለ እንደ ሀገር ፖለቲካው መስክ ትልቅ ድል ተገኝቷል ለማለት ይቻላል። እንደ ጋራ ምክር ቤት ለቀጣዩ ትውልድ አመለካከትን በሰላማዊ መንገድ ማራመድ እንደሚቻልና እንደሚገባ ማስተማር ከቻልን እኛ ከምንም በላይ ውጤታማ መሆን እንደቻልን ነው የሚሰማን። እኛን የሚደግፉ አካላትም ይህንን መሠረት አድርገው መሆን አለበት የሚል አቋም አለን።

**አዲስ ዘመን፧- ስለነበረን ጊዜ እናመሰግናለን።**

**አቶ ደስታ፧-** እኔም አመሰግናለሁ።

ስፖርት እና መዝናኛ

# ፋሽን

## ውድ ሽቶ ወይንስ ቆንጆ ሽቶ ?

**ሰሚራ በርሀ**

ሽቶዎች በተለያዩ ሀገራት በተለያየ መንገድ ተሰርተው ለገበያ ይቀርባሉ። ፈረንሳይ በዚህ በእጅጉ ትታወቅበታለች። ለመጀመሪያ ጊዜ ሽቶን በመጠቀም የሚታወቁት ግብጽ እና ጥንታውያን ቻንያውያን መሆናቸውን መረጃዎችም ይጠቁማሉ። ሽቶ ከ17ተኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ እንደነበርም እነዚሁ መረጃዎች ይጠቁማሉ፤ እነዚህ ሽቶዎች ደረጃ እና ዓይነት አላቸው፤ ዋጋቸውም እንዲሁ ይለያያል።

ሽቶን አብዝቶ ከመውደድ አንስቶ ከሌሎች ሀገሮች አምጥታ በመሸጥ ወደ ንግዱ ዓለም የገባቸው መሠረት ካሳ እንደምትለው፤ ሰዎች የሚቀቡት ሽቶ መለያ ጠረናቸው እስከሚሆን ድረስ በቅርባቸው ባሉ ሰዎች በሽቷቸው የሚታወቁበት ሁኔታ አለ። በተገኙበት ቦታም መልካቸው ሳይታወቅ በሽቶው ብቻ ማን እንደሆኑ እስከ ማወቅም ሲደረስ ይስተዋላል። ይህ ሊሆን የሚችለው እነዛ ሰዎች ለዓመታት አንድ ሽቶ ብቻ ምርጫቸው አድርገው ሲጠቀሙ ነው።

የሽቶ አድናቂዎች እና ወዳጆች ከመደርደሪያቸው ላይ ሽቶ በፍጹም የማይጠፋ አንድ እና ከዛም በላይ ሽቶ ያላቸው ናቸው። ለእለት ተዕለት ብለው የለዩዋቸው እና የክት ብለው የሚያስቀምጧቸው ሽቶዎችም አሏቸው። ለሽቶ ምንም ያህል ገንዘብ ቢያወጡ አይቆጫቸውም። በርካታ ሽቶዎች ቢኖራቸውም እንዲሁ አይጠሉም። ሽቶ በጣም ከመውደዳቸው የተነሳም ላይበረክትላቸው ይችላል፤ እነዚህ የሽቶ አፍቃሪዎች የሚጠጣ ሽቶ ቢኖር ሲሉ የሚናገሩበት ሁኔታም ያጋጥማል።

የእነዚህ ሽቶ ወዳጆች ሌላኛው ገጽታ ደግሞ ሰዎች የተቀቡት ሽቶ ምን ዓይነት እንደሆነም ማወቅ ይችላሉ። ሽቶውን የተቀባው የማያውቁት ከሆነና የተቀባውም የሚወዱትን ሽቶ ከሆነም ከማድነቅ ወደኋላ አይሉም። እነዚህ የሽቶ ወዳጆች አንድን ሰው በሚያዘወትረው



የሽቶ ዓይነት ወይንም ጠረን መለየትም ይችላሉ።

« ወደ ሥራው ከመግባቴ በፊት ሽቶ በጣም እወድ ነበር፤ ከዛ በኋላ ነው ለምን እራሴ እያመጣሁ አልሸጥም ብዬ መሸጥ የጀመርኩት። » የምትለው መሠረት፣ ብዙ ዓይነት ሽቶዎችን ከተለያዩ ሀገራት በማምጣት ለገበያ ታቀርባለች።

አንዳንዶች ትልልቅ ስም ያላቸው ሽቶዎች ጥሩ ጥራት እንዳላቸው ተደርጎ ሊታሰብ ይችላል ይላሉ። መሠረት ግን ትልልቅ ስም ያላቸው ሽቶዎች ሁሉ ጥሩ ላይሆኑ የሚችሉበት አጋጣሚ እንዳለ ትናገራለች፤ አንድ ሽቶ ደረጃውን የጠበቀ ነው እንዲባል ቢያንስ ሶስት መገለጫዎችን በመሠረታዊነት ማሟላት እንደ አለበት ከልምዷ ተነስታ ታብራራለች።

ትልልቅ ስም ያላቸው ሽቶዎች ከሚጋሩት መገለጫ አንዱ ሽቶውን ከተቀባነው በኋላ ቆዳችን ላይ የሚቆይበት የጊዜ ርዝማኔ ነው ስትል ጠቅሳ፣ ሽቶዎች ጥራት ካላቸው ግብዓቶች በሚሰሩበት ጊዜ መዓዛቸው ቆዳችን ላይ ረዘም ላለ ጊዜ ይቆያል ነው የምትለው። ስለዚህ አንድን ሽቶ ጥራቱን የጠበቀ ነው፤ አይደለም የሚለውን ለማረጋገጥ ተቀብተውት የሚቆይበትን ጊዜ ማየት እንደሚያስፈልግ መሠረት ጠቅሳለች። « የሽቶው መዓዛ ለበርካታ ሰዓታት፣ ከአንድ ቀንም በላይ አብሮን የሚቆይ እና ለአፍንጫም የማይረብሽ ከሆነ ጥሩ ሽቶ ነው ማለት ይቻላል» ስትል ትገልጻለች።

በተለምዶ ውስብስብ መዓዛ ያላቸው ሽቶዎች አንድ መዓዛ ብቻ ካላቸው ሽቶዎች የበለጠ ደረጃቸውን የጠበቁ ናቸው ይባላል። ይህ ግን ሁልጊዜ ትክክል ላይሆን እንደሚችል ማስታወስ ተገቢ ነው። ውስብስብነትን ከሽቶ ጥራት ጋር ማያያዛችን በቅንጦት ብራንዶችና በሀሰተኛ ብራንዶች መካከል ያለውን ልዩነት ለመጥቀስም ጭምር መሆኑንም ልብ ይላሉ። ብዙ ጊዜ የቅንጦት ሽቶዎች የሚጠቀሟቸው ጥራት ያላቸው ግብዓቶች በከፍተኛ ጥናትና የጥራት መለኪያዎች ውስጥ አልፈው ስለሚመጡ ደረጃቸውን የጠበቁ የሚሆኑበት እድል ሰፊ ነው።

ሽቶዎች ከትንሽ እስከ ትልቅ በተለያየ መጠን ተዘጋጅተው ለገበያ ይቀርባሉ። ሰዎች ሽቶ ከመግዛታቸው በፊት እዛው ተቀብተው እንዲሞክሩት ይደረጋል፤ አልያም ደግሞ ለሙከራ ተብሎ በትንሽ ብልቃጥ የተዘጋጀ ሽቶ ለደንበኞች ይቀርባሉ።

ሽቶን ለማዘጋጀት ለዚህ ተብለው የተለዩ ኬሚካሎች፣ አበባዎች ፣ ፍራፍሬዎች እና ግብዓቶች ያስፈልጋሉ። በርካታ ዓይነት ሽቶዎችን በማምረት የሚታወቁ ብራንዶች ሲኖሩ፣ ለወንዶች እና ሴቶች ተብለው የሚለዩ ሽቶዎችም አሉ። ሰዎች በአጠቃላይ ያላቸው የቆዳ ባህሪ የሚለያይ ሲሆን፣ ሙሉ በሙሉ በጾታ ባይለይም በአብዛኛው ሴቶች ለስለስ ያለ እና ጣፋጭ ጠረን ያለው ሽቶን ይመርጣሉ፤ ወንዶች ደግሞ ጠንከር ያለ መአዛ ያለው ሽቶ ይመርጣሉ።

የሽቶ ዋጋም እንደ ብራንዱ ዓይነት እንደሚለያይ የምታነሳው ወይዘሮ መሠረት የሚዘጋጁበት መንገድ ለሚኖራቸው ዋጋ አስተዋጽኦ ይኖረዋል ነው የምትለው። አንደኛ ደረጃ ሁለተኛ ደረጃ ተብለው በገበያው ላይ ይገኛሉ፤ ከአንድ መቶ ሺህ ብር በላይ ዋጋ ያላቸው ሽቶዎች በገበያ ላይ እንደሚገኙም ተናግራለች። «ብዙ ዓይነት ሽቶዎች ስላሉ ትክክለኛውን ሽቶ ተጠቃሚ ያልሆነን ሰው ለመለየት ያስቸግራል። » የምትለው ወይዘሮ መሠረት፣ እሷ ግን ሁሉንም ዓይነት ሽቶ እንደየሰዎች ምርጫ በሱቋ ውስጥ ትይዛለች። በጣም ውድ የሚባሉ ሽቶዎችን የሚጠቀሙ ሰዎች ጥቂት መሆናቸውን ተናግራ፣ እነዚህን መሰል ሽቶዎች ከማምጣቷ በፊት ከደንበኞቿ ግማሽ ክፍያ እንደምትቀበልም ነው ያስታወቀችው።

የፋሽን ኢንዱስትሪው ሁሌም ቢሆን ሽቶ ለማምረት ጥልቅ የሆኑ ጥናቶችን ያካሂዳል። አንድ ሽቶ ለገበያ ከመቅረቡ በፊት በቆዳ እና በሌሎች አካላት ላይ ጉዳት አለማድረሱ ለማረጋገጥ አስፈላጊ የደህንነት መመዘኛዎችን ማለፍ ግድ ይለዋል።

ሽቶን አብዝተው የሚወዱ እና የሚጠቀሙ ሰዎች የመኖራቸውን ያህል ቀጥታ ከቆዳቸው ጋር አገናኝተው ሲቀቡት አንዳንድ እንደ ሽፍታ ያሉ ምልክቶች የሚያጋጥሟቸው ሰዎችም አሉ፤ እነዚህም በጥንቃቄ በልብሳቸው ላይ ይቀባሉ። ሽቶዎች በተለያየ መንገድ ለገበያ የሚቀርቡ ሲሆን፣ አንደኛ ደረጃ የሆኑ ሽቶዎችን ለመግዛት በሽቶው ላይ ያለውን መግለጫ ወይንም ባርኮድ መመልከት ፣ የተሰራበትን ሀገር ማየት እና ሽቶው የተሰራባቸው ንጥረ ነገሮች ማንበብ ያስፈልጋል።

# ትዝብት/ ማረፊያ

## ከፀሐይ እና ከጨረቃ እምነትንና እውነትን ፍለጋ

**ከአንለይ ጥላሁን ምትኩ**

የሰው ልጅ በእምነትና በእውነት ላይ በመንገሥ (በመቆም) ህልውናውን የሚገነባ እና የሚተክል የማንነቱ ባለዳ ነው። አንድም ሰሪ፣ አንድም ተሰሪ ነው። የእምነቱም ፤ የእውነቱም ማረጋገጫ ወይም መግለጫ ሀሰሳው ሩቅና ጠናና ነው። ከሙከራዎቹ መካከል ጨረቃንና ፀሐይን አንድም ከሚሰጡት ጥቅም ፣ አንድም ከውበትና ሃይል (ብርሃን) ፣ በርሱ (በሰው) ሕይወት ላይ ያላቸው ከፍተኛ ተፅዕኖ ከልዕለ ሃይል አንፃር (ይተረጉማል) ተተርጉሟል።

በእኔ እምነት በቀደመው ዘመን ሚት ብቸኛው የእምነትና የእውነት ገላጭ የነበረ ይመስለኛል። በያዝነው የሠለጠነ ዘመን ደግሞ ሳይንስ የተጋድሎ ሜዳ በመሆን እውነትንም፤ እምነትንም ማስተንተኛው(መቅረጫ) ነው፤ ለሰው። ስለሆነም ሰው ሙዳይ፣ ሚትና ሳይንስ ደግሞ አለላ ናቸው። ታዲያ በቀላሉ የማይዘለቅበትን እልፍኝ በወፍ በረር ( ከዚህም፤ ከዛም) ሰበዞቹን ለመቃኘት እሞክራለሁ። ከጨለማ ገፋፊዋ፣ የተመስጦና የውበት ተምሳሌት ጨረቃ እንጀምር።

**ሉናር ቴዮሪ {Lunar Theory}** የጨረቃን እንቅስቃሴ ከክዋክብት አንፃር በሂሳባዊ ስሌት የመግለፅ (የማስቀመጥ) እሳቤ ነው። ይህ ቴዮሪ የሚመሰረተው አንድም በቀደመ የእውቀቱ ግስጋሴ (ማለትም ሂሳባዊ ስሌቶች፣ መሠረታዊ እሳቤዎች) እና መጠናዊ (quantitative)ስሌት፣ አሊጎሪዝም እና የጅኦሜትሪ ስዕላዊ መግለጫ (የጨረቃን አቀማመጥ ከጊዜ ስሌት ጋር የሚያሳይ) ናቸው።

ሉናር ቴዮሪ ከ2000 ዓመታት በላይ የዳበረ ታሪክ ያለው የምርምር ዘርፍ ነው። በመሆኑም ዘመናዊ ቅርፅ የያዘው ካለፉት ሶስት ክፍለ ዘመናት ወዲህ ነው። በአሁኑ ወቅት ለመሠረታዊ ምርምር እና ለቴክኖሎጂ ግብዓት (ዓላማ) አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል።

ሉናር ቴዮሪ ከጥንት እስካለንበት 21ኛው ክፍለ ዘመን ድረስ ባደረገው የእድገት ግስጋሴ ውስጥ የማይተካ ሙያዊ አስተዋፅኦ ያበረከቱ ምሁራን ከነሥልጣኔ ዘመናቸው ሰፍረው ይገኛሉ።

የተፈጥሮን ጉልበትም ሆነ ውበት በቋንቋና በስሌት ለመተርጎም የሚሄድበትን ርቀት ትዕምርታዊ ሆኖ አገኘቸዋለሁ። እውነቱንና እምነቱን ፈለገ ወይም አሰሰ የምለው ለዚህ ነው። ሰው የእውነቱ ባሪያ ነውና፤ ይፈልጋል። ይጨብጣል። ያፀናል። አንድም በልማድ ሰነድነት ፤ አንድም በንድፈሃሳብ ደረጃ ያሰርጻል። ይተክላል። ታዲያ የሚተክለው የራሱን እውነት ነው፤ የሚተረጎም እስከሆነ ድረስ።

**ሉናር ሚት(Lunar Myth)** የጨረቃ አምልኮት ወይም አምላክን የሚገልፁ ተረኮች ስያሜ ነው። በጥንታዊ ተረኮች አማካኝነት የጨረቃን እንቅስቃሴ፣ መጠን (ምዕራፎች)እና አቅጣጫ ሂደቶች የሚያስቃኝ አምልኮታዊ ሥርዓትም ነው።

**የጨረቃ አምላክ(Lunar Deity)** የጨረቃ አምላክ ወይም አማልክት የሚገለፅበት አምልኮ ሲሆን አንዳንዴ ደግሞ ልክ ሕይወት እንዳለው ሰው ሊቆጠር ይችላል። ይህ አምልኮ እንደየባህሉ ልዩነቶች የተለያዩ አገልግሎቶች እና ልማዶች(ሥርዓቶች) አሉት። ነገር ግን በአመዛኙ ተመሳሳይ ወይም ተቀራራቢ ናቸው። በጥንታዊ እምነቶች ውስጥ በርካታ የጨረቃ አማልክቶች የመገኘታቸው ምስጢርም ይኸው ልዩነት ነው።

አማልክቶቹ በተለያዩ ዓለማት በአይነትም ሆነ በፆታ የተለያዩ ናቸው። ለአብነትም የግሪኳ ሴት አማልክት «ሰሊን»(selene) እና የሮማዋ አማልክት «ሉና» (luna) እንዲሁም የቻይናዋ «ቻንጊ»(chang'e) ተጠቃሽ ናቸው። በተጨማሪም አፍሪካዊ ከሆኑ የጨረቃ አማልክት መካከል አቡክ «Abuk» ተጠቃሽ ሲሆን የእምነት (የሚት) ስሙ ደግሞ «ዲንካ» (Dink) ይባላል። የአማልክቱ «መለኮታዊ» ተግባርም ውልደት(fertility)፣ምግባር (morality) ፣ ፈጠራ(creativity) እና ፍቅር (love) ናቸው። የእምነቱ በረከቶች በመሆናቸው ለመመለኩ ምክንያቶች ናቸው።

**የጨረቃ ምዕራፎች እና ግርዶሽ** መሬት ላይ ሆነን ጨረቃን ካየናት በአንፀባራቂ «ግራጫ» ገፅታዋ ላይ የፀሐይ ብርሃን ተንፀባርቋል ማለት ነው። ይህ ማለት ጨረቃ ብርሃን አታመነጭም፤ ከፀሐይ ያረፈባትን ታንፀባርቃለች እንጂ ፤ ልክ መሬት ላይ በቀን እንደሚሆነው።

በወር ውስጥ የምንመለከተው የተለያዩ የጨረቃ ገፅታዎች «የጨረቃ ምዕራፎች» (lunar phases) ይባላል። የዚህ ምክንያቱ ደግሞ የጨረቃ ምህዋር (orbits) በመሬት ዙሪያ እና የመሬት ምህዋር (ንፍቀ ክበብ) ተፅዕኖ በፀሐይ ዙሪያ ስለሆነ ነው። ይህ ሁሉ የእንቅስቃሴ ውጤት ነው።

በጨረቃ ግርዶሽ ወቅት መሬት በፀሐይና በጨረቃ መካከል ትሆናለች። ይህም የፀሐይን ብርሃን በመገደብ (በማስቀረት) ጨረቃ በጥቅጥቅ ጨለማ እንድትዋጥ ያደርጋታል። አንዳንዴ ደግሞ የመሬት ጥላ ጨረቃን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ሊጋርዳት ይችላል። ይህም ሂደት በሁለት ይከፈላል። እነሱም፡ - ሙሉ ግርዶሽ እና ከፊል ግርዶሽ ናቸው። እያንዳንዳቸውን እንደሚከተለው እንመልከት።

**ሀ.ሙሉ ግርዶሽ (Total lunar eclipse)፡-**ጨረቃ እና ፀሐይ ከመሬት በተቃራኒ አቅጣጫ ሲሆኑ የሚፈጠር የግርዶሽ አይነት ነው። ማለትም መሬት የፀሐይን ብርሃን ሙሉ በሙሉ በመጋረድ ጨረቃ ላይ ጥላዋን ታጠላለች።

**ለ.ከፊል ግርዶሽ (partial lunar eclipse)፡-**የመሬት ከፊል ገፅታ ብቻ ጥላውን በጨረቃ ላይ ሲያሳርፍ የሚፈጠር የግርዶሽ አይነት ነው።

ሉናር የጊዜ አቆጣጠር ተምሳሌት ከሆኑት መካከል የቻይና ሉናር የዘመን አቆጣጠር (Chinese Lunar Calendar) አንዱ ነው። ከሌሎች የሚለየው የፀሐይን ሥርዓት ደርቦ መጠቀሙ ነው። የወር ለውጡ የሚመሠረተው አንዴ በፀሐይ ሌላ ጊዜ ደግሞ በጨረቃ ሥርዓቶች ላይ ነው። የወሩ ርዝማኔ የሚመሠረተው በሁለቱ አዲስ ጨረቃዎች መካከል ባለው የጊዜ ርቀት አማካኝነት ነው። ይህ የጨረቃ ወር ስያሜ የተወሰደው ከፀሐይ ሥርዓት(solar system) ነው።

**የፀሐይ ሚት (Solar Myth)** የፀሐይ እምነት ወይም አምላክ ተረክ (ሚት) ነው። ይህም በባህላዊ ተረኮች መነሻነት የፀሐይን እንቅስቃሴ (motion)፣ተፅዕኖ እና አቅጣጫ መግለጫ ሙያም ነው። ይህን እሳቤ የሚያጠና የሳይንስ ዘርፍ ሶላሪዝም(solarism) ይባላል። ሶላሪዝም የጥንት ፎክሎራዊ ተረኮችን እና ሌጀንዶችን መነሻ በማድረግ የተፈጥሮንና በዋናነት የፀሐይን እንቅስቃሴ፣ መጠን የሚመረምር፣ የሚፈክርና የሚተነትን የጥናት መስክ ነው።

እንደ «ሙለር»(Müller's) ገለፃ ከሆነ ሶላር ሚት የተገኘው ወይም የተወለደው ከኢንዶ-ኤሮፖ የቋንቋ ጥናት ነው። በሙለር እምነት «ሳንስክሪት» ቋንቋ በርካታ የፀሐይ አማላክትን ስሞች ወይም ስያሜዎች የሚጠቀም ሲሆን ይህም ሁኔታ በሌሎች ቋንቋዎች በተመሳሳይ መልኩ አገልግሎት ላይ መዋሉን ታዝቧል። ይህም የሚትን ድንበር ዘለል (ተሻጋሪነት) ባህሪ ጠቋሚ መሆኑን ታዝቧል።

**የፀሐይ አምላክ(Solar Deities)** በፀሐይ የተወከለ አምላክ ወይም አማልክት ሲሆን የሃይል እና የጥንካሬ ተምሳሌት ነው። የፀሐይ እምነት ወይም አምልኮ በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ በተለያየ መንገድ ወይም ስልት የተገለጠ እውነታ ነው። ለአብነትም በአፍሪካ እንደ «ማጀክ»(magec) (Tenerife goddess of the sun and Light) እና «ኢንያንጋ» ደግሞ በበርካታ ሕዝብ ዘንድ የጨረቃ አምላክ ተደርገው ይመለካሉ። እንዲሁም በግብፅ ሚቶሎጂ ውስጥ «ኬፐሪ»(kheori) ደግሞ የፀሐይ መውጫ ፣ የፈጠራ እና የአዲስ ሕይወት ተምሳሌት(አምላክ) ሆኖ ይመለካል። እንዲሁም «ራ»(Ra) የፀሐይ አምላክ ነው። ከፀሐይ አማልክቶች መካከል ጥቂቶቹ የሚከተሉት ተጠቃሽ ናቸው።

አፍሪካዊ የሆኑት፡- አንያንው (Anyanwu)፣ ማጀክ ( Magec)፣ እንነጋ (iNyanga) እና የዙሉ ሕዝቦች ናቸው። እንዲሁም ራ (Ra) በግብፆች ዘንድ የፀሐይ አምላክ በመባል ይመለካል። ሰክመት (Sekhmet) ደግሞ የጦር እና የፀሐይ አምላክ ተደርጎ የሚታመንበት ነው።

በአጠቃላይ ሉናር እና ሶላር ሚት ቴዮሪ ለበርካታ የሙያ ዘርፎች ግብዓት የሚሆኑ እሳቤዎች፣ ምልከታዎች ያቀፈ ነው። በድህረ ዘመናዊነት የሳይንስ ምርምር አማካኝነት የሙያዎችን ድንበር የጣሰ እና በከፍተኛ ደረጃ ያስተሳሰረ እሳቤ ነው፤ ሚት። የተለያዩ ተረኮች ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ግለሰባዊ ፋይዳ እንደ ሳይኮሎጂ፣ አንትሮፖሎጂ፣ ሶሾሎጂ እና ፍልስፍና እንዲሁም ነገረመለኮት ወዘተ...ያሉ ሙያዎች ጉዳይ (ተጠኝ) የሆነ ሙያ ነው።

ሚት በባህሪው ምናባዊ ተረክ በመሆኑ ኩሸት ነው። ይህ ደግሞ ተምሳሌታዊ በመሆኑ ከዘወትራዊ ኑሮ የራቀ እና የጠነነ ነው። በመሆኑም ተረኮቹ እውነት ሆነው መተረካቸው የእምነት መጣረስ ያስከትላሉ የሚል እይታ አለኝ። የሃይማኖቶቹ አጀማመርም ሆነ ቀኖና መሠረት ማጠየቂያም ጭምር ነው። ማለትም ከሚትነት ወደ ዶግማና ቀኖና የተለወጡ የአምልኮ ተቋምነት የተቀየሩት በሂደት ነው። ያም ሆኖ ሚታዊ ተረክ የታጨቀባቸው የአምልኮ ሰነዶች አሏቸው።

አዲስ ዘመን | ሰኞ ነሐሴ 6 ቀን 2016 ዓ.ም

# ዓለም አቀፍ

## አሜሪካ ለሳኡዲ አረቢያ በሚደረግ የመሣሪያ ሽያጭ ላይ ጥላው የነበረውን እግድ ለማንሳት ወሰነች

በጋዜጣው ሪፖርተር



አሜሪካ ለሳኡዲ አረቢያ በሚደረግ የመሣሪያ ሽያጭ ላይ ጥላው የነበረውን እግድ ለማንሳት ወሰነች።

የፕሬዚዳንት ባይደን አስተዳደር አሜሪካ ለሳኡዲ አረቢያ የጦር መሣሪያ እንዳትሸጥ ጥሎት የነበረው ማዕቀብ ለማንሳት መወሰኑን የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚስቴር አስታውቋል።

አሜሪካ ማዕቀቡን የጣለችው ሳኡዲ አረቢያ በየመን ጦርነት የነበራት ሚና እንዲቀንስ ጫና ለማድረግ ነበር። አንድ ከፍተኛ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ባለሥልጣን እንደተናገሩት ከመሬት ወደ አየር የሚተኮሱ ሚሳይሎችን ለሳኡዲ የመሸጥ እግድ መነሳቱን ማረጋገጣቸውን ሮይተርስ ዘግቧል።

ባለስልጣኑ እንደገለጹት አሜሪካ ሁኔታዎችን እየገመገመች እና ከኮንቬንሽናል አርምስ ትራስፈር ፖሊሲ ጋር የማይቃረን መሆኑን እያረጋገጠች ለሳኡዲ የጦር መሣሪያ ታስተላልፋለች።

አስተዳደሩ እግዱን ለማንሳት መወሰኑን ለኮንግረሱ ማስረዳቱን የኮኔግሬሽናል ረዳት ተናግረዋል።

“ሳኡዲዎች የሚመለከታቸውን አድርገዋል፤ ስለዚህ በእኛ በኩል የሚጠበቅብንን ለማድረግ ተዘጋጅተናል” ሱሉ አንድ ከፍተኛ የባይደን አስተዳደር ባለሥልጣን ገልጸዋል።

በአሜሪካ ሕግ መሠረት ዋና ዋና ዓለምአቀፍ የመሣሪያ ሽያጭ ስምምነቶች ከመጽደቃቸው በፊት በኮንግረስ ወይም በተወካዮች ምክርቤት ቀርበው መጽደቅ ይኖርባቸዋል።

የዲሞክራት እና የሪፐብሊካን ተወካዮች ሳኡዲ አረቢያ በየመን እያደረገች ባለው ዘመቻ ንጹሃን መገደላቸውን እና የሠብዓዊ መብቶች ጥሰቶች መፈጸማቸውን በመጥቀስ ባለፉት ዓመታት ለሳኡዲ በሚደረገው የጦር መሣሪያ ሽያጭ ላይ ስጋታቸውን ሲገልጹ ቆይተዋል።

ነገርግን ይህ ተቃውሞ ሀማስ በእስራኤል ላይ ከባድ የተባለውን ጥቃት ማድረሱን ተከትሎ በመካከለኛው ምስራቅ ብጥብጥ ከተነሳ በኋላ ቀዝቀዝ ሊል ችሏል።

የአስተዳደሩ ባለሥልጣን እንደናገሩት ሳኡዲ እና የየመኖቹ ሀውቲዎች በተመድ አማካኝነት በፈረንጆቹ ሚያዝያ 2022 የተኩስ አቁም ስምምነት ላይ ከደረሱ በኋላ ሳኡዲ አረቢያ በየመን ላይ ስትፈጽም የነበረውን የአየር ጥቃት ያቆመች ሲሆን ሀውቲዎችም ወደ ሳኡዲ ግዛት መተኮሳቸውን አቁመዋል።

የየመን ጦርነት ኢራን እና ሳኡዲ አረቢያ ከሚያደርጓቸው በርካታ የእጅ አዙር ጦርነቶች አንዱ እንደሆነ ይጠቀሳል።

በሳኡዲ አረቢያ የሚደገፈውን የየመን መንግሥት በፈረንጆቹ 2014 መጨረሻ ከሰንዓ ያነሱት ሀውቲዎች ከ2015 ጀምሮ በሳኡዲ አረቢያ የሚመራውን ጥምር ኃይል ሲዋጉ ቆይተዋል። ጦርነቱ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ የመናውያን እንዲገደሉ እና 80 በመቶ የሚሆነው የየመን ሕዝብ በርዳታ ላይ ጥገኛ እንዲሆን አድርጎታል።

ባይደን በፈረንጆቹ 2021 ለሳኡዲ በሚደረግ የጦር መሣሪያ ሽያጭ ላይ እግድ የጣሉት፤ ሳኡዲ በየመን በምታደርገው ዘመቻ በንጹሃን ላይ ከፍተኛ ግድያ አድርሳለች በሚል ምክንያት ነበር።

## የትራምፕ የምርጫ ቅስቀሳ ቡድን ኢራንን በመረጃ ምንተፋ ከሰሰ

በጋዜጣው ሪፖርተር



የዶናልድ ትራምፕ የምርጫ ቅስቀሳ ቡድን ኢራንን በመረጃ ምንተፋ ከሰሰ።

የሪፐብሊካን ፓርቲ የቅስቀሳ ቡድኑ የኢራን መንግሥት ሚስጢራዊ መረጃዎችን ሰርቆ አሠራጭቷል የሚል መግለጫን ቢያወጣም ቀጥተኛ ማስረጃን ግን አላቀረበም።

ቴህራንን የሚከሰው መግለጫ የወጣው ፖለቲኮ በሀምሌ ወር ከማይታወቁ ምንጮች በትራምፕ የምርጫ ቅስቀሳ ዙሪያ ታማኝ ሰነዶች ደርሶኛል የሚል ዘገባን ባወጣ ማግስት ነው።

ትራምፕ ምክትላቸው ሆነው እንዲወዳደሩ በመረጧቸው ጄዲ ቫንስ ዙሪያም የተለያዩ መልዕክቶች እንደደረሱት ፖለቲኮ ዘግቦ ነበር።

የትራምፕ የምርጫ ቅስቀሳ ቡድን “እነዚህ ሰነዶች ለአሜሪካ አፍራሽ አመለካከት ካላቸው የውጭ ሃይሎች በሕገወጥ መንገድ ነው የተገኙት፤ በ2024ቱ ፕሬዚዳንታዊ ምርጫ ጣልቃ በመግባት የዴሞክራሲያዊ ሂደቱን ለማወክ ያለሙ ናቸው” ብሏል።

የቀድሞው ፕሬዚዳንት ዶናልድ ትራምፕ በራሳቸው የማህበራዊ ትስስር ትሩዝ ሶሻል ባወጡት መግለጫም የምርጫ ቅስቀሳ ቡድናቸው ድረገጽ በኢራን የመረጃ ዘራፊዎች መጠቃቱን ገልጸዋል።

የተሰረቁት ሰነዶች ማንኛውም ሰው ሊያገኛቸው የሚችሉ ናቸው ያሉት ትራምፕ፥ የመረጃ ስርቆቱ እንዴትና በየትኛው የመረጃ መንታፊ ቡድን እንደተከናወነ ግን በዝርዝር ከመናገር ተቆጥበዋል።

የትራምፕ የምርጫ ቅስቀሳ ቡድን ማይክሮሶፍት ባለፈው ዓርብ ያወጣውን መረጃም አጣቅሶ አቅርቧል።

የማይክሮሶፍት ተመራማሪዎች ከኢራን ጋር ግንኙነት ያለው የመረጃ መንታፊ ቡድን በሰኔ ወር ከህዳሩ ፕሬዚዳንታዊ ምርጫ ጋር ግንኙነት ያላቸው የከፍተኛ ባለስልጣናት አካውንቶችን ሰብሮ ለመግባት መሞከሩን መግለጻቸው የሚታወስ ነው።

የማይክሮሶፍት መረጃ የትኞቹ የአሜሪካ ባለሥልጣናት በመረጃ መንታፊ ቡድኑ ኢላማ እንደተደረጉ ግን አልጠቀሰም ይላል የሬውተርስ ዘገባ።

በመንግሥታቱ ድርጅት የኢራን ቋሚ መልዕክተኛ ግን “የኢራን መንግሥት በቀጣዩ የአሜሪካ ምርጫ ጣልቃ የመግባትም ሆነ መረጃዎችን የመመንተፍ ፍላጎት የለውም” የሚል መግለጫ አውጥቷል።

ቴህራን ለሚቃጡ ጥቃቶች ምላሽ የመስጠትና የመከላከል የሳይበር አቅም ማዳበሯን በመጥቀስም በሌሎች ሀገራት ላይ ግን የሳይበር ጥቃት መፈጸም እንደማትፈልግ አብራርቷል።

በሥልጣን ዘመናቸው ከኢራን ጋር ግንኙነታቸውን ያሻከሩት ትራምፕ በሀምሌ ወር የተፈጸመባቸው የግድያ ሙከራ ከቴህራን ጋር ግንኙነት እንዳለው ሲኤንኤን ባለፈው ወር ባወጣው ዘገባ ማመላከቱ የሚታወስ ነው።

ቴህራን ግን በትራምፕ የግድያ ሙከራ ሴራ እጇ አለበት በሚል የቀረበባትን ክስ ማጣጣሏ አይዘነጋም።

# የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ፖሊሲው መነሻና መድረሻ

ቴዎድሮስ ፈሬ ልሶር (የኩሽ አሽክታብ)

የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራም ተግባራዊ ከሆነ ውሎ አድሯል። በነዚህ ቀናቶች ውስጥ የተለያዩ ሃሳቦች መነሳታቸው አልቀረም። የኢኮኖሚ ማሻሻያውን ተከትሎ የኢትዮጵያ ብሔራዊ የሀገሪቱን የውጪ ምንዛሪ አስተዳደር ሥርዓት ማሻሻያ በማድረግ ሂደቱ በመቀላጠፍ ላይ ይገኛል።

በሥራ ላይ የዋለው ይህ ማሻሻያ ፕሮግራም ሀገራችን ኢትዮጵያን በሁሉም ዘርፍ ተወዳዳሪ ወደሆነና በገበያ ላይ በተመሰረተ የውጪ ምንዛሪ ሥርዓት እንደሚያሸጋግራት እና በኢኮኖሚው ውስጥ ለረጅም ጊዜ ገዝፎ የሰነበተውን የማክሮ ኢኮኖሚ አለመረጋጋት መዛባት እንደሚያስተካክል እምነት ተጥሎበታል።

የውጪ ምንዛሪ አስተዳደር ማሻሻያው በአዲሱ የውጪ ምንዛሪ መምሪያ መሠረት ተግባራዊነቱ የሚቀጥል ሲሆን ይህ የምንዛሪ አስተዳደር ሥርዓት ማሻሻያ በሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ መርሀ ግብር ላይ የተመሰረተ በቀጣይም በሥራ ላይ ከሚውሉ ሰፊ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያዎች መሀል አንዱ ነው። ዋና አላማውም ቀጣይነት ባለው፣ ሰፊና ተደራሽነቱ የገዘፈ፣ ሁሉን አሳታፊ የኢኮኖሚ እድገትን ማረጋገጥ ነው።

የውጪ ምንዛሪ አስተዳደር ውጤት ተኮር በሆነ አላማ የተለያዩ የፖሊሲ ማሻሻያዎችን አድርጓል። የፖሊሲ ማሻሻያው በጥናትና ምርምር የተደገፈ ያረጀውን የሚቀይር፣ ለሀገር የተሻለ የለውጥ አቅጣጫን የሚቀይስ፣ በውስጥና በውጪ የምንዛሪ አስተዳደር ላይ አዲስና አዋጪ ሕግጋትን የደነገገ ነው። ከማሻሻያዎቹ መሀል.. የውጪ ምንዛሪ አስተዳደር ሥርዓቱ የውጪ ምንዛሪ ተመን በባንኮችና በደንበኞች መፈቃቀድ ወደሚወሰንበት የገበያ ሥርዓት ተሸጋግሯል።

በአዲሱ የማሻሻያ ፖሊሲ የውጪ ምንዛሪን ለብሔራዊ ባንክ የማስተላለፍ ግዴታ ቀርቷል። ላኪዎችና ንግድ ባንኮች ያፈሩትን የውጪ ምንዛሪ ለራሳቸው ማስቀረት ሲችሉ ይህም ለግሉ ሴክተር የሚሰጠውን የውጪ ምንዛሪ በበለጠ ያሻሽለዋል። ቀደም ሲል በ38 የገቢ ንግድ ሸቀጦች ላይ ተጥሎ የነበረው እግድ ተነስቶ ምርቶቹ ወደሀገር የሚገቡበት አቅጣጫ ተቀምጧል። ወደ ውጪ የሚደረግ የካፒታል ሂሳብ ፍሰት እንደ በፊቱ የተገደበ ሲሆን የውጪ ምንዛሪ ገበያው ለገቢ ሸቀጦችና አገልግሎቶች ግን ነፃ ሆኗል።

ምርቶችን ወደ ውጭ የሚልኩ ነጋዴዎች ካፈሩት የውጪ ምንዛሪ ገቢ ለራሳቸው ያስቀሩት የነበረውን 40 ፐርሰንት ወደ 50 እድገት አሳይቷል። ከማሻሻያው በፊት ባንኮች ለተለያዩ የገቢ ሸቀጦች የሚጠቀሙበት የውጪ ምንዛሪ አሰራርና አደላደል ደንቦች ቀሪ ሆነዋል። በሥራ ላይ ካሉና በባንኮች ከተቋቋሙ የውጪ ምንዛሪ ቢሮዎች በተጨማሪ ባንክ ያልሆኑ የግል የውጪ ምንዛሪ ቢሮዎች እንዲቋቋሙ አቅጣጫ ተቀምጧል። በገበያ ዋጋ የውጪ ምንዛሪ ጥሬ ገንዘብ እንዲገዙና እንዲለውጡ የሥራ ፈቃድ ተችሯቸዋል።

ሌላው የማሻሻያው አካል የሆነው ሸቀጦችን በፍራንኮ ቫሉታ ወደ ሀገር ውስጥ ያለማስገባት የተጣሉ ክልከላዎች በአዲስ ሥርዓት በቅርቡ መታየታቸው ነው። የውጭ ተቋማት፣ በውጭ ኢንቨስተሮች እና በትውልደ ኢትዮጵያውያን (ዲያስፖራ) የተከፈቱ የውጪ ምንዛሪ ሂሳቦችን አስተዳደር የሚመለከቱ በርካታ ሕጎች ላልተዋል። እንዲሁም በሀገር ውስጥ ነዋሪ የሆኑ ሰዎች ከውጭ የሚላክላቸውን ሀዋላ፣ በውጪ ምንዛሪ የሚከፈል ደሞዝን፣ የኪራይ ገቢን እና ሌሎች ገቢዎችን የሚያስቀምጡባቸውን የውጭ አገልግሎት ክፍያዎችን እንዲፈጽሙ ተፈቅዷል።

የግል ኩባንያዎች ወይም ባንኮች በሚወስዷቸው የውጪ ብድሮች ላይ ይከፍሉት የነበረው የወለድ ተመን ጣሪያ ተነስቷል። መመዘኛውን የሚያሟሉ የውጭ ኢንቨስተሮች በኢትዮጵያ ሰነድ ሙዓለ ንዋይ ገበያ (Ethiopian Securities Exchange) እንዲሳተፉ ተደርጓል። በልዩ የኢኮኖሚ ዞኖች ውስጥ የሚሰሩ ኩባንያዎች የውጪ ምንዛሪ ገቢያቸውን ሙሉ በሙሉ ለራሳቸው መያዝን ጨምሮ ልዩ የውጪ ምንዛሪ አጠቃቀም መብት ተሰቷቸዋል።

ከኢትዮጵያ ወደ ውጭ ሀገራት የሚጓዙ ወይም ወደ ኢትዮጵያ የሚገቡ መንገደኞች ሊይዙ በሚገባ የውጪ ምንዛሪ ጥሬ ገንዘብ መጠን ላይ ተጥለው የነበሩ የተለያዩ ደንቦች ላልተዋል። ከላይ የተዘረዘሩት ከአስር በላይ የሆኑ የማሻሻያ ፖሊሲዎች ቀጣዩንና በተስፋ የሚጠበቀውን የሀገራችንን እድገት የሚወስኑ እንዲሁም ከቀረው ዓለም ጋር ያለንን ግንኙነት የበለጠ የሚያጠነክሩ እንደሚሆኑ ይታመናል።

እኒህ የማሻሻያ ፖሊሲዎች የአስር ዓመቱን የመንግሥት የልማት መሪ እቅድና ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርም ፕሮግራምን በመሳሰሉ ወሳኝ ሰነዶች ውስጥ ከሰፈሩት የመንግሥት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ጋር የተቀናጁ እንዲሁም ከሌሎች የእቅድ ዘርፎች ጋር መሳ ለመሳ የቆሙ ናቸው። የሪፎርም ሰነዶቹ ኢኮኖሚው እየተወሳሰበና እያደገ ሲሄድ ሀገሪቱ በሂደት በገበያ ላይ ወደተመሰረተ የውጪ ምንዛሪ ሥርዓት እንደምትሸጋገር የሚመሰክሩ ናቸው።

የውጪ ምንዛሪ አስተዳደር ማሻሻያ ያስፈለገበት ዋነኛ አላማ በበፊቱ ነባር ሥርዓት የነበረውን ተግዳሮት ለመቅረፍ እንዲሁም በጥቂት ተግዳሮት የተሻለ ሀገራዊ ተስፋን ለማምጣት ከመሻት እንደሆነ እሙን ነው። ቀደም ባለው ጊዜ ከአምራቹ ዘርፍ ይልቅ ጥቂት ሕገ ወጦችና ደላሎች ተጠቃሚ የሚሆኑበት፣ ስር የሰደደ የውጪ ምንዛሪ እጥረት እንዲከሰት መንገድ የቀደደ ነበር። በዚህም ሳቢያ በርካታ የንግድ ድርጅቶችና ባለሀብቶች ተጎጂ ሆነዋል። የውጪ ንግድና የፋብሪካ ምርቶችን ለማስፋፋት፣ የውጪ ኢንቨስትመንትን ለመሳብና የሀገሪቱን የውጪ ምንዛሪ አሃዝ ለማሳደግ የተቀመጡ ፖሊሲዎችንና ውጤታማነት ጥያቄ ውስጥ አስገብቶታል።

ከዚህ አኳያ በአዲሱ የፖሊሲ ማሻሻያ መሠረት በገበያ የሚወሰን የውጪ ምንዛሪ ሥርዓት በርካታ ኢኮኖሚያዊ በረከቶች አሉት። ለአብነት ብንመለከት የውጪ ምንዛሪ ገቢ በሚያስገኙ ዘርፎች ላይ የተሰማሩ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያንን ይጠቅማል። ወደውጭ የሚላኩ እንደቡና፣ ሰሊጥ፣ የቅባት እህሎች፣ አበባ፣ አትክልትና ፍራፍሬ፣ ጫት የመሳሰሉ ምርቶችን የሚያመርቱ በሚሊዮን የሚቆጠሩ አርሶ አደሮች ተጠቃሚ የሚያደርግ ነው።

የቁም እንስሳትንና የሥጋ ተዋጽኦችን ለውጭ ገበያ የሚያቀርቡ አርብቶ አደሮችና ነጋዴዎች፣ በወጪ ንግድ ዘርፍ የተሰማሩ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ የፋብሪካ ሠራተኞች፣ በማዕድን ፍለጋ ላይ የተሰማሩ አያሌ ዜጎችና አምራቾች፣ በሆቴልና ቱሪዝም ዘርፎች ላይ የሚሰሩ በሺህ የሚቆጠሩ ነጋዴዎች፣ በውጭ ሀገር ከሚኖሩ ዘመድ፣ ጓደኛ የውጪ ምንዛሪ የሚላክላቸው በሚሊዮን የሚሰሉ የሀዋላ ተጠቃሚዎች በተጨማሪም ከውጭ ሀገር ገንዘብ ፈሰስ የሚደረግላቸው በመቶዎች የሚቆጠሩ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና የግል ተቋማት እንዲሁም ሌሎች አካላት የዚህ ማሻሻያ ተጠቃሚዎች ይሆናሉ።

ሌላው የውጪ ምንዛሪ ማሻሻያው ሊያስገኝ የሚችለው ጥቅም የሀገሪቱ የውጪ ምንዛሪ ገቢ በተገቢው ሁኔታ ወደሀገር ውስጥ መግባቱንና ለዜጎችና ለአምራች ዘርፎች ጥቅም መዋሉን ለማረጋገጥ ያግዛል። ቀደም ሲል የነበረው የውጪ ምንዛሪ ፖሊሲ የኮንትሮባንድ ንግድን የሚያበረታታ፣ ላኪዎችና አስመጪዎች የሸቀጦችን ዋጋ ከሕግ አግባብ ውጭ ከፍ ወይም ዝቅ እንዲያደርጉ እድል የሚሰጥ፣ የካፒታል ሽሽትን የሚያበረታቱ፣ ሀገር ማግኘት የሚገባትን ጥቅምና የውጪ ምንዛሪ ገቢ እንዳታገኝ እክል የሚፈጥሩ ነበሩ። በተሻሻለው አዲሱ የፖሊሲ ሥርዓት እነዚህ ሁሉ የሚስተካከሉበት ከሕግ አግባብ ውጭ ያሉ አካሄዶች የሚተረቁበት ነው።

ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ የሚያመርቱ ኢንዱስትሪዎችን በማበረታታት የማምረት አቅማቸውን እንዲያሳድጉና እንዲያስፋፉ የሚያበረታታ መሆኑ ነው። እንዲሁም ኢትዮጵያ ታምርት በተሰኘው የሀገር በቀል እሳቤ እቅድ ውስጥ ተሳታፊ የሆኑ ኢንዱስትሪዎች የዚህ እድል ተጠቃሚ ይሆናሉ። ከቅርብ አመታት ወዲህ የግሉን ዘርፍ ለማሳደግና ኢኮኖሚውን ለማነቃቃት እንዲሁም ኢኮኖሚውን ለውጭ ኢንቨስተሮች ክፍት እና ምቹ ለማድረግ እየተሄደበት ያለውን እንቅስቃሴ የሚደግፍና የሚያበረታታ መሆኑ ሌላው የማሻሻያ ፖሊሲ በረከት ነው። ቀደም ሲል ለግል ዘርፉ ዝግ የነበሩ እንደ ቴሌኮም፣ ሎጀስቲክስ፣ ባንክ፣ ካፒታል ገበያ፣ ጅምላና ችርቻሮ ንግድ የመሳሰሉ ዘርፎችን ክፍት ማድረግ አብሮ የሚነሳ ጉዳይ ነው።

የውጪ ምንዛሪ ማሻሻያው የውጭ ኢንቨስተሮችን በመሳብ የውጭ የቀጥታ ኢንቨስትመንትን በማሳደግ፣ የንግድ ሥርዓታችንንም ከአጎራባችና ከአቻ ሀገራት ጋር የተስማማ እንዲሆን በማሳለጥ በኩል ሚናው የጎላ ነው። ሀገራችን የውጪ ምንዛሪ እጥረት ሰለባ ናት። ከሕዝብ ብዛት፣ ከሰው ኃይል፣ ከግብዓት፣ ከተሻሻለ ሎጀስቲክ፣ ከኃይል አቅርቦት፣ ከአየር ሁኔታና ከማዕድን አኳያ በብዙ መልኩ ለኢንቨስትመንት ምቹና ሳቢ ሀገር ብትሆንም በአስቸጋሪ የውጪ ምንዛሬ ፖሊሲ ሳቢያ ግን በሚፈለገው መልኩ ተጠቃሚ ስትሆን አይታይም። የውጪ ምንዛሪ የፖሊሲ ማሻሻያ ደግሞ ይሄን ተግዳሮት በመቅረፍ ረገድ አዋጪ ነው።

በኢኮኖሚው ውስጥ ተሰግስገው ያሉ ኢመደበኛነትንና ሕገ ወጥነትን ሲያበረታቱ የቆዩ የንግድ አሰራሮችን ያስተካክለው። በግርድፉ ስናየው የምንዛሪ ማሻሻያው የውጪ ምንዛሪ እጥረትን የሚቀርፍ፣ የንግድ ተወዳዳሪነትን የሚያበረታ፣ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን ለመሳብና የግሉን ዘርፍ ለመደገፍ ያለውን ተነሳሽነት በማጠንከር የላቀ አስተዋጽኦ ያደርጋል።

የፖሊሲ ማሻሻያው ዝም ብሎ አሊያም በችኮላ ወደትግበራ የገባ ሳይሆን በሰፊ ቅድመ ዝግጅት ራሱን አዘጋጅቶ ወደሥራ የገባ ነው። እንደ መጀመሪያ አንዳንድ ተግዳሮቶች የሚኖሩ ቢሆንም ለነዚህ ምላሽ የሚሆኑ የመፍትሔ አማራጮችንም ይዟል። በተለይም አነስተኛ ገቢ ባላቸው ዜጎች ላይ ሊደርስ የሚችለውን የኑሮ ጫና ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ከደሞዝ ጭማሪ ባለፈ እንደ ነዳጅ፣ ማዳበሪያ፣ መድኃኒትና የምግብ ዘይትን በመሳሰሉ ከውጭ በሚገቡ መሠረታዊ ሸቀጦች ላይ ድጎማ በማድረግ እጁን አገብቷል።

ሌላው በከፍተኛ የዋጋ ንረት ሕይወትን ማሸነፍ ላቃታቸው የመንግሥትን የበጀት ጉድለት በማይጎዳ መልኩ የደሞዝ ጭማሪ መደረጉ ነው። በተጨማሪም በከተማና በገጠር ለሚገኙ አነስተኛ ገቢ ላላቸው ወገኖች በሴፍቲኔት በኩል ተጠቃሚ የሚሆኑበት መንገድ ተመቻችቷል። ከዚህ ጋር አብሮ የሚነሳው ለማህበራዊ ወጪ እና ለእዳ ክፍያ የሚሆን ገንዘብ በርዳታ መልክ መገኘቱ ነው። ከነዚህ የመፍትሔ አማራጮች ጎን ለጎን በገንዘብና በፊስካል ፖሊሲዎች መካከል ውህደትን ለመፍጠር ብሔራዊ ባንክና የገንዘብ ሚኒስቴር ትብብር ፈጥረዋል።

በውጪ ምንዛሪ ማሻሻያ ፖሊሲ ዙሪያ እንደማጠቃለያ ሊነሳ የሚችለው ከአተገባበሩ ጋር አብሮ የሚነሳው ተጠባቂው የኢኮኖሚ እድገታችን ነው። ከሌሎች አጋዥ የማክሮ ኢኮኖሚ እሳቤዎች ጋር ተሰልፎ በቀጣይ የተሻለችን ኢትዮጵያ እንድናይ እድል ይፈጥራል። በዓለም አቀፉ የገንዘብ ድርጅት የማክሮ ኢኮኖሚ ትንታኔ መሠረት በሀገራችን በመተግበር ላይ ያሉ የማሻሻያ ፖሊሲዎች እድገትን የሚያፋጥኑ፣ የዋጋ ንረትን የሚያላሉ፣ የፊስካል አቅምን የሚያሳድጉ፣ የወጪ ንግድና የውጭ ኢንቨስትመንትን በማስፋፋትና የሀገሪቱን ዓለም አቀፍ የውጪ ምንዛሪ መጠባበቂያ ክምችትን በማሳደግ ረገድ ከፍተኛ ሚና አለው ተብሏል።

በዚህ ትንታኔ መሰረት በማሻሻያ ፖሊሲዎቹ በኩል በሚቀጥሉት አራት ዓመታት የሀገራችን ኢኮኖሚ በአማካይ 8 በመቶ ያክል እንደሚያድግ፣ የዋጋ ንረቱ ወደአስር በመቶ ዝቅ እንደሚል፣ የታክስ ገቢ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት አኳያ ያለው ድርሻ 11 በመቶ እንደሚሆን፣ የመንግሥት እዳ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት 35 በመቶ ዝቅ ያለ ድርሻ እንደሚኖረው፣ የወጪና ገቢ ንግድ ዋጋ ወደ 20 ቢሊዮን ዶላር እንደሚያድግ፣ ቀጥታ የውጪ ኢንቨስትመንት ወደ 8 ቢሊዮን ዶላር እንደሚያሻቅብ፣ ዓለም አቀፍ የመጠባበቂያ ክምችት ደግሞ ከ10 ቢሊዮን ዶላር በላይ እድገት እንደሚያመጣ ትንበያው ገልጿል። የዚህ ትንበያ መነሻ ሃሳብ በመሆን ያገለገለው ሰሞነኛው የኢኮኖሚ ማሻሻያ ፖሊሲ መሆኑ ደግሞ ነገን ተስፋ እንድናደርግ እድል የሚሰጠን ነው።

**በውጪ ምንዛሪ**
**ማሻሻያ ፖሊሲ ዙሪያ እንደማጠቃለያ ሊነሳ የሚችለው ከአተገባበሩ ጋር አብሮ የሚነሳው ተጠባቂው የኢኮኖሚ እድገታችን ነው። ከሌሎች አጋዥ የማክሮ ኢኮኖሚ እሳቤዎች ጋር ተሰልፎ በቀጣይ የተሻለችን ኢትዮጵያ እንድናይ እድል ይፈጥራል**

# ስፖርት





## ትዕግስት አሰፋ በማራቶን የብር ሜዳሊያ በማስመዝገብ የመጀመሪያ ሆናለች

ብርሃን ፈይሳ

በ33ኛው የፓሪስ ኦሊምፒክ የኢትዮጵያ ተሳትፎ በሴቶች የማራቶን ብር ሜዳሊያ ተደምድሟል፡፡ የዓለም የማራቶን ክብረወሰን ባለቤቷ ጀግና አትሌት ትዕግስት አሰፋ እጅግ ፈታኝ በነበረው ፉክክር፤ በመጨረሻዎቹ ሜትሮች ተቀድማ የብር ሜዳሊያ አጥልቃለች፡፡ በዚህም ኢትዮጵያ በመድረኩ 1 የወርቅ እና 3 የብር በጥቅሉ 4 ሜዳሊያዎችን በማግኘት ተሳትፎዋን አጠናቃለች፡፡

በዳገታማነቱ እጅግ ከባድ በተባለው የፓሪስ ኦሊምፒክ ማራቶን፤ በተለይ በሴቶች ምድብ ፍጹም ጠንካራና እስከመጨረሻው አሸናፊ አትሌቶችን መለየት አዳጋች የሆነ ውድድር ተደርጓል፡፡ ምርጥ የዓለም ማራቶን አትሌቶች በተካፈሉበት በዚህ ውድድር በተለይ የኢትዮጵያ፣ የኬንያ እና የኔዘርላንድስ አትሌቶች ትከሻ ለትከሻ ተያይዘው በመሮጥ እስከመጨረሻው ተጉዘዋል፡፡ ርቀቱ ሊጠናቀቅ ጥቂት ሜትሮች ሲቀሩት ተስፈንጥራ የወጣችው ትዕግስት በተፎካካሪዋ የኔዘርላንድስ አትሌት ሲፈን ሃሰን ብትገፈተርም ሚዛኗን ጠብቃ በመሮጥ የወርቅ ሜዳሊያው ለማጥለቅ አድናቆት የተቸረው ትግል አድርጋለች፡፡ በመጨረሻም በኢትዮጵያዊቷ ቲኪ ገላና 2012 ላይ የተመዘገበው የኦሊምፒክ ክብረወሰን በአንድ ደቂቃ ተሻሽሎ በትውልደ ኢትዮጵያዊቷ የኔዘርላንድ አትሌት ሲፈን ሃሰን የበላይነት ሊጠናቀቅ ችሏል፡፡

በዚህ ውድድር ኢትዮጵያን ወክለው የተሳተፉት አትሌት ትዕግስት አሰፋ፣ አማኔ በሪሶ እና መገርቱ ዓለሙ ሲሆኑ፤ ከውድድሩ አስቀድሞ ከፍተኛ አሸናፊነት ግምት አግኝተው ነበር፡ ፡ የኦሮሚያ ፖሊስ አትሌት የሆነችው ትዕግስት ባለፈው ዓመት የበርሊን ማራቶንን 2 ሰዓት ከ11 ደቂቃ ከ53 ሰከንድ በመሮጥ የዓለም ክብረወሰኑን የሰበረችው እንዲሁም በቡዳፔስቱ የዓለም ቻምፒዮን መሆን የቻለችው ጠንካራዋ አትሌት አማኔ በሪሶ ፓሪስ ላይ ያሳዩት የቡድን ሥራ አስደናቂ ነበር፡፡




ከ40ኛው ኪሎ ሜትር በኋላ ለአሸናፊነት ተፎካካሪ ከነበረው ቡድን አማኔ ተቆርጣ ብትቀርም በጽናቷ ለአትሌቶች ሁሉ ተምሳሌት የሆነችው ትዕግስት ግን ለሀገሯ ሜዳሊያውን ለማስመዝገብ እስከመጨረሻው ታግላለች፡፡ በዚህም 2:22:58 በሆነ ሰዓት በሦስት ሰከንድ ተቀድማ የብር ሜዳሊያ ማጥለቅ ችላለች፡፡ ይህም በኦሊምፒክ የሴቶች ማራቶን የብር ሜዳሊያ ያጠለቀች የመጀመሪያዋ ኢትዮጵያዊት አትሌት አድርጓታል፡፡

በኦሊምፒክ የሴቶች ማራቶን በአትሌት ፋጡማ ሮባ የ1996 የአትላንታ ኦሊምፒክ የወርቅ ሜዳሊያ በማግኘት የመጀመሪያዋ አፍሪካዊትና ፈርቀዳጅ ስትሆን ቲኪ ገላና በ2012 የለንደን ኦሊምፒክ በርቀቱ ሁለተኛውን ክብር አስመዝግባለች፡፡ በቀጣዩ የሪዮ ኦሊምፒክ ማሬ ዲባባ የነሃስ ሜዳሊያ ስታገኝ፤ ትዕግስትን ትናንት የብር ጨምሮ አክላበታለች፡፡

ለረጅም ጊዜ በጉዳት ምክንያት ከአትሌቲክሱ ርቃ የቆየችው ትዕግስት በህክምና ባለሙያዎች ዳግም ወደ ሩጫ እንዳትመለስ ቢነገራትም እጅ ሳትሰጥ ጠንክራ በመሥራት የማራቶን የዓለም ክብረወሰን ባለቤትና የኦሊምፒክ የብር ሜዳሊያ አሸናፊ ለመሆን በቅታለች፡፡ በ2022 እና 2023 የበርሊን ማራቶንን በማሸነፍ ለዚህ ኦሊምፒክ ስትታጭ በዝግጅት ወቅት ውድድሩ ወደ ሚካሄድበት ስፍራ በራሷ ወጪ ተጉዛ ጥናት በማድረግ ጭምር ነው ለዚህ ክብር የበቃችው፡፡ አምና የቦስተን ማራቶን አሸናፊ የነበረችው የዓለም ቻምፒዮና አማኔ አብዛኛውን የውድድር ርቀት በተፎካካሪነት በመሮጥ 5ኛ ደረጃን ስትይዝ የገባችበት ሰዓትም 2 ሰዓት ከ23 ደቂቃ ከ57 ሰከንድ ሆኖ ተመዝግቦላታል፡፡ ሌላኛዋ አትሌት መገርቱ ዓለሙ ደግሞ ውድድሩን አቋርጣለች፡፡

በ10ሺህ እና 5ሺ ሜትር ርቀቶች የነሃስ ሜዳሊያ ባለቤት የሆነችው አትሌት ሲፋን ሃሰን በማራቶንም አስደናቂ ብቃት በማሳየት አሸናፊ ሆናለች፡፡ አትሌቷ 2 ሰዓት ከ22 ደቂቃ ከ55 ሰከንድ በሆነ ሰዓት የኦሊምፒክ ክብረወሰንን ከእጇ በማስገባት ጭምር ፓሪስ ላይ 3 ሜዳሊያዎችን አጥልቃለች፡፡ ኬንያዊቷ አትሌት ሄለን ኦቤሪ ደግሞ በ2 ሰዓት ከ23 ሰከንድ ከ10 ሰከንድ በመግባት ለሀገሯ የነሃስ ሜዳሊያውን አስገኝታለች፡፡

በአትሌቲክስ ስፖርት ብቻ በመካከለኛ እና ረጅም ርቀት 33 አትሌቶችን በፓሪስ ኦሊምፒክ ያሳተፈችው ኢትዮጵያ በመድረኩ 1 የወርቅ እና 3 የብር በጥቅሉ 4 ሜዳሊያዎችን በማስመዝገብ ፉክክሯን ቋጭታለች፡፡ በዚህም በዓለም የደረጃ ሰንጠረዥ 46ኛ ላይ ስትቀመጥ በአፍሪካ ደግሞ ኬንያ፣ አልጄሪያ እና ደቡብ አፍሪካን በመከተል 4ኛዋ ሀገር ሆናለች፡፡ ትናንት በተጠናቀቀው በዚህ ኦሊምፒክ ላይም ቻይና፣ አሜሪካ እና ጃፓን በርካታ ሜዳሊያዎችን በማስቆጠር ቀዳሚዎቹን ደረጃዎች ይዘዋል፡፡